# ዘ

**ዘ** ከ"**ወ**" ፊደል ቀጥሎ የሚመጣ የአማርኛ ፊደል (ግእዙ ሆሄ) ::

**ዘሃ "ዝሃ"** ን ተመ.

**ዘለለ**[1] ግ 1. ወደ ላይ እንጣጥ አለ:: *ዘሎ የቤቱን ጣራ በእጁ ነካ*: 2. እመር አለ፥ እግሮቹን ከመሬት ከፍ አድርጎ በማንሳት ከአንድ ቦታ ወደ ሌላ ቦታ ተንቀሳቀሰ፥ ተሻገረ:: *የቦዩን ውሃ በእግሩ ሳይነካ ዘሎ ተሻገረ*:: 3. ተጫወተ፥ ቦረቀ፥ ጨፈረ:: 4. አለፈ፥ ተወ:: *ሶስተኛውን ገፅ ዘሎ አራተኛውን አነበበ*: 5. ከተወሰነው መጠን አለፈ፥ ከፍ አለ፥ በለጠ::

**ዘለህ አትሳደብ** ያለምክንያት፥ ከመሬት ተነስተህ አትሳደብ::

**ዝላይ** ስ 1. ጭፈራ፥ ጨዋታ:: 2. መዝለል፥ እንጣጥ ማለት::

**ዘለል አለ** ግ ላቅ ብሎ ታየ፥ በለጥ አለ::

**ተዘለለ** ግ ታለፈ፥ ተረሳ፥ ተተወ ::

**የማይዘለል** የማይተው፥ የማይታለፍ፥ ቸል የማይባል::

**ተዛለለ** ግ ተጫወተ፥ ተሳፋ ::

***መዛለያ*** ስ 1. *መረማመጃ፥ መሸጋገሪያ*:: 2. *የልጆች መጫወቻ ቦታ* ::

**ዘለለ**[2] ግ በበሰለ ወይም በተብላላ ድፍድፍ ላይ ውሃ ጨመረ፥ ሞላ፥ ሸመ ::

**ዝልል** ስ በበሰለ ወይም በተብላላ ድፍድፍ ላይ ውሃ ከተሞላበት በሏላ ወዲያው በወንፊት ተጣርቶ ሊጠጣ የሚችል የጠላ አይነት ::

**ተዘለለ** ግ በበሰለ ወይም በተብላላ ድፍድፍ ላይ ውሃ ተጨመረ፥ ተሞላ፥ ተሸመ ::

**ዘለላ** ስ 1. (የእንባ) አነስተኛ ጠብታ:: 2. ፍሬ የተሸከመች አነስተኛ ቅርንጫፍ:: *የወይን ዘለላ* ::

**ዘለሰ** ግ 1. ቆረጠ፥ ጣለ፥ አጋደመ፥ ለሸለሸ (ዛፍን):: 2. አቀረቀረ፥ ደፋ (አንገትን)::

***መዘለሻ*** ስ አነስተኛ መጥረቢያ ::

**ዘለሰኛ** ስ ግጥሙ ባለ ሁለት ቤት የሆነ፥ ቀስና ዝግ ወይም ረገብ ተደርጎ የሚዜም የመሰንቆ ምትና ዜማ ::

**ዘለቀ** ግ 1. መጣ:: *ወደዚህ መቼ ትዘልቃለህ?* 2. አንድን ነገር ከመጀመሪያ እስከ መጨረሻ አከናወነ፥ ጨረሰ፥ ተወጣ:: 3. ራቀ:: *ዘልቆ ሄደ::* 4. ቆየ፥ ከረመ፥ ሰነበተ:: *ከረምቱን አብሮን ዘለቀ::* 5 ከአንድ ወገን ጫፍ በመነሳት፥ በውስጥ በኩል አልፎ በሌላው ወገን ጫፍ በኩል ታየ፥ ብቅ አለ::

**ዘልቆታል** 1. ገብቶታል፥ በደንብ አውቋል:: *ትምህርቱ ዘልቆታል*:: 2. እስከ መጨረሻው ሄዷል::

**ዘለቃ** ስ 1. ዘለአለም፥ መጨረሻ:: *እስከ ዘለቃው አንገናኝም*:: 2. ወደፊት:: *ያለፈው አልፏል! ለዘለቃው ግን አስብበት* ::

**ዘለቄታ** ስ ዘለቃ::

**ዘለቄታ የለውም** አይቆይም፥ እድሜ የለውም::

**ለዘለቄታው** ለወደፊቱ፤ እስከመጨረሻው::

**ዘላቂ** ቅ እስከ መጨረሻ የሚሄድ፥ የሚቆይ::

**ዝለቅ** ግ ግባ፥ ጎራ በል::

**ተዘለቀ** ግ ተከናወነ፥ ተፈፀመ፥ ተጨረሰ::

**አይዘለቅም** በቀላሉ አይገፋም፥ ያስቸግራል፥ እንዲህ በዋዛ የሚወጡት አይደለም::

**ተዛለቀ** ግ ተቻችሎ ኖረ፥ ቆየ::

**አዘለቀ** ግ አቆየ፥ አከረመ፥ አሰነበተ፥ የተወሰነ ጊዜ አደረሰ::

**አዛለቀ** ግ 1. እስከ መጨረሻው አብሮ ሆነ፥ ቆየ:: 2. አዋጣ፥ ጠቀመ:: *ሁሌ መጠጣት አያዛልቅም::*

**ዘለበት** ስ ከብረት፥ ከፕላስቲክ ወይም ከቀንድ፥... የሚሰራ የቀበቶ፥... መቆለፊያ::

**ዘለባብዳ "ዘላበደ"** ስር ተመ.

**ዘለንጋ** ስ ከግድግዳ ጋር ተያይዞ ከእንጨትና ከጭቃ የሚሰራ የእቃ መደርደሪያ::

**ዘለአለም (ዘላለም)** ተው.ግ. ሁልጊዜ፥ ዘወትር::

**ዘለአለማዊ** ቅ 1. ቋሚ፥ ኗሪ:: 2. መጨረሻ፥ ፍፃሜ የሌለው::

**ዘለዘለ** ግ 1. ቁራጭ ስጋን በስለት እየሰነጠቀ በመሸንሸን ቅጥነትና ርዝማኔ እንዲኖረው አደረገ:: 2. በጥርሱ ነከሰ፥ ዘነተረ (አካልን)::3. (ዘይ.) አማ፥ አባጨ (ሰውን)::

**ዘለዘል(ዘልዘልቱ)** ቅ (ስድብ) 1. ዘልዛላ:: 2. ዘዋሪ፥ ስራ ፈት፥ ማጋጣ::

**ዘልዛላ** ቅ 1. (ስድብ) ባለጌ፥ ስድ አደግ:: 2. (ስድብ) ዘዋሪ፥ ስራ ፈት:: 3. ያለአግባብ በጣም የረዘመ (ለምሳሌ ልብስ)::

**ዝልዝል** ስ የተዘለዘለ ስጋ::

**ተንዘለዘለ** ግ ተንጠለጠለ፥ ውዝውዝ አለ::

**ተንዘላዘለ** ግ 1. ስራ ፈቶ ወዲያ ወዲህ አለ፥ ባለገ:: 2. አለቅጥ ረዘመ::

**አንዘለዘለ** ግ አንጠለጠለ፥ ውዝ ውዝ እንዲል አደረገ::

**አንዘላዘለ** ግ በአስተዳደግ ጉድለት አባለገ ::

**ዘለገ** ግ ረዘመ፥ በለጠ፥ ከፍ አለ (በቁመት) ::
**ዘለግላጋ** ቅ መለሎ፥ ረጅም ቁመት ያለው ::
***ዘለገለገ**
**ዝልግልግ** ቅ ምልግልግ ::
**ዝልግልግ አለ** ግ ተዝለገለገ፥ ማለገ፥ ሙልጭልጭ አለ ::
**ተዝለገለገ** ግ እንደለሃጭ ተጎተተ፥ ተምለገለገ፥ ማለገ::
**አዝለገለገ** ግ አምለገለገ፥ አዝረበረበ::
**ዘለግላጋ** "**ዘለገ**" ስር ተመ.
**ዘለጎሰ** ግ ሲፅፍ ወይም ሲያነብ ቃልን፥ ፊደልን፥... እየዘለለ፥ እየገደፈ ፃፈ፥ አነበበ::
**ዝልጉስ** ቅ 1. በጥንቃቄ ያልተፃፈ፥ የተገደፈ (ፅሁፍ):: 2. ጥንቃቄ የሌለው፥ ግድ የለሽ::
**ዘለፈ**[1] ግ ነቀፈ፥ ሰደበ::
**ዘለፋ** ስ ነቀፋ፥ ስድብ፥ ቁጣ::
**ዝለፊያ** ዝ.ከ.
**ዘለፈ**[2] ግ 1. ዘለሰ፥ ጣለ፥ አጋደመ(ዛፍን፥...):: 2. ዘንበል፥ ደፋ አደረገ (እንገትን)::
**መዘለፊያ** ስ ትንሽ መጥረቢያ::
***ዘለፈለፈ**
**ዝልፍልፍ(ዘለፍላፋ)** ቅ 1. አቅመቢስ፥ ደካማ:: 2. ለስላሳ፥ ዝንፍልፍል::
**ዝልፍልፍ አለ** ግ ተዝለፈለፈ::
**ዝልፍልፍ አደረገ** ግ አዝለፈለፈ::
**ተዝለፈለፈ** ግ ዛለ፥ አቅም አጣ፥ ደከመ፥ ተልፈሰፈሰ::
**አዝለፈለፈ** ግ አዛለ፥ አቅም አሳጣ፥ አደከመ::
**ዘለፋ** "**ዘለፈ**" ስር ተመ.
**ዘለፍላፋ** "***ዘለፈለፈ**" ስር "**ዝልፍልፍ**"ን ተመ.
**ዘላለም** "**ዘለአለም**" ን ተመ.
**ዘላቂ** "**ዘለቀ**" ስር ተመ.
**ዘላበደ** ግ ያልተያያዘና እውነትነት የሌለው ነገር ተናገረ፥ ቀባጠረ፥ ቀላመደ::
**ዘላባጅ** ቅ ቀላማጅ፥ ቀባጣሪ::
**ዘለባብዳ** ዝ.ከ.
**ዘላን** ስ 1. አንድ ቦታ ላይ ቋሚ የሆነ መኖሪያ ቤት የሌለው፥ ለከብቶቹ ሳርና ውሃ ለማግኘት ሲል እንደየወቅቱ ሁኔታ ከቦታ ወደ ቦታ እየተዘዋወረ የሚኖር ህዝብ:: 2. (ዘይ.) ተቆጣጣሪና ቋሚ አድራሻ የሌለው፥ በፈለገበት የሚያድር ሰው::
**ዘልቆስታል** "**ዘለቀ**" ስር ተመ.

**ዘልዘልቱ** "**ዘለዘለ**" ስር "**ዘልዛላ**" ን ተመ.
**ዘልዛላ** "**ዘለዘለ**" ስር ተመ.
**ዘመመ**[1] ግ 1. አዘነበለ፥ አጋደለ:: 2. ዝማሜ ተብሎ የሚጠራውን የዜማ ስልት ተከትሎ መቋሚያውን (ዘንጉን) ወደግራና ወደቀኝ፥... በማወዛወዝ አብሮ እየተንቀሳቀሰ አዜመ(ደብተራ)::
**ዝማሜ** ስ ከሰውነትና ከመቋሚያ ውዘዋዜ ጋር እየተቀናጀ የሚዜም የአቋቋም የዜማ ስልት::
**አዘመመ** ግ አዘነበለ፥ አጋደለ::
**አዝማሚያ** ስ ዝንባሌ፥ አካሄድ፥ አቅጣጫ (የነገር፥ የእስተሳሰብ፥ የፍላጎት፥...)::
**ዘመመ**[2] ግ የእህልን ነዶ ሞላላ ቅርፅ አስይዞ ከመረ::
**ዘመሚት** ስ ቀላ የሚልና ምስጥ ወይም ጉንዳን የሚመስል ነፍሳት::
**ዘመረ** ግ በድምፁ እያዜመ አመሰገነ፥ አወደሰ፥ ዜማን አሰማ::
**መዘምር** (ብ.ቁ. **መዘምራን**) ስ በዜማ የሚያወድስ፥ የሚያመሰግን፥ የዜማ ባለሙያ የሆነ ደብተራ::
**መዝሙር** ስ 1. በዜማ የተዘጋጀና እሁድ እሁድ በኢትዮጵያ አርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን የሚዘመር የያሬድ ድርሰት:: 2. ከላይ የተጠቀሰውን ድርሰት የያዘ መፅሃፍ:: 3. የተወሰነ የዜማ ስልት ተከትሎ በድምፅ የሚዜም መንፈሳዊ ወይም ስጋዊ ድርሰት::
**መዝሙረኛ** ስ ዘማሪ፥ መንፈሳዊ ወይም አለማዊ የመዝሙር ድርሰትን በዜማ የሚያሰማ (ሰው)::
**ዘማሪ** (ብ.ቁ **ዘማርያን**) ስ መዝሙርን በዜማ የሚያሰማ፤ መዝሙረኛ::
**ዝማሬ** ስ 1. ዜማ:: *የወፎቹ ዝማሬ ከሩቅ ይሰማል::* 2. በዜማ የሚቀርብ ውዳሴ፥ ምስጋና:: 3. ከእጣን ሞገር በፊት በቅኔማህሌት የሚባል ያሬዳዊ የዜማ ድርሰት::
**ዝማሬ መዋስእት** ስ ዝማሬና መዋስእት የሚባሉትን የያሬድ ድርሰቶች በአንድነት የያዘ የዜማ መፅሃፍ::
**አዘመረ** ግ1. ማሲንቆ እየመታ በዜማ ግጥም ደረደረ፥ ዘፈነ (አዝማሪ):: 2. ጮሀ፥ ፎከረ፥ ደነፋ::
**አዝማሪ** ስ 1. በባህላዊ የሙዚቃ መሳሪያዎች እየታጀበ በመዝፈን የሚተዳደር (ሰው):: ቅ 2. (ስድብ) ምላሰኛ፥ ተሳዳቢ::
**ዘመተ** ግ 1. ሄደ፥ ተጓዘ (ለጦርነት፥ ለውጊያ ወይም ለሌላ ተግባር):: 2. ተስፋፋ፥ ተናኘ፥ ተሰራጨ (በሽታ፥ ወሬ፥...):: 3. ተንሰራፋ፥

ተራባ (ኣትክልት፥...)።

**ዘመቻ** ስ 1. ለጦርነት የሚደረግ እንቅስቃሴ፥ ጉዞ። 2. በተወሰነ ጊዜ ውስጥ እንዲጠናቀቅ በህብረትና በርብርቦሽ የሚከናወን ተግባር።

**ዘማች** ስ ወደ ዘመቻ ለመሄድ በዝግጅት ላይ ያለ ወይም የዘመተ ሰው።

**ዘማች ኣሞራ** ስ ወቅቶችን እየጠበቀ ከኣንድ ቦታ ወደ ሌላ ቦታ በመዘዋወር የሚኖር የኣሞራ ኣይነት።

**ተዘመተ** ግ ተራባ፥ ተስፋፋ፥ ተናኘ (በሽታ፥ ወሬ፥...)።

**አዘመተ** ግ 1. በጦርነት ወይም በሌላ ስራ ላይ ኣሰማራ። 2. ግንዱ የራሱን ስርና ቅርንጫፍ በማውጣት እየተራባ እንዲሄድ ለማድረግ ከስሩ ሳይነቀል ቅርንጫፉን ኣፈር ውስጥ እንዲጋደምና ከወደ ኣናቱ ብቻ ቀጥ ብሎ እንዲቆም በማድረግ ኣራባ።

**አዝማች** ስ 1. የዘማቾች ኣለቃ ወይም መሪ። 2. በዜማ፥ በዘፈን ወይም በግጥም ስንኞች መካከል ኣልፎ ኣልፎ ጣልቃ እየገባ በመደጋገም የሚባል የዜማ፥ የዘፈን፥ የግጥም ቃል ወይም ሃረግ።

**አዛመተ** ግ 1. ኣሰራጨ፥ ኣዳረሰ፥ ነዛ። 2. ኣለማ፥ ኣራባ፥ ኣባዛ።

**ዘመነ(ዘበነ)** ግ ዘመናይ ሆነ።

**ዘመን**(ብ.ቁ.**ዘመናት**) ስ ጊዜ፥ ወቅት፥ ኣመት።

**ለዘመናት** ለረጅም ጊዜ፥ ለብዙ ኣመታት።

**ዘመነ ሃዲስ** ስ ከክርስቶስ ልደት ወዲህ ያለው ጊዜ፥ ዘመን።

**ዘመነ ሉቃስ** ስ በዘመነ ማርቆስና በዘመነ ዮሃንስ መካከል ያለው ኣመት፥ ጊዜ፥ ዘመን።

**ዘመነ መሳፍንት** ስ በኢትዮጵያ ከኣስራ ስምንተኛው መቶ ክፍለ ዘመን ኣጋማሽ እስከ ኣስራ ዘጠነኛው መቶ ክፍለ ዘመን ኣጋማሽ ድረስ ስልጣን በመሳፍንት ተከፋፍሎ የነበረበት ጊዜ።

**ዘመነ ማርቆስ** ስ በዘመነ ማቴዎስና በዘመነ ሉቃስ መካከል ያለው ኣመት፥ ጊዜ፥ ዘመን።

**ዘመነ ማቴዎስ** ስ በዘመነ ዮሃንስና በዘመነ ማርቆስ መካከል ያለው ኣመት፥ ጊዜ፥ ዘመን ።

**ዘመነ ብሉይ** ስ የኦሪት ዘመን ።

**ዘመነ ኣስተርእዮ** ስ ከጥምቀት (ከጥር 11 ቀን ጀምሮ) እስከ ሁዳዴ ፆም መግቢያ ያለው ወቅት፥ ጊዜ።

**ዘመነ እንኩቶ** ስ በማንኛውም በኩል ችግር የሌለበት ደግ ጊዜ ።

**ዘመነ ዮሃንስ** ስ በዘመነ ሉቃስና በዘመነ ማቴዎስ መካከል ያለው ጊዜ፥ ዘመን፥ ኣመት ።

**ዘመነ ግርንቢጥ/ግልምቢጥ** ስ እውነት የጠፋበት፥ ሃሰት የሰፈነበት ጊዜ፤ ነገሩ ሁሉ የተገላቢጦሽ የሆነበት፤ የነበረው ባህል፥ ልምድ፥... የተለወጠበት ጊዜ።

**ዘመነ ፅጌ** ስ ከመስከረም 26 እስከ ህዳር 6 ቀን ያለው ጊዜ፤ የኣበባ ወቅት።

**ዘመን መለወጫ** ስ የኣመቱ የመጀመሪያ ቀን፤ እንቁጣጣሽ፤ እንደ ኢትዮጵያ የቀን ኣቆጣጠር መስከረም ኣንድ ቀን።

**ዘመን ኣመጣሽ** ቅ ኣዲስ የተፈለሰፈ፥ የተሰራ፥ የመጣ፥ የታየ፥ የተገኘ ።

**ዘመናዊ** ቅ 1. በኣይነቱ ወይም በሁኔታው ኣዲስ የሆነ። 2. በወቅቱ ያለውን ኣዲስ ሁኔታ (የኣስተሳሰብ፥ የኣኗኗር፥...) የሚከተል ።

**ዘመናይ (ዘበናይ)** ቅ 1. ባለጊዜ፥ እንደፈለገው ለመሆን ጊዜ ያመቸው፥ ኑሮው የተሳካለት። 2. የ"**ዘመናዊ**"ን 2ኛ ፍቺ ተመ.

**ዘመዘመ** ግ 1. ለቁልፍ (ለኣዝራር) ማስገቢያ ተብሎ በልብስ ላይ የሚበጁ የቀዳዳዎችን ኣፍ፥ የልብስን ጠርዝ ወይም ክፈፍ፥... በክር ቀመቀመ። 2. በበርኖስ፥ በጨርቅ፥...ላይ የጥልፍ ስራ ሰራ፥ ጠለፈ።

**ዘምዛሚ** ስ የዝምዝማት ስራ ባለሙያ።

**ዝምዝማት(ዝምዝም)** ስ በጨርቅ ወይም በበርኖስ፥...ላይ የሚሰፋ ቅምቅማት፤ ጥልፍ ።

**ተዘመዘመ** ግ 1. ዳር ዳሩ በክር ተሰፋ፥ ተቀመቀመ። 2. ጥልፍ ተጠለፈበት (በጨርቁ፥ በበርኖሱ፥... ላይ)።

***ዘመደ**

**ዘመድ** ስ 1. በትውልድ የኣባት ወይም የእናት ወገን የሆነ ሰው (ለምሳሌ እኅት፥ እክስት፥ የእኅት ወይም የእክስት ልጅ)። 2 ወዳጅ ።

**ዘመድ ኣፈራ/ኣበጀ/ገዛ** ዘመድ፥ ወዳጅ ኣገኘ።

**ዘመድ ኣዝማድ** ስ ተወላጅ፥ ዝርያ፥ ወገን፤ ቁጥሩ በርከት ያለ ዘመድ።

**የዘመድ ዋጋ** ስ በዝምድና፥ በወዳጅነት ወይም በመተዋወቅ የተነሳ ኣንድን ነገር ከተወሰነው ዋጋ በመቀነስ ለገዥው የሚሸጥበት ዋጋ።

**ዝምድና** ስ 1. ተዛምዶ፤ የዘር ወይም የትውልድ ግንኙነት። 2. መመሳሰል፥ ግንኙነት። *ዝምድና ያላቸው ሃሳቦች የበለጠ ቢብራሩ መልካም ነው።*

**ተዛመደ** ግ 1. ተወዳጀ፥ ተስማማ። 2. ተቀላቀለ፥ ተዋሃደ። 3. ተጋባ፥ በጋብቻ ተሳሰረ፥ ተዋለደ ።

**ተዛምዶ(ተዘምዶ)** ስ ዝምድና ::

**አዛመደ** ግ 1. አወዳጀ÷ አስማማ:: 2. አዋሃደ:: 3. አገናዘበ÷ አመሳሰለ÷ አያያዘ÷ አገናኘ ::

**አዛማጅ** ቅ አገናኝ::

**አዝማች ቅፅል** ስ (ሰዋ.) መስተፃምሩ "የ" በሃላፊ አንቀፅ ላይ እያረፈ ግሱን ከስም ጋር የሚያዛምድ ምእላድ፤ መስተፃምራዊ ቅፅልም ይባላል (ለምሳሌ:- የገባ ያገለግላል በሚለው አነጋገር ውስጥ "የ" አዛማጅ ቅፅል ነው:: በአሁንና በትንቢት ጊዜያት ደግሞ "የም" ወይም "የሚ" ይሆናል:: የምትናገረውን አስበህ ተናገር በሚለው ውስጥ "የም" አዛማጅ ቅፅል ነው)::

**ዘማሪ "ዘመረ"** ስር ተመ.

**ዘማች "ዘመተ"** ስር ተመ.

**ዘማኑም** ስ ጥንበ በላ የአሞራ አይነት::

**ዘማዊ "ዘሞተ"** ስር ተመ.

**ዘምቢል "ዘንቢል"** ን ተመ.

**ዘምባባ "ዘንባባ"** ን ተመ.

**ዘምናና "*ዘበነነ"** ስር **"ዘብናና"** ን ተመ.

**ዘምዛሚ "ዘመዘመ"** ስር ተመ.

**ዘሞተ** ግ ሴሰነ÷ አመነዘረ::

**ዘማዊ** ስ አመንዝራ÷ ሴሰኛ::

**ዝሙት** ስ ሴሰኝነት÷ ሽርሙጥና÷ አመንዝራነት::

**ዝሙት አዳሪ** ስ በሽርሙጥና የምትተዳደር ሴት፤ ሴተኛ አዳሪ::

**ዝሙተኛ** ቅ ዘማዊ÷ አመንዝራ::

**ዘረመትራን(ዘረመትር)** ስ የአሳ መያዣ ወጥመድ፤ መግለቢ::

**ዘረመጠ** ግ በሃይል ወጋ÷ ቀረቀረ÷ ከተተ÷ ዶለ ( ጦር÷ ጋሬጣ÷...)::

**ዘረምቦ "ዘረንቦ"**ን ተመ.

**ዘረረ** ግ 1. ዘረጋ÷ አሰጣ:: 2. አጋደመ:: 3.ጣለ÷ ደበለለ::

**ተዘረረ** ግ 1. ተዘረጋ÷ ተሰጣ:: 2. ተጋደመ÷ ወደቀ÷ተኛ::

**ዘረር** ስ ለናፍጭ የሚመስል÷ በየማሳው ውስጥ በቅሎ የሚገኝ የሳመን አይነት፤ ወፍ ዘረር እየተባለም ይጠራል::

**ዘረ ቆርጥም "ዘራ"** ስር ተመ.

***ዘረበረበ**

**ተዝረበረበ** ግ ተንጠባጠበ (ለሃጭ)::

**አዝረበረበ** ግ አንጠባጠበ::

***ዘረበበ**

**ተንዘረበበ** ግ ተንጠለጠለ÷ ተንዘለዘለ÷ ወደ ታች ወረደ (ከንፈር)::

**አንዘረበበ** ግ አንጠለጠለ÷ አንዘለዘለ÷ ወደታች አወረደ(ከንፈርን)::

**ዘረ ቢስ "ዘራ"** ስር ተመ.

**ዘረነቀ** ግ 1. አለቦታው÷ አለአግባቡ አስገባ÷ ዶለ÷ ጨመረ:: 2. ዘባረቀ÷ ነገር አበላሸ::

**ዘረንቦ (ዘረምቦ)** ስ እድሜው አነስተኛ የሆነ ከጫጩት ከፍ የሚል ዶሮ::

**ዘረኛ "ዘራ"** ስር ተመ.

**ዘረኝነት** ዝ.ከ

**ዘረ አዳም** ዝ.ከ

***ዘረከረከ**

**ዘረክራካ (ዝርክርክ)** ቅ ጥንቁቅ ያልሆነ፤ ጥንቃቄ÷ ብቃት÷ ጥራት÷... የሚያንሰው::

**ዝርክራኪ** ቅ የተንጠባጠበ÷ ውድቅዳቂ::

**ዝርክርክ አለ** ግ ተዝረከረከ::

**ዝርክርክ አደረገ** ግ አዝረከረከ::

**ተዝረከረከ** ግ 1. ተንጠባጠበ÷ እዚህም እዚያም ተበታተነ:: 2. ፅዳት የጎደለው ሆነ፤ በመልክ በመልኩ ያልተሰናዳ ሆነ÷ ምስቅልቅል አለ:: 3. ሳይሰበሰብ÷ ሳይከናወን÷ሳይጠናቀቅ ቀረ:: 4. ተጎለጎለ÷ ወጣ÷ ተነገረ(ምስጢሩ)::

**አዝረከረከ** ግ 1. አንጠባጠበ÷ በታተነ:: 2. ያለ ጥንቃቄ አደረገ÷ ሰራ÷...:: 3. እዚህም እዚያም ምስቅልቅል አደረገ:: 4. ሳይሰበስብ÷ ሳያከናውን÷ ሳያጠናቅቅ ቀረ:: 5. ጎለጎለ÷ አወጣ÷ ተናገረ(ምስጢርን)::

**ዘረከቦ** ቅ ቀፈታም÷ ሆደ ዘርጣጣ::

**ዘረከተ** ግ ቀደደ÷ በሸረከ÷ ሸረከተ::

**ተዘረከተ** ግ ተቀደደ÷ ተሸረከተ::

**ዘረክራካ "*ዘረከረከ"** ስር ተመ.

**ዘረዘረ** ግ 1. እንደ ገብስ÷ ስንዴ÷ በቆሎ÷ ዘንጋዳ÷... የመሳሰለው ቡቃያ አድጎ ማሸት ወይም ማፍራት ጀመረ:: 2. ሸከሸከ፥ ጥቅጥቅ እንዳይል አደረገ (ለምሳሌ ሽማኔ ሽማን):: 3. ነጣጠለ÷ ለያየ÷ በተንተን አደረገ:: 4. ጥርሱ ሳለቀ ማጭድ ጥርስ አበጀ፤ ሞረደ:: 5. ጥቅል ገንዘብን ወደ አነስተኛ ክፍልፋይ ወይም ሽርፍራፊ ገንዘብ ቀየረ÷ ለወጠ፤ መነዘረ:: 6. አልፎ አልፎ ሽበት ጣል ጣል አደረገበት÷ ገብስማ ሆነ (ፀጉር):: 7. ተነተነ÷ ዝርዝር አወጣ÷ ጥቅል የነበረውን አፍታታ::

**ዘረዘረች** ግ ባል ሳታገባ ጊዜው አለፈባት÷ቆማ ቀረች(ልጃገረድ)::

**መዘራዝር** ስ ስራው ሊያልቅ ትንሽ የቀረውና ከፊት ግንድ አካባቢ የደረሰ የሽማ ድር አንድነት እጅብ እያለ ለአሰራር እንዳያስቸግር ሽማኔው ድሩን በከፊል በከፊል እየመደበ የሚያበጀው ቋጠሮ፥ ቁጥረት።

**መዘራዝር ገባ** ተሰርቶ ሊያልቅ ደረሰ (ሽማ)።

**መዝርዝር** ስ ሪፖርት፥ ዘገባ።

**ዘርዛራ** ቅ ያልተጠጋጋ፥ በየመሃሉ ሰፋ ሰፋ ያለ ክፍተት ያለው (ማጭድ፥ ወንፊት፥ ጥርስ፥...)።

**ዘርዛራ ወንፊት** (ዘይ.) ምስጢር የማይደብቅ፥ ወሬኛ።

**ዝርዝር** ስ 1. የጥቅል ገንዘብ ክፍልፋይ፥ ምንዛሪ፥ ሽርፍራፊ። 2. እያንዳንዱ ስም፥ እቃ፥...የተመዘገበበት ፅሁፍ። ቅ 3. በተናጠል ያለ ወይም የተቀመጠ እያንዳንዱ (ነገር)። 4. በዶሮ ጭንቅላት ላይ እንደ ቀንጮ ሆኖ የሚበቅል ስስና ነጠላ ቆዳ፥ ዱልዱም ያልሆነ። *ዝርዝር ዶሮ*። 5. ጥቅጥቅ ያልሆነ፥ የተበታተነ።

**በዝርዝር** አንድ ባንድ፥ በስፋት። *ዜናውን በዝርዝር ነገረኝ።*

**ዝርዝር ውስጥ ገባ** ስለእያንዳንዱ ጉዳይ በስፋትና በጥልቀት ተናገረ ።

**ዝርዝር እርባታ** ስ (ሰዋ.) ግስንና ስምን በተለያዩ መደቦች፥ ፆታና ቁጥር (እኔ፥ አንተ፥ አንቺ፥ እኛ፥...) የመተንተን ተግባር።

**ተዘረዘረ** ግ 1. አንድ ባንድ ተተነተነ፥ ተነገረ፥ ተጠቀሰ። 2. ወደ ቅንስናሽ ገንዘብ ተለወጠ፥ ተመነዘረ (ጥቅሉ ገንዘብ)። 3. ተራራቀ፥ በተን በተን አለ፤ ሳይጠቀጠቅ፥ ሳይጠጋጋ ቀረ።

**ተዘራዘረ** ግ ተሰዳደበ፥ አንዱ የሌላውን ጉድ አወጣ።

**አዘረዘረ** ግ 1. ማፍራት፥ ፍሬ መያዝ ጀመረ። 2. ሽበተ፥ ገብስማ ሆነ (ፀጉር)። 3. መነዘረ።

***ዘረዘረ**

**ተንዘረዘረ** ግ ተንቀጠቀጠ (በእልህ፥ በቁጣ፥ በህመም፥...)።

**አንዘረዘረ** ግ አንቀጠቀጠ (እልህ፥ ቁጣ፥ ህመም)።

**ዘረገፈ** ግ 1. ዘከዘከ፥ ጎለጎለ (ከውስጥ)። 2. ደፋ፥ ገለበጠ፥ አራገፈ። 3. አወጣ፥ ዘረዘረ (ምስጢርን)።

**ዘርጋፋ** ቅ (ዘይ.) ቦርጫም፥ ሆደ ትልቅ።

**ዝርግፍ** ዝ.ክ.

**ዝርግፍ ወርቅ** ስ ከወርቅ የተሰራ የአንገት ጌጥ አይነት።

**ዝርግፍግፍ ወጣ** 1. ተዘረገፈ፥ ተበታተነ። 2. ተጎለጎለ። 3. (ዘይ.) ገዘፈ፥ ወፈረ (ሰውነቱ)።

**ተዘረገፈ** ግ 1. ተዘከዘከ፥ ተጎለጎለ። 2. ተደፋ፥ ተገለበጠ፥ ተበተነ። 3. ቦርጭ አወጣ፥ በጣም ወፈረ።

**ዘረጋ** ግ 1. አጋደመ፥ አንጋለለ፥ አስተኛ። 2. ቀጥ አደረገ፥ አረዘመ። *በጣቶቹ ኮርኒሱን ለመንካት እጁን ዘረጋ/ዛፉ ቅርንጫፎችን በሰፊው ዘረጋ።* 3 ከፈተ፥ ገለጠ። *መፅሃፉን ዘረጋ*። 4. ወጠረ። *ዝናብ እንዳይመታው ጥላውን ዘረጋ* ። 5. ቀጥ አደረገ፥ አቃና፥ አስተካከለ (የተጣጠፈን፥ የተጨበጠን፥ የተጠማዘዘን፥ የተኮማተረን፥ የጎረበን፥...)። 6. አሰጣ፥ አነጠፈ፥ ዘረረ። *የታጠበውን ልብስ ከሽቦው ላይ ዘረጋ/ ምንጣፉን ከወለሉ ላይ ዘረጋ።* 7. ፈታ፥ ተረተረ (የተጠቀለለን)። 8. ጣለ፥ ዘረረ (በዱላ፥ በጥይት፥...)። 9. አቋቋመ፥ አበጀ፥ መሰረተ። *የልማት አውታሮችን ዘረጋ*።

**ዝርግ** ቅ 1. የተዘረጋ፥ ሰታታ፥ ጠፍጣፋ የሆነ። 2. (ስድብ) ስራፈት፥ ሰነፍ።

**ዝርግ ሳህን** ስ ሰታታ የሆነ ወይም ጎድጓዳነት የሌለው የመመገቢያ ሳህን።

**ዝርግት አለ** ግ ወደቀ (በህመም፥ በሞት፥...)።

**ተዘረጋ** ግ 1. ተጋደመ፥ ተኛ። 2. ተወጠረ፥ ተገተረ። 3. ቀና፥ ቀጥ አለ፤ ተስተካከለ። 4. ተመሰረተ፥ ተቋቋመ፥ ተዘጋጀ ።

**ተዘረጋጋ** ግ አቅም አጣ፥ ተዝለፈለፈ፥ ዧ ብሎ ተኛ።

**ተንዘራጋ** ግ ዧ ብሎ ወደቀ።

**አንዘራጋ** ግ ክፉኛ ጣለ (በሽታ ሰውን)።

***ዘረጠ**

**ዘረጦ** ቅ 1. (ስድብ) ፈሳም። 2. ፈሪ፥ ቡከን። 3. ስራፈት፥ አውደልዳይ።

**ዘርጣ** ቅ አፉ እንዳመጣለት የሚናገር፥ ተሳዳቢ፥ ምላሰኛ። *አፈ ዘርጣ* ።

**ዘረጥ አለ** ግ የፈስ ድምፅ ተሰማ።

**ዘረጥ አደረገ** ግ የፈስ ድምፅ አሰማ።

**ዘረጥራጣ(ዝርጥርጥ)** ቅ 1. (ስድብ) ፈሳም፤ ፈሱን እንደ አህያ የሚያጮህ። 2. ፈሪ፥ ቡከን።

**ተዝረጠረጠ** ግ ተንቦቀቦቀ፥ ፈስ በፈስ ሆነ።

**አዘረጠ** ግ ፈሱን እንደ አህያ ዘረጥ አደረገ፥ የፈስ ድምፅ አሰማ።

**አዝረጠረጠ** ግ 1. አምቦቀቦቀ፥ አከታትሎ የፈስ ድምፅ አሰማ፥ አጮሀ። 2. አስጨነቀ፥ አርበደበደ። 3. ጉድ አስወጣ፥ አስጎለጎለ።

**አንዛረጠ** ግ 1. እንደ አህያ ፈሳ፤ ፈሱን አጮሀ፥ አሰማ። 2. አዘጠዘጠ፥ ስራ ፈታ፥ አውደለደለ።

**አንዛራጭ** ቅ ስራ ፈት፥ አውደልዳይ።

**ዘረጠጠ** ግ 1. እግርን ሳበ፥ ጎተተ (ለመጣል)። 2. በጥርሱ ዘነጠለ፥ ቦተረፈ፥ ዘረገፈ፥ ጣለ። *ጅቡ ላሀያዋን ዘረጠጣት* ። 3. ናደ፥ አፈረሰ፥ ዘረገፈ (ክምርን)። 4. ከፊት ከፊት አደረገ፥ አራራቀ። 5. ለአንድ ሰው የሚገባውን ክብር ነሳ፥ አዋረደ (በመጥፎ አነጋገር)።

**ዘርጣጣ(ዘረጠጥ)** ቅ (ስድብ) ቀብዳዳ፥ ቀፈታም፥ ቦርጫም።

**ዝርጥጥ** ዝ.ክ.

**ዝርጥጥ አለ** ግ 1. ክስሩ ሰፋ ያለ ሆነ። *የእሀሉ ክምር ዝርጥጥ ብሏል።* 2. ተንዘረጠጠ።

**ተዘረጠጠ** ግ ተናደ፥ ፈረሰ (ክምር)።

**ተንዘረጠጠ** ግ ተንቀበደደ፥ ተንገፈጠጠ፥ ቦርጫም ሆነ።

**አንዘረጠጠ** ግ አንገፈጠጠ (ሆድን)።

**ዘረጥራጣ** "*ዘረጠ" ስር ተመ.

**ዘረጦ** ዝ.ክ.

**ዘረፈ** ግ 1. ቀማ፥ ነጠቀ፥ ወሰደ (የሌላውን ንብረት)። 2. ጊዜ ሳይፈጅበት በአንድ አፍታ ቅኔ አቀነባብሮ (አሳክቶ) አቀረበ፥ አሰማ፥ ተናገረ። 3. በጣም በርካሽ ገዛ።

**ዘረፋ** ስ 1. የሌላን ንብረት በሃይል መውሰድ፥ ቅሚያ፥ ንጥቂያ። 2. ጊዜ ሳይፈጅ በፍጥነት እየተቀነባበረ በቃል የሚነገር የቅኔ አደራረስ። 3. የርካሽ ግዢ።

**ዘራፊ** ስ 1. ቀማኛ፥ ወንበዴ፥ ነጣቂ። 2. ጊዜ ሳይፈጅበት፥ ወዲያው ወዲያው ቅኔ የማቀናበር፥ የማዘጋጀት፥ የማፍለቅ ችሎታ ያለው (ለቅኔ ተማሪ)።

**ዘራፍ** ስ 1. ጀግንነትን፥ ልበሙሉነትን፥ ድፍረትን፥ ቆራጥነትን፥ አልበገር ባይነትን፥... በማስመልከት፥ ከፍ ባለ ድምፅ የሚባል ፉከራ፤ የፉከራ አዝማች፥ የድንፋታ ቃል። ቅ 2. ቸር፥ ለጋስ፥ ሲሰጥ እጁ የማይሳሳ። *እገሌ እጁ ዘራፍ ነው።*

**ዘራፍ አለ** 1. ተቆጣ፥ ደነፋ፥ *እንዴት ይሆናል አለ።* 2. ፎከረ።

**ዝርፊያ** ስ ቅሚያ፥ ንጥቂያ።

**ተዘረፈ** ግ ተቀማ፥ ተነጠቀ፥ ንብረቱ ተወሰደበት።

***ዘረፈ**

**ዘርፍ** ስ 1. በጃንጥላ፥ በአልጋ ልብስ፥... ዳር ዳር ለጌጥ የሚሰራ መርገፍ። 2. ክፍል፥ ወገን። አጅ. *በኤኮኖሚው ዘርፍ ብዙ እርምጃዎች ተወስደዋል።* 3. (ሰዋ.) በአንድነት እንዲናበቡ ወይም እንዲጣመሩ በሚደረጉ ቃላት ውስጥ "የ" የሚያርፍበት ቃል ምጠሪያ። (ለምሳሌ የቤት ልጅ፤ የእንጀራ እናት፤ ቤተክርስቲያን (የክርስቲያን ቤት) በሚሉት ሃረጎች ውስጥ፥ ልጅ የቤት፣ እናት የእንጀራ፤ ክርስቲያን ደግሞ የቤት ዘርፍ ናቸው)።

**ዘረፍራፋ** ቅ 1. ዘርፍ ያለው። 2. ዝርክርክ።

**ተዛረፈ** ግ ሁለት ወይም ከሁለት የበለጡ ቃላት ተጣምረው የአንድ ቃል መልክ እንዲይዙና በአንድነት እንዲነበቡ ተደረገ፤ ተያያዘ፥ ተጣመረ (ቃልና ቃል)።

**ተዝረፈረፈ** ግ 1. ዘርፉ በዛ፥ ረዘመ። 2. ተዘናፈለ (ፀጉር)። 3. ተዝረከረከ።

**አዛረፈ** ግ (ሰዋ.) ቃልና ቃልን አጣመረ፥ አናበበ፥ አያያዘ፥ ዘርፍና ባለቤት አደረገ።

**አዝረፈረፈ** ግ አዝረከረከ፥ አበላሸ።

***ዘረፈጠ**

**ዘረፈጥ (ዘርፋጣ)** ቅ (ስድብ) ከተቀመጠበት የማይነሳ፥ ሰነፍ፥ ረሀጥ፥ ስራ የማይችል፥ ገልቱ።

**ዝርፍጥ** ዝ.ክ.

**ተዘረፈጠ** ግ በስንፍና ወይም በግዴለሽነት እግሩን ዘርግቶ ተቀመጠ።

**ተንዘራፈጠ** ግ ተመቻችቶ፥ ተደላድሎ፥ እንደልቡ ተቀመጠ።

**አንዘራፈጠ** ግ አመቻችቶ፥ አደላድሎ አስቀመጠ።

***ዘረፈፈ**

**ዘረፈፍ (ዘርፋፋ)** ቅ 1. ከርፋፋ፥ ቀርፋፋ። 2. በጣም ረዥም በመሆኑ መሬት ሊነካ የደረሰ (ለምሳሌ ልብስ፥ የዛፍ ቅርንጫፍ)።

**ዝርፍፍ አለ** ግ ተንዘረፈፈ።

**ዝርፍፍ አደረገ** ግ አንዘረፈፈ።

**ተንዘረፈፈ** ግ 1. አለቅጥ ረዘመ (ለምሳሌ ልብስ፥ መጋረጃ)። 2. ተንቀረፈፈ፥ ተንቀረደደ፥ ተጎተተ።

**አንዘረፈፈ** ግ 1. አለቅጥ አስረዘመ (ለምሳሌ ልብስን)። 2. አንቀረፈፈ፥ ጎተተ።

**ዘረፋ** "ዘረፈ" ስር ተመ.

**ዘረፍራፋ** "*ዘረፈ" ስር ተመ.

**ዘራ** ግ 1. እንዲበቅል በመሬት ላይ በተነ፥ ረጨ፥ ነሰነሰ (ዘርን)። 2. ነዛ፥ አዳረሰ፥ ናኘ (ወሬን፥ በሽታን)። 3. (ዘይ.) በተነ፥ አባከነ (ገንዘብን)።

**'ዘር** ስ 1. ሲዘሩት የሚበቅል ፍሬ (የእፅዋት፥ የእህል፥...)። 2. ልጅ (የሰው፥ የእንስሳ)። 3. ወገን፥ ዘመድ፥ ትውልድ፥ ተወላጅ። 4. በግብረ ስጋ ግንኙነት ጊዜ ከወንዱ አባለ ዘር የሚወጣው ፈሳሽ። 5 የፊደላት ቅርፅ ወይም መልክ። *ልጁ የፊደላትን ዘር በሚገባ ለይቷል።*

**ዘር ቆጠረ** የትውልድ ሃረግን ተነተነ፥ ዘረዘረ።

**ዘር ተካ** ወለደ።

**ዘር ይመስክር** ከቶም ሆነ ደግ የወላጅ የስራ ውጤት በልጅ ላይ ይታይ (በልጅ መባረክ ወይም መረገም ይገለፅ)።

**ዘር ይውጣልህ** (ምር.) ዘርህ፥ ትውልድህ ይባረክ፥ ደህና ልጆች ይብቀሉበት።

**ዘርህ ይለምልም** (ምር.) ዘርህ ይባረክ፥ ይበርክት ፥ ይብዛ።

**ዘረቆርጥም** ቅ 1. የዘሩበትን የማያበቅል (መሬት)። 2. የተማረውን ትምህርት በቶሎ የሚረሳ (ሰው)። 3. የተማረውን ለሌላ ሳያስተምር የቀረ (ምሁር)።

**ዘረቢስ** ቅ (የን.አነ.) የመጣበት የማይታወቅ።

**ዘረአዳም** ስ (ኢ.አ.ተ.ቤ.) 1. ለኔቢጤ ወይም ለባይተዋር በነፃ የሚደረግ ኣጠር ያለ የፀሎተ ፍትሃት አይነት።2. የሰው ዘር።

**ዘር ማንዘር (ዘራንዘር)** ስ የአንድ ነገር ዝርያ በአጠቃላይ።

**የዘር ሃረግ** ስ የዘር፥ የትውልድ አመጣጥ፥ ተዛምዶ።

**የዘር ልዩነት** ስ አንዱን የሰው ዘር በመደገፍና ከፍ ከፍ በማድረግ ሌላውን ዘር የማገለል፥ የመጫን፥ የመለየት፥ የመጨቆን ድርጊት።

**የዘር መድልዎ** ስ በዘር ላይ ተመስርቶ በሰዎች ላይ የሚደረግ አድልዎ፥ ተፅእኖ።

**የዘር ወራት** ስ ዘር የሚዘራበት ወቅት።

**የዘር ግንድ** ስ የአንድ ቤተሰብ ወይም ተወላጆች ከስር ተያይዞ የመጣ ዋነኛው መስመር (የዘር አባት ወይም እናት)።

**ዘረኛ** ቅ ሰዎችን በዘር ከፋፍሎ የሚያጋጭና በዘር ምክንያት ለአንዱ እያደላ ሌላውን የሚጎዳ፥ የዘረኝነት አስተሳሰብን፥ አመለካከትን የሚያራምድ።

**ዘረኝነት** ስ የዘር ልዩነት፤ በዘር መድልዎ ላይ የተመሰረተ አስተምህሮ፥ ፖሊሲ አመለካከት።

**ዝሪት** ስ ተዘርቶ የበቀለ የእህል ቡቃያ።

**ዝር** ስ በማሳ ላይ የተዘራ፥ የተበተነ እህል።

**ዝርያ** ስ 1. ዘመድ፥ ወገን፥ ነገድ፥ ተወላጅ። 2. አይነት።

**ተዘራ** ግ 1. በእርሻ ላይ ተበተነ፥ ተረጨ (ዘር)። 2. ተሰራጨ፥ ተራባ።

**አዘራ** ግ የእህልን ፍሬ ከገለባ ወይም ከአብቅ ለመለየት ወደላይ እየበተነ አነፈሰ፥ ለንፋስ ሰጠ።

**አዘራች** ሽል ያዘች፥ አረገዘች (ላም)።

**ዘራፊ** "ዘረፈ" ስር ተመ.

**ዘራፍ** ዝ.ከ.

**ዘር** "ዘራ" ስር ተመ.

**ዘርማንዘር** ዝ.ከ.

**ዘርዛራ** "ዘረዘረ" ስር ተመ.

**ዘርጋፋ** "ዘረገፈ" ስር ተመ.

**ዘርጣ** "ዘረጠ" ስር ተመ.

**ዘርጣጣ** "*ዘረጠጠ" ስር ተመ.

**ዘርጭ እንቧይ** ስ ቁመቱ አስተናግር የሚያህል፥ አተር የሚያካክሉ ፍሬዎች ያሉት፥ ግንዱና ቅጠሉ ላይ እሾህ ያለበት የእፅዋት አይነት።

**ዘርፋጣ** "ዘረፈጠ" ስር ተመ.

**ዘርፋፋ** "ዘረፈፈ" ስር ተመ.

**ዘርፍ** "*ዘረፈ" ስር ተመ.

**ዘቀዘቀ** ግ 1. የላዩን ወደ ታች አደረገ፥ ገለበጠ፥ ደፋ። 2. ጋዳላ፥ ዘንባላ፥ ቆልቋላ እንዲሆን አደረገ። 3. ጋዳላ፥ ዘንባላ ሆነ፥ አቆለቆለ። 4. ወደ ታች ወረደ፥ አመራ፥ ተጓዘ።

**ዘቅዛቃ** ቅ 1. ዘንባላ፥ ጋዳላ፥ ቆልቋላ። 2. ተዳፋት፥ ቁልቁለት (መንገድ)።

**ዝቅዝቅ** ቅ 1. ቁልቁል። 2. ጥለቱ ወይም መቋጫው እንደቀሚስ ጥለት በእግር አቅጣጫ እንዲሆን ተደርጎ የተዘጋጀ (ጋቢ፥ ኩታ)።

**ተዘቀዘቀ** ግ 1. ከወደ ላይ በኩል የነበረው ወይም ከላይ መሆን የነበረበት ወደታች በኩል ሆነ። 2. ከራሱ በኩል ወደ ታች፥ ከእግሩ በኩል ወደ ላይ ሆነ።

**አዘቀዘቀ** ግ አቆለቆለ፥ ወደ ታች ወረደ፥ ሄደ።

**አዘቀዘቀች** በግርጌ በኩል የሚውለውን የነጠላ ጫፍ በራስጌ በኩል አድርጋ ለበሰች፤ አሸረጠች (በሃዘን ምክንያት)፤ ዘቅዝቃለችም ይባላል።

**ዘቀጠ** ግ 1. ሰመጠ፥ ዘገጠ፥ ወደ ስር ወረደ (በፈሳሽ ውስጥ)። 2. ሰረገ፥ ወደ መሬት ውስጥ ገባ፥ ተቀመጠ (ፈሳሽ)። 3. (ዘይ.) በአስተሳሰቡ፥ በአደራጎቱ ብልሹ፥ አጥፊ ሆኖ ተገኘ፥ አሽቆለቆለ ወራዳ ሆነ።

**ዝቃጭ** ስ ከፈሳሽ ስር ተኝቶ የሚገኝ እንደ አተላ ያለ አሰር፥ ቆሻሻ።

**ዝቃጪም** ቅ (ስድብ) ቆሻሻ።

**ዝቅጥቃጭ** ስ በብዛቱም ሆነ በአይነቱ በርከት ያለ ዝቃጭ።

**አዘቀጠ** ግ ዘቀጠ።

**ዘቃቅቤ (ዝቃቅቤ)** ስ በቅመምነት የሚያገለግል አነስተኛ ተክል፤ በሶብላ።

**ዘቅዛቃ** "ዘቀዘቀ" ስር ተመ.

**ዘበለለ** ግ ትልቅና ደንዳና የሆነ አይነ ምድር አወጣ፥ ተፀዳዳ።

**ዘበተ** ን 1. ተሳለቀ፥ ቀለደ፥ አሳገጠ፥ አሽሟጠጠ:: 2. ዛተ፥ ፎከረ፥ አስፈራራ::

**መዘበቻ** ስ መሳለቂያ፥ መቀለጃ፥ መተረቻ::

**ዘበት** ስ ቀልድ፥ ለግጥ፥ ፌዝ፥ ቧልት::

**ዘበት ነው** ቀልድ ነው፤ አይሆንም፥ አይደረግም::

**ዝብብት** ስ ስላቅ፥ ሽሙጥ፥ ፌዝ፥ ቧልት::

**ተዘባበተ** ን ተሳለቀ፥ ቀለደ፥ አሾፈ፥ አፌዘ::

**መዘባበቻ** ስ 1. መቀለጃ፥ ማሾፊያ፥ መተረቻ:: 2. መዛዛቻ፥ መፎካከሪያ::

**ዘበተረ** ን ቦጨቀ፥ ቦተረፈ፥ ዘነተረ::

**ዘበት** "ዘበተ" ስር ተመ.

**ዘበነ** "ዘመነ"ን ተመ.

***ዘበነነ**

**ዘብናና (ዘምናና)** ቅ ኩራተኛ፥ ቀብራራ::

**ዝብንን አለ** ን ተዘባነነ::

**ዝብንን አደረገ** ን አዘባነነ::

**ተዘባነነ** ን ተኩራራ፥ ተንቀባረረ::

**ተዘባናኝ** ቅ ኩራተኛ::

**አዘባነነ** ን አኩራራ፥ አንቀባረረ::

**ዘበናይ** "ዘመነ" ስር "ዘመናይ"ን ተመ.

**ዘበኛ** "ዘብ" ስር ተመ.

**ዘበዘበ** ን 1. ነተረከ፥ ነዘነዘ፥ ጨቀጨቀ:: 2. ነገር አስረዘመ፥ አንዛዛ::

**ዘብዛባ** ቅ ነትራካ፥ ነዝናዛ፥ ጨቅጫቃ:: 2. ነገር ቶሎ የማይቆርጥ::

**ዘበጠ** ን 1. መታ (በዱላ):: 2. ተለመጠ፥ ጎበጠ:: 3 ጎደጎደ (መሬት)::

**ዘባጣ** ቅ 1. ጎባጣ፥ ለማጣ:: 2. የጎደጎደ፥ ረባዳ (መሬት)::

**ዘብጥ** ዝ.ከ.

**ተዘበጠ** ን ተመታ::

**አዘበጠ** ን 1. ዘባጣ አደረገ:: 2. ዘበጠ::

**ዘበጦ (ዘብጣጣ)** ቅ (ስድብ) ቂጣም::

**ዘቢብ** ስ የደረቀ የወይን ፍሬ::

**ዘባ** ን ጎብጥ አለ፥ ተለመጠ፥ ተጣመመ::

**ተዛባ** ን 1. ጎብጥ አለ፤ ተዛነፈ፥ መስመሩን ለቀቀ:: 2. ተሳሳተ፥ ተጣመመ::

**አዛባ** ን 1. አዛነፈ፥ መስመሩን እንዲለቅ አደረገ:: 2. አሳሳተ፥ አጣመመ:: *ነገሩን አዛብቶ አቀረበ::*

**ዘባረቀ** ን 1. አምታታ፥ ደባለቀ፥ አሳሳተ (ሃሳብን ወይም ሌላ ነገርን):: 2. የሆነ ያልሆነውን ተናገረ::

**ዘባራቂ** ቅ አምታች፥ ነገር የሚያሳክር፥ እንደመጣለት የሚለፈልፍ::

**ተዘባረቀ** ን ተደባለቀ፥ ተቀላቀለ፥ ተምታታ::

**ተዘበራረቀ** ን ተደበላለቀ፥ ተመሰቃቀለ፥ ተምታታ፥ ግልፅነት አጣ::

**አዘባረቀ** ን አምታታ፥ አደባለቀ፥ ስርአት አሳጣ::

**አዘበራረቀ** ን አመሰቃቀለ፥ አደበላለቀ፥ አምታታ::

**ዘባተሎ** ስ ቡትቶ፥ የተቀዳደደ ልብስ::

**ዘባተሏም** ቅ (የን. አነ.) ዘባተሎ የሚለብስ፥ ቡቱቷም::

**ዘባጣ** "ዘበጠ" ስር ተመ.

**ዘብ** ስ በጥበቃ ስራ ላይ የተመደበ ሰው::

**ዘብ ቆመ** በጥበቃ ስራ ላይ ሆነ፥ ተሰማራ::

**ዘብ ጠባቂ** ስ ዘበኛ::

**ዘበኛ** ስ መስሪያ ቤቶችን ወይም የግለሰቦችን ቤትና ንብረት የሚጠብቅ ሰው::

**ዘብናና** "ዘበነነ" ስር ተመ.

**ዘብዛባ** "ዘበዘበ" ስር ተመ.

**ዘብጣጣ** "ዘበጠጥ"ን ተመ.

**ዘብጥ** "ዘበጠ" ስር ተመ.

**ዘብጥያ** ስ እስር ቤት::

**ዘብጥያ ወረደ** እስር ቤት ገባ፤ ታሰረ::

***ዘቦጠቦጠ**

**ዝቡጥቡጥ** ቅ 1. የወፈረ፥ የደፈረሰ፥ ያልጠራ (ጠላ ወይም ፈሳሽነት ያለው ነገር):: 2. ጓጓላ ያለበት፥ በወጉ ያልተበጠበጠ (ለምሳሌ ተልባ):: 3. በሚያስጠላ ሁኔታ የወፈረ (ሰው)::

**ዝቡጥቡጥ አለ** ን ተዝቦጠቦጠ::

**ዝቡጥቡጥ አደረገ** ን አዝቦጠቦጠ::

**ተዝቦጠቦጠ** ን 1. በወፍራሙ ተበጠበጠ፤ ጓጓላ ሆነ:: 2. ያለ ልክ ወፈረ::

**አዝቦጠቦጠ** ን በወፍራሙ በጠበጠ፤ አጓጎለ:: 2. ያለ ልክ አወፈረ::

**ዘች**

**ዘች ዘች አለ** ን ሮጥ ሮጥ፥ ዘጭ ዘጭ አለ (የወፍራም ሰው አሯሯጥ)::

**ዘነቀ** ን ቀየጠ፥ ቀላቀለ፥ ደባለቀ፥ ጠመረ::

**ዝንቅ** ቅ ቅይጥ፥ ድብልቅ፥ ቅልቅል::

**ዝንቅ ኢኮኖሚ** ስ ቅይጥ ኢኮኖሚ::

**ተዘነቀ** ን ተቀላቀለ፥ ተቀየጠ፥ ተደባለቀ::

**ተዛነቀ** ዝ.ከ.

**አዛነቀ** ን አደባለቀ፥ አቀያየጠ::

**ዘነቆለ** ግ ወጋ፥ ጠነቆለ፥ ደነቆለ።

**ዘንቋል** ቅ የነገር ስልት የማያውቅ፥ ዘባራቂ፥ ነገር የሚያበላሽ።

**ዘነበ (ዘነመ)** ግ ከሰማይ፥ ከዳመና ወስጥ ዝናብ ወረደ፥ ወደ መሬት ተንጠባጠበ።

**ዘነበለት** አገኘ (ገንዘብ)።

**ዝናብ (ዝናም)** ስ ከላይ፥ ከሰማይ፥ ከዳመና ወደ መሬት የሚወርድ የውሃ ነጠብጣብ።

**ዝናቡን ለግቧል** በቂ ዝናብ ዘንቧል።

**ዝናቡን ቀዳው** በጣም ዘነበ።

**ዝናብ መታው / ደበደበው** ዝናብ አበሰበሰው፥ ዘነበበት።

**ዝናብ ጣለ** ዝናብ ዘነበ።

**የዝናብ ልብስ** ስ ውሃ የማያስገባ፥ በዝናብ ጊዜ የሚለበስ ልብስ።

**ዝናባማ** ቅ ዝናብ የሚበዛበት፥ ብዙ ጊዜ የሚዘንብበት (ቦታ፥ አካባቢ፥ ሃገር፥ ...)።

**አዘነበ** ግ 1. ዝናብ እንዲጥል አደረገ። 2. (ዘይ.) አዥጎደጎደ (ስድብን፥ ...)።

***ዘነበለ**

**ዘንባላ** ቅ ወደ አንድ ወገን ጋደል፥ ዘመም ያለ።

**ዝንባሌ** ስ 1. አዝማሚያ። 2. ምርጫ፥ ፍላጎት። *የሰነ ፅሁፍ ዝንባሌ አለው።*

**ዘንበል አለ** ግ 1. ወደ አንድ ወገን ዘመም፥ ጋደል አለ። 2. ወደ አንድ ወገን አደላ።

**ዘንበል አደረገ** ግ ጋደል፥ ዘመም አደረገ።

**አዘነበለ** ግ 1. አጋደለ፥ አዘመመ። 2. አደላ (የፍላጎት፥ የምርጫ)።

**ዘነተረ** ግ ቦጨቀ፥ ቦተረፈ።

**ተዘነተረ** ግ ተቦጨቀ፥ ተቦተረፈ።

***ዘነከተ**

**ዘንካታ** ቅ ያማረ፥ ውብ፥ መለሉ።

**ተዘናከተ** ግ ተዋበ፥ አማረ (በአረማመድ፥...)።

**ዘነዘነ** ግ ከፋፈለ፥ ሸነሸነ፥ አደላደለ።

**ዝነዘና** ስ ሽንሸና፥ ድልደላ።

**ተዘናዘነ** ግ ተከፋፈለ።

**አዘናዘነ** ግ ሸነሸነ፥ አከፋፈለ።

**ዘነዘና[1]** ስ ከወፍራም እንጨት ወይም ከብረት የተሰራ መውቀጫ፤ የሙቀጫ ግልገል (ስእሉን ሙቀጫ ስር ተመ.)።።

**ዘነዘና[2]** ስ 1.ውስጠ ክፍት የሆነ የእፅዋት አይነት። 2. ከዘነዘና እንጨት የሚሰራ ውኸርሞ፤ የጋያ ጨስ መማጊያ።

**ዘነጋ** ግ ረሳ፥ ሳያስታውስ ቀረ።

**ዝንጉ** ቅ 1. የሚረሳ፥ የማያስታውስ። 2. ቸልተኛ፥ ተላላ።

**ዝንጋታ** ስ መርሳት።

**ተዘነጋ** ግ ተረሳ።

**ተዘናጋ** ግ ሳይጠነቀቅ ቀረ፥ ቸል አለ፥ ተሳነፈ።

**አዘናጋ** ግ 1. አረሳሳ፥ አታለለ። 2. አስረሳ።

**አዘናጊ** ቅ ሆን ብሎ የሚያረሳሳ።

**አዘነጋ** ግ አረሳሳ፥ አዘናጋ፥ አታለለ።

**ዘነጠ** ግ 1. ተሸቀረቀረ፥ አማረ፥ አጌጠ፥ ቆነጀ። 2. (ዘይ.) ተኩራራ።

**ዘናጭ** ቅ 1. አለባበሱን የሚያሳምር፥ ሸቅርቅር። 2. ጥሩ፥ ሸጋ።

**አዘነጠ** ግ አሸቀረቀረ፥ አስጌጠ፥ አሳመረ።

**ዘነጠለ** ግ 1. ቀደደ። 2. ገነጠለ፥ ከዋናው አካል ለየ። 3. ቦጨቀ፥ ቦተረፈ። *ጅብ የዘነጠለው ይመስላል።* 4. በዝንጥል መታ፥ ደበደበ። 5. ያነባበብን ስርአት እያበላሸ አነበበ። 6. (ዘይ.) አክብሮት ለሚገባው ሰው ተገቢውን አክብሮት ሳይሰጥ ቀረ (ለምሳሌ "እርስዎ" መባል የሚገባቸውን ሰው "አንተ" ወይም "አንቺ" እያለ አናገረ)።

**ዝንጣይ** ስ ግንጣይ፤ የተገነጠለ የዛፍ ቅርንጫፍ ወይም የሌላ አካል ክፍል።

**ዝንጥል** ዝ.ከ.

**ተዘነጠለ** ግ 1. ተቀደደ፥ ተሸረከተ። 2. ተቦጨቀ፥ ተቦተረፈ። 3. ተዘነጠፈ፥ ተቆረጠ፥ ተገነጠለ። 4. ቦርጫም ሆነ፥ ሆዱ ተንቀበደደ።

**ዘነጠፈ** ግ ገነጠለ፥ ዘነጠለ፥ ቆረጠ፥ ቀጠፈ።

**ዘንጣፋ** ቅ ረዥም፥ ዠርጋዳ፥ ጥሩ አቋም ያለው።

**ዝንጣፊ** ቅ የተቆረጠ ቅርንጫፍ።

**ተዘነጠፈ** ግ 1. ወረደ፥ ዱብ አለ። 2. ተዘረረ፥ ወደቀ።

***ዘነፈ**

**ዝንፈት** ስ ተባለጥ፥ እላፊ፤ የሸማ ፈርጆች መበላለጥ፥ ያንዱ ፈረጅ ርዝመት ከመንትያው ዝቅ ወይም ከፍ ብሎ መገኘት።

**ዝንፍ እንዳትል** 1. ከአካባቢው ዞር እንዳትል፥ እንዳትነቃነቅ፥ ወደሌላ አቅጣጫ እንዳትሄድ። 2. ቃልህን፥ ሃሳብህን፥... እንዳትቀይር።

**ተዛነፈ** ግ 1. ከመስመር ወጣ፥ ተዛባ፥ ተንጋደደ። 2. ተበላለጠ፥ አንዱ ከሌላው (ከአጣማሪው) ጋር ርዝመቱ ሳይመጣጠን ቀረ፥ ተረፈ (የነጠላ ወይም የጋቢ ፈርጅ)።

**ተዛነፍ** ስ ከፍና ዝቅ የማለት፥ ያለመስተካከል ሁኔታ::

**አዛነፈ** ግ 1. ከመስመር አወጣ፥ አዛባ፥ አንጋደደ፥ አወላገደ:: 2. አበላለጠ፥ አንዱ ፊርጅ ከአጓዳኙ እንዲያንስ ወይም እንዲበልጥ አደረገ::

***ዘነፈለ**

**ዘንፋላ** ቅ 1. ውብና ለስላሳ የሆነ፥ የሚያምር (ለምሳሌ ፀጉር):: 2. አቋሙ የሚማርክ፥ በምቾት የተያዘ፥ ሸበላ፥ ዠርጋዳ::

**ተዘናፈለ** ግ 1. ረጅምና ለስላሳ ሆኖ አደገ (ፀጉር):: 2. በመጠኑ ጋደም፥ ዘንበል አለ (ለምሳሌ የተመቻውና ቀመናው ያማረ ሰብል)::

**ዘና** ግ 1. ረታ፥ ቀና፥ ተፍታታ፥ ተዘረጋጋ (ተኮራምቶ፥ ተጨማትሮ የነበረ አካል):: 2. ረጋ፥ አረፈ፥ ሃሳቡን ጣለ::

**ዘና አለ** ግ 1. ተዘናጋ:: 2. ተመቻቸ፥ ተደላደለ፥ በድሎት ላይ ሆነ::

**ተዛና** ግ 1. ተፍታታ፥ ተዘረጋጋ:: 2. ሃሳቡን ጣለ፥ ተደሰተ፥ እንደልቡ ሆነ፥ ተመቻቸ:: 3. ቀበጠ፥ ተቀናጣ:: 4. ተዘናጋ፥ ቸል አለ::

**ተዝናና** ግ 1. ተዛና፥ በልዩ ልዩ ነገር ራሱን አስደሰተ:: 2. ሰውነቱን አፍታታ:: 3. ተኩራራ:: 4. ተቀናጣ፥ ቀበጠ::

**መዝናኛ** ስ የመደሰቻ፥ የማረፊያ ቦታ ወይም ጊዜ::

**አዝናና** ግ 1. በልዩ ልዩ ነገር አስደሰተ:: 2. እንዲፍታታ፥ እንዲዘረጋጋ፥ እንዲመቻች፥ እንደልቡ እንዲሆን አደረገ::

**አዝናኝ** ቅ አስደሳች::

**ዘናና** ቅ ጭንቅላቱ ወይም ራሱ ትልቅ ሆኖ ወደ አንድ በኩል ዘንበል ያለ::

**ዘናጭ** "ዘነጠ" ስር ተመ.

**ዘንቁል** "ዘነቆለ" ስር ተመ.

**ዘንቢል (ዘምቢል)** ስ ከሰሌን ወይም ከቃጫ፥... የሚሰራና በእጅ የሚንጠለጠል የእቃ መያዣ::

**ዘንባላ** "ዘነበለ" ስር ተመ.

**ዘንባባ (ዘምባባ)** ስ የሰሌን ዛፍ አይነት::

**ዘንቾ** ስ ወደ ትልቅ ሪቅ ወይም ጎተራ ወስጥ ለመግባት ሲፈለግ በመረጋገጫነት እንዲያገለግል ተብሎ የሪቁን ወይም የጎተራውን ቁመት በማካከል አግድም የሚሰካ እንጨት::

**ዘንካታ** "ዘነከተ" ስር ተመ.

**ዘንድ** 1. ከስምና ተውላጠ ስም ጋር እየገባ ቦታን፥ በአጠገብ መገኘትን፥ ... የሚያመለክት ቃል:: *መፅሃፉን እሱ ዘንድ ታገኘዋለህ/መፅሃፉ ከበደ ዘንድ ነው::* 2. በትንቢት አንቀፅ ከሚነገር ግስ ጋር እየገባ ግሱ እንዳያስር የሚያደርግ ቃል:: *በዝግጅቱ ላይ ይገኙ ዘንድ ተጋብዘዋል::*

**ዘንድሮ** ይህ አመት፤ አሁን ያለንበት፥ የያዝነው አመት::

**ዘንዶ** ስ ርዝመቱና መጠኑ በጣም ትልቅ የሆነ የእባብ አይነት::



ዘንዶ

**ዘንጋዳ** ስ መጠኑና ቅርፁ ማሽላ የሚመስል የአገዳ እህል::

**ዘንግ** እንደምርኩዝ ወይም በትር ሆኖ የሚያገለግል ቀጠን፥ ረዘምና ቀጥ ያለ እንጨት ወይም ብረት::

**ዘንጣፋ** "ዘነጠፈ" ስር ተመ.

**ዘንፋላ** "*ዘነፈለ" ስር ተመ.

**ዘከረ** ግ 1. ሰጠ፥ መፀወተ:: 2. በእግዚአብሄር፥ በፃድቃን፥... ስም ዝክር አዘጋጅቶ አበላ፥ አጠጣ:: 3. የተዘጋጀውን ጠበል ጠዲቅ ፀሎት አድርጎ ባረከ:: 4. አሰበ፥ አስታወሰ::

**መዘከሪያ** ስ ፀሎት እንዲደረግበትና እንዲባረክ ከዝክር ድግስ ላይ በትንሹ የሚወሰድ ጠበል ጠዲቅ::

**ዝክር** ስ በእግዚአብሄር፥ በፃድቃን፥... ስም የሚዘጋጅ ጠበል ጠዲቅ፤ ድግስ::

**ተዘከረ** ግ 1. ሰጠ፥ መፀወተ:: 2. ታወሰ፥ ታሰበ:: 3. የተዘጋጀው ጠዲቅ ፀሎት ተደረገበት ተቀረሰ::

**ተዝካር** ስ በሙታን ስም የሚዘጋጅ የመታሰቢያ ድግስ (ምግብና መጠጥ)::

**ተዝካሩ ተበላ** አለቀለት፥ አበቃ::

**ተዝካሩ ወጣ** 1. አለቀለት፥ አበቃ:: 2. ለሞተ ሰው የአርባ ወይም የሰማንያ ቀን መታሰቢያ ተደገሰለት::

**አዘከረ** ግ ዝክር አደረገ፥ ደገሰ::

**አዝካሪ** ስ የዝክር ድግስ አዘጋጅቶ የሚያበላ፥ የሚያጠጣ ሰው::

**ዘከዘከ** ግ 1. ዘረገፈ፥ አራገፈ፥ ገለበጠ:: 2 በሃይል ነከሰ፥ በጥርሱ በተረፈ፥ ወጋ:: 3. በስለት ወጋ፥ ቀደደ፥ ዘነጠለ:: 4. ዘረዘረ፥ ሸከሸከ፥ ማግን አራርቆ ጣለ:: 5. ተፈላጊውንና የማይፈለገውን ሳይለይ በሙሉ አሳለፈ፥ አወረደ (ወንፊት):: 6. (ዘይ.) የሚያውቀውን ሁሉ አወራ፥ ምስጢር አወጣ::

**ዘክዛካ(ዝክዝክ)** ቅ 1. ዘርዛራ፥ ሽክሽክ፥ ያልተጠቀጠቀ (ልብስ፥ ወንፊት፥...)። 2. (ዘይ.) ምስጢር የማይጠብቅ፥ ወሬኛ።

**ዘካ** ስ በእስልምና ሃይማኖት ከማንኛውም የስራ ውጤት ከአስር አንድ የሚሰበሰብ አስራት፥ የአስራት ክፍያ፤ ምፅዋት።

**ዘኬ** ስ 1. ለተዝካር ተብሎ የሚዘጋጅ እንጀራ፥...። 2. ለሙታን መታሰቢያ ተብሎ የሚዘጋጅ መክፈልት፤ ምግብና መጠጥ።

**ዘክዛካ** **"ዘከዘከ"** ስር ተመ.

**ዘወ̈ረ** ግ አዞረ፥ ጠመዘዘ፥ አሽከረከረ።

**መዘወሪያ** ስ ማዞሪያ፥ መጠምዘዣ፥ እጀታ።

**መዘውር** ስ 1. ማሽከርከሪያ፥ ማዞሪያ፥ እጀታ። 2. አንድን ነገር እንዲዞር፥ እንዲሽከረከር የሚያደርግ መካኒካዊ ጉልበት፥ ሃይል። 3. ጠፍር፥ ቋድ (የበቅሎ፥ የፈረስ መሰንከያ)። 4. የመኪና መሪ።

**ዝውውር** **"ዞረ"** ስር ተመ.

**ዘወርዋራ** **"ዞረ"** ስር ተመ.

***ዘወተረ**

**ዘወትር** ተው.ግ. ሁል ጊዜ፥ በየእለቱ፥ በየቀኑ።

**የዘወትር** የሁል ጊዜ። *የዘወትር ልብስ/ የዘወትር ጠባይ።*

**ተዘወተረ** ግ ተደጋገመ፥ የሁልጊዜ ድርጊት ሆነ።

**አዘወተረ** ግ መላልሶ፥ ደጋግሞ፥ ሁልጊዜ አደረገ።

**አዘውታሪ** ቅ አንድን አይነት ድርጊት መላልሶ በየጊዜው የሚፈፅም።

**ዘው**

**ዘው አለ** ግ ጥልቅ፥ ግብት አለ።

**ዘው ዘው አለ** ግ እዚህም እዚያም ገባ፥ ጥልቅ አለ።

**ዘው አደረገ** ግ ጥልቅ አደረገ።

**ዘውድ** ስ ከወርቅ፥ ከእንቁ፥... የሚሰራና ነገስታት እንደአክሊል፥ እንደቆብ በራሳቸው ላይ የሚደፉት የነጋሲነት ማእረግ ምልክት።

**ዘውድ ደፋ** ነገሰ።

**ዘውድ ጫነ** ዝ.ከ.

**የዘውድ ስርአት** ስ በንጉስ የሚመራ ስረአት።



ዘውድ

**የዘውድ አማካሪ** ስ የንጉስ አማካሪ።

**የዘውድ አገዛዝ** ስ በንጉስ የሚመራ ስርአት።

***ዘየመ**

**ዜማ** ስ ቃና፥ ስልትና ተከታታይነት ያለው፥ የተለያዩ የሃዘን ወይም የደስታ ስሜቶችን መግለፅ የሚያስችል ሙዚቃዊ ድምፅ።

**ዜማ ሰበረ** ዜማው ከስንኙ ወይም ከግጥሙ ምጣኔ ጋር አልጣጣም አለ፥ ተበላሸ።

**የዜማ ምልክት** ስ እንደ ጭረት፥ ድፋት፥ ደረት (ˋ ᒥ ᒍ) ያለ፥ አንድ ዜማ በምን አይነትና እንዴት እንደሚዜም የሚመራ፥ የድምፅ አወጣጥን ሁኔታ የሚያሳይ ምልክት።

**የዜማ ቤት** ስ (ቤ.ክህ.) መንፈሳዊ የዜማ ትምህርት የሚሰጥበት ትምህርት ቤት።

**አዜመ** ግ 1. ዜማን አሰማ። 2. ዘፈነ፥ አንጎራጎረ።

**ዘየረ** ግ (እስል.) 1. ሰላም አለ፥ ሰላምታ ሰጠ። 2. በዜማ አወደሰ፥ ምስጋና አቀረበ። 3. ጎበኘ፥ ተሳለመ (ቅዱስ የሆኑ ቦታዎችን)።

**ዝየራ** ስ (እስል.) 1. የእጅ ሰላምታ። 2. በዜማ የሚቀርብ ውዳሴ፥ ምስጋና። 3. ጉብኝት (ቅዱስ የሆኑ ቦታዎችን)።

**ዘየነ** ግ አስጌጠ፥ አሰዋበ፥ ሸለመ፥ አሽቀረቀረ፥ አሳመረ።

**ዝይን** ቅ ሽቅርቅር፥ የተዋበ፥ ያማረ።

**ተዘየነ** ግ አጌጠ፥ አማረ፥ ተሽቀረቀረ፥ ተዋበ።

**ዘየደ** ግ ብልሃት ፈጠረ፥ አበጀ።

**ዘዴ** ስ 1. ብልሃት፥ ጥበብ፥ እውቀት። 2. የአሰራር መንገድ፥ ስልት።

**በዘዴ** ተው.ግ በብልሃት።

**ዘዴኛ** ቅ ብልሃተኛ፥ ጥበበኛ፥ ዘዴ አዋቂ።

**ዘዬ** ስ 1. ፈሊጥ፥ የአሰራር መንገድ። 2.ልማድ። 3. አካባቢያዊ አነጋገር፤ ቀበልኛ።

**ዘይቤ** ስ 1. ውስጠ ምስጢር ያለው አነጋገር። 2. በምሳሌ፥ በንፅፅር፥... አማካይነት ንግግርን በማስዋብ ስሜትን ለመግለፅ የሚያስችል የአነጋገር ስልት።

**በዘይቤ ተናገረ** በቅኔ፥ ሰወር አድርጎ ተናገረ።

**ዘይቤአዊ አነጋገር** ስ በምሳሌ፥ በንፅፅር፥ በሰውኛ፥... አማካይነት ጎልቶ ወይም ተውቦ የሚቀርብ አነጋገር። (ለምሳሌ አንበሳ የሆነ ወንድም አለኝ / እንደ .ርግብ የዋህ ሁን)።

**ዘይቱን** ስ ሲበስል የቆዳው ቀለም ቢጫ፥ ውስጡ ደግሞ ቀይ ወይም ነጭ የሚሆንና በትናንሽ ጠንካራ ፍሬዎች የተሞላ፥ ቆዳው ጭምር የሚበላ ሎሚ የሚያክል ፍሬ የሚያፈራ ተክል፤ ፍሬውም ዘይቱን ይባላል፡፡

**ዘይት** ስ 1. እንደ ኑግ፥ ሰሊጥ፥... ካሉ የቅባት እህሎች ወይም እንደ ጉሎ ካሉ ፍሬዎች ተጨምቆ የሚወጣ ወይም ከሌሎች ነገሮች የሚዘጋጅ ቅባትነት ያለውና ከውሃ ጋር ሊቀላቀል የማይችል፥ ለምግብ ማጣፈጫነት፥ ለቅባትነት የሚያገለግል ፈሳሽ። 2. ከከርሰ ምድር ወጥቶ የሚዘጋጅና በልዩ ልዩ ሜካኒካዊ መሳሪያዎች ውስጥ (ለምሳሌ የመኪና ሞተር፥...) ፍትጊያ እንዳይኖር ለመከላከል፥ ለማለስለስ፥... የሚያገለግል፥ ከውሃ ጋር ለመቀላቀል የማይችል፥ ዝልግልግነት ያለው ፈሳሽ።

**ዘይት ቀለም** ስ ዘይትነት ያለው፥ ስእሎችን ወይም ልዩ ልዩ የቀለም ቅቦችን ለመስራት የሚያገለግል ቀለም።

**ዘዴ** **"ዘየደ"** ስር ተመ.

**ዘዴኛ** ዝ.ከ.

***ዘገመ**

**ዘገምታ** ስ ዝግታ።

**ዘገምተኛ** ቅ ዝግተኛ፥ ቀስ የሚል።

**አዘገመ** ግ በቀስታ፥ በዝግታ ተራመደ፥ ተንቀሳቀሰ።

**አዝጋሚ** ቅ በቀስታ የሚራመድ፥ የሚሄድ።

**አዝጋሚ ለውጥ** ስ በቀላሉ ግልፅ ሆኖ የማይታይ፥ ነገር ግን ቀስ በቀስ የሚካሄድ የመጠን ለውጥ።

**ዘገር** ስ ጦር።

**ዘገበ** ግ 1. አጠናቀረ፥ አዘጋጀ (ወሬን፥ ሪፖርትን፥...)። 2. ፃፈ፥ መዘገበ። 3. ሰበሰበ፥ አከማቸ፥ አጠራቀመ።

**ዘገባ** ስ 1. ስለ አንድ ነገር የተሰጠ ዝርዝር መግለጫ። 2. የዜና ጥንቅር።

**ዘጋቢ** ስ ዜና አዘጋጅ፥ አጠናቃሪ።

**ዘገነ** ግ በእጅ አፈሰ፥ አነሳ፥ ያዘ (እንደ ጥራጥሬ፥... ያሉትን)።

**ዝግን** ስ 1. ተቀቅሎ ከተመተረ በኋላ ለብቻው ከተሰራ ሽሮ ወጥ ጋር ወይም ብቻውን ሊበላ የሚችል ስጋ። 2. የስጋ ጥብስ ወጥ። 3. ዝግኝ።

**ዝግኝ (ዝግን)** ቅ በአንድ እጅ ብቻ የታፈሰ፥ የተዘገነ (የጥራጥሬ ወይም የሌላ ነገር መጠን)።

**ተዘገነ** ግ በዝግኝ ተነሳ፥ ታፈሰ፥ ተወሰደ (ጥራጥሬ፥ ውሃ፥...)።

**ዘገነነ** ግ ሰቀጠጠ ወይም የሚያስፈራ፥ የሚያስደነግጥ ስሜት ፈጠረ።

**ዘግናኝ** ቅ ሰቅጣጭ፥ አስደንጋጭ፥ አሳዛኝ፥ *የመኪናው አደጋ እጅግ ዘግናኝ ነበር።*

**ዘገየ** ግ ቆየ፤ ወደኋላ ቀረ፥ ቀስ አለ።

**አዘገየ** ግ አቆየ፤ ወደ ኋላ አስቀረ።

***ዘገጀ**

**ዝግጁ** ቅ የተዘጋጀ፥ ስንዱ።

**ዝግጅት** ስ 1. መሰናዶ። 2. የተጠናቀቀ ወይም የሚጠናቀቅ የስራ ክንውን። 3. አንድን ፅሁፍ፥ ፊልም፥ ትያትር፥... ለተደራስያን በሚቀርብ መልክ የማዘጋጀት ተግባር።

**ተዘጋጀ** ግ 1. ተሰናዳ። 2. ተከናወነ፥ ተቀናበረ። 3. ተሰርቶ አለቀ፥ ቀረበ።

**ተዘገጃጀ** ግ ተሰናዳ።

**አዘጋጀ** ግ 1. አሰናዳ። 2. አከናወነ። 3. ሰርቶ፥ ፅፎ አወጣ፥ አቀረበ።

**ማዘጋጃ ቤት** ስ የከተማን አስተዳደር በተመለከተ የተለያዩ ስራዎችን የሚሰራ መስሪያ ቤት።

**አዘጋጅ** ስ 1. የትያትርን፥ የፊልምን ዝግጅት የሚሰራ (ሰው)። 2. መፅሄትን፥ ጋዜጣን ወይም መፅሃፍን አጠናቅሮ የሚያወጣ ግለሰብ ወይም ድርጅት። 3. አንድ አይነት ፕሮግራም፥ ሴሚናር፥ ስብሰባ፥ እንዲካሄድ የሚያደርግ፥ የሚያቀነባብር ግለሰብ ወይም ድርጅት።

**ዘገጠ** ግ ዘቀጠ፥ ሰረገ፥ ሰጠመ።

**አዘገጠ** ግ 1. አዘቀጠ፥ አሰረገ፥ አሰጠመ። 2. ዘገጠ።

**ዘጊ**[1] **"ዘጋ"** ስር ተመ.

**ዘጊ**[2] **"*ዘጋ"** ስር ተመ.

**ዘጋ** ግ 1. ገጠመ፥ ከደነ፥ ደፈነ (በርን፥ መፅሃፍን፥ ...)። 2. እንዲያቆም፥ እንዲያቋርጥ አደረገ። *ሬዲዮኑን ዘጋ/ቧንቧውን ዘጋ።* 3. አገደ፥ ከለከለ (መተላለፊያን፥...)። 4. ከሰው ተለይቶና ቤት ዘግቶ ሱባኤ ያዘ፥ ለብቻው ተቀመጠ (ባህታዊ)። 5. የምግብ ፍላጎት አሳጣ፥ ምግብ ከለከለ፥ አስጠላ። 6. አጠቃለለ፥ ደመደመ፥ ጨረሰ። 7. አንቆ ያዘ፥ አላናግር አለ። *ጉንፋን ድምፁን ዘጋው።* 8. (የአራዳ አነ.) ዝም አለ፥ አኮረፈ። 9.(የአራዳ አነ.) አስጠሊታ፥ አስቀያሚ ሆነ።

**መዝጊያ** ስ 1. የበር ግጣም፥ ሳንቃ። 2. መከደኛ። 3. ሬዲዮ፥ ቧንቧ ወይም ሌላ ነገር በማያስፈልግበት ጊዜ እንዳይሰራ ማቆሚያ። 4. መደምደሚያ፥ ማጠቃለያ (የፅሁፍ፥ የሃሳብ፥ የስብሰባ፥...)።

**ዘጊ** ቅ (ተራ አነ.) ደስ የማይል፥ አስቀያሚ፥ አስጠሊታ።

**ዝግ** ቅ 1 የተከደነ፥ የተደፈነ፥ የተቆለፈ። 2 የተከለከለ፥ የታገደ (መንገድ)። 3 ስራ ያቆመ። 4 (ዘይ.) የማይናገር፥ ሁሉንም ነገር በሆዱ አምቆ የሚይዝ።

**ዝግ ስብሰባ** ስ ከተፈቀደላቸው የተወሰኑ ሰዎች በስተቀር ሌላ ሳይገባበት የሚካሄድ ስብሰባ።

**ዝግ ችሎት** ስ ለአደባባይ÷ ለህዝብ ክፍት ሳይሆን የሚመለከታቸው ሰዎች ብቻ ባሉበት የሚካሄድ ችሎት÷ ዳኝነት።

**ተዘጋ** ግ 1. ተደፈነ። 2. ታገደ÷ ተከለከለ፤ የማያሳልፍ ሆነ። *መንገድ ተዘጋ።* 3. ዝም አለ። 4. ስራ አቆመ (ት/ቤት÷ ፋብሪካ÷...)።

***ዘጋ**

**ዘጊ** ቅ የሚያደራ (ድርን)።*እንደ ዝሃ ዘጊ ምን ያመላልሰሻል።*

**አዘጋ** ግ ድር ወይም ዝሃ አደራ÷ ዘረጋ።

**አዝጊ** ቅ አድሪ÷ ድርን የሚያደራ።

**ዘጋቢ** **"ዘገበ"** ስር ተመ.

**ዘግናኝ** **"ዘገነነ"** ስር ተመ.

***ዘጎረጎረ**

**ዝጉርጉር (ዥጉርጉር)** ቅ ጠቃጠቆ (የነጥና ጥቁር ወይም የተለያዩ ቀለማት ስብጥር)።

**ተዝጎረጎረ (ተዥጎረጎረ)** ግ የተለያዩ ቀለማት ስብጥር ወይም ቡራቡሬ ሆነ።

**አዝጎረጎረ(አዥጎረጎረ)** ግ የተለያዩ ቀለማት ስብጥር ወይም ቡራቡሬ አደረገ።

**ዘጠረ** ግ 1. በብዛት ጨመረ÷ ሞጀረ። 2. ገጠገጠ÷ ተከለ (ድንኳንን)። 3. ነፋ÷ ወጠረ (ሆድን)።

**ዝጥር** ቅ ውጥር÷ የተወጠረ።

**ተዘጠረ** ግ 1. በብዛት ተጨመረ÷ ተሞጀረ። 2. ተገጠገጠ÷ በብዛት ተተከለ (ድንኳን)። 3 ተነፋ÷ ተወጠረ÷ አበጠ።

**ዘጠና** ስ 1. በሰማንያ ዘጠኝና በዘጠና አንድ መካከል ያለ ቁጥር መጠሪያ፤ በአሃዝ ሲፃፍ÷ '90'ነው። ቅ 2. ብዛቱ÷ መጠኑ ዘጠኝ ጊዜ አስር ያህል የሆነ። *ዘጠና ብር።*

**ዘጠኝ** ስ 1. በስምንትና በአስር መካከል ያለ ቁጥር መጠሪያ፤ በአሃዝ ሲፃፍ '9' ነው። ቅ 2.መጠኑ ወይም ብዛቱ በስምንትና በአስር መካከል የሆነ። *ዘጠኝ መፅሃፎች።*

***ዘጠዘጠ**

**ዘጠዘጥ (ዘጥዛጣ)** ቅ (ስድብ) አፋዳሽ÷ አውደልዳይ፤ ያለ ስራ ከወዲያ ወዲህ እያለ የሚያረጠርጥ።

**ዘጥ ዘጥ(ዘጭ ዘጭ) አለ** ግ 1. አዘጠዘጠ÷ አረጠረጠ። 2. ሩጫ አይሉት ርመጃ አይነት አካሄድ ሄዶ (ብዙውን ጊዜ ወፍራም ሰው)።

**አዘጠዘጠ** ግ አውደለደለ÷ አፋደሰ።

**አዘጥዛጭ** ቅ ስራ የማይሰራ÷ አውደልዳይ፤ አረጥራጭ።

**ዘጥ**

**ዘጥ አለ (ዘጭ አለ)** ግ ዱብ አለ÷ ወደቀ።

**ዘጥዛጣ** **"*ዘጠዘጠ"** ስር **"ዘጠዘጥ"**ን ተመ.

**ዘጭ አለ** **"ዘጥ"** ስር ተመ.

**ዘፈር** ስ ዘርፍ።

**ዘፈቀ** ግ 1. ደፈቀ÷ ነከረ÷ አስገባ÷ አሰመጠ÷ ከተተ (ውሃ ውስጥ)። 2. (ዘይ.) ከተተ÷ አስገባ (እዳ÷ መከራ÷... ውስጥ)።

**ዝፍቅ** ቅ (ስድብ) ሞኝ÷ ቂል።

**ተዘፈቀ** ግ 1. ተነከረ÷ ገባ÷ ሰጠመ (ውሃ ውስጥ)። 2. ገባ (እዳ÷ መከራ÷... ውስጥ)።

**ዘፈነ** ግ 1. አዜመ÷ አንጎራጎረ (ዘፈንን)። 2. ዘፈንን÷ ዜማን አሰማ (ሬዲዮ÷ ቴፕ)። 3. ተንቀጠቀጠ÷ ተንዘፈዘፈ (ሰውነት)።

**ዘፈነብኝ** ተረገረገብኝ÷ የስድብና የቁጣ ንግግር ተናገረኝ።

**ዘፈን** ስ ዜማ÷ እንጉርጉሮ (አለማዊ የሆነ)።

**ዘፈን አወረደ** ዘፈኑን በዜማ÷ በእንጉርጉሮ መራ÷ አቀነቀነ።

**ዘፈን አወጣ** አዳዲስ ዘፈኖችን አቀረበ÷ ደረሰ÷ ለህዝብ አሰማ።

**ዘፋኝ** ቅ ድምፃዊ ተጫዋች÷ አንጎራጓሪ።

**አስዘፈነ** ግ ሰውን÷ ሬዲዮን ወይም ቴፕን÷ እንዲዘፍን÷ ዘፈን እንዲያሰማ አደረገ።

**ዘፈዘፈ** ግ 1. እንዲርስ ውሃ ውስጥ ለብዙ ሰአት አቆየ÷ ነከረ÷ ዘፈቀ (ጥራጥሬን÷ ልብስን÷ ...)። 2. ከመረ÷ ቆለለ። 3. በብዛት ቆረጠ÷ ረፈረፈ÷ ለሸለሸ (ዛፍን)።

**ዘፋዘፎ** ቅ ረዥምና ወፍራም÷ ሰውነተ ከባዳ የሆነ÷ ቅርዕቢስ።

**ዘፍዛፋ** ዝ.ከ.

**ዝፍዝፍ** ቅ 1. እንዲርስ የተነከረ። 2. (ስድብ) ረሀጥ÷ ከተቀመጠበት የማይነሳ÷ ሰነፍ።

**ተዘፈዘፈ** ግ 1. ውሃ ውስጥ ተነከረ (እንዲርስ)። 2. ስራ ሳይሰራ ተቀምጦ ዋለ፤ ተረፈቀ÷ ሰነፈ።

***ዘፈዘፈ**

**ተንዘፈዘፈ** ግ ተንቀጠቀጠ።

**አንዘፈዘፈ** ግ አንቀጠቀጠ።

***ዘፈጠጠ**

**ዘፍጣጣ (ዝፍጥጥ)** ቅ ሆደ ዘርጣጣ÷ ጎፍጣጣ።

**ዝፍጥጥ አለ** ግ ተንዘፈጠጠ።

**ተንዘፈጠጠ** ግ ተንዘረጠጠ፥ ተንገፈጠጠ (ሆድ፥...)።

**አንዘፈጠጠ** ግ አንዘረጠጠ፥ አንገፈጠጠ፥ (ሆድን፥ ...)።

**ዘፈፈ** ግ ተንዛፈፈ።

**ዘፋፋ** ቅ 1. ትልቅነትና ስፋት ያለው (የዛፍ ቅርንጫፍ)። 2. እርዝማኔና ከባድነት ያለው (አካላዊ አቋም)። 3. ዘርፋፋ፥ ሰፊና ረጅም (ልብስ)።

**ተንዛፈፈ** ግ 1. ሰፋ፥ ተንሰራፋ፥ ተዘረጋ (የዛፍ ቅርንጫፍ)። 2. ተንዘረፈፈ፥ ረዘመ (ልብስ)።

**ዘፋኝ** "ዘፈነ" ስር ተመ.

**ዘፋዘፎ** "ዘፈዘፈ" ስር ተመ.

**ዘፋፋ** "ዘፈፈ" ስር ተመ.

**ዘፍ**

**ዘፍ አለ** ግ በቁመቱ ሙሉ ወደቀ፥ ተጋደመ።

**ዘፍ አደረገ** ግ በቁመቱ ሙሉ እንዲወድቅ አደረገ፥ ጣለ።

**ዘፍዛፋ** "ዘፈዘፈ" ስር ተመ.

**ዘፍጣጣ** "*ዘፈጠጠ" ስር ተመ.

**ዙ** የ"ዘ" ፊደል ካእብ ዘር።

**ዙረት** "ዞረ" ስር ተመ.

**ዙሪያ** ዝ.ከ.

**ዙር** ዝ.ከ.

**ዙርያ** "ዞረ" ስር "ዙሪያ"ን ተመ.

**ዙሮሽ** ዝ.ከ.

**ዙጣ** ቅ ወፈር ያለ፥ አጭር (ሰው)።

**ዙጥ**

**ዙጥ አደረገ** ግ ፈሳ።

**ዙፋን** ስ 1. የንጉስ መንበር፥ አልጋ። 2. ንጉስ የሚቀመጥበት የተጌጠ ትልቅ ወንበር።

**ዙፋን ቤት** ስ የንጉስ ዙፋን የሚቀመጥበት ቤት።

**ዙፋን ችሎት** ስ ንጉስ በዳኝነት የሚቀመጥበት ችሎት።

**ዚ** የ"ዘ" ፊደል ሳልስ ዘር።

**ዚቅ** ስ 1. (ኢ.ኦ.ተ.ቤ.) በማህሌት ጊዜ ከመልክ መረግድ ቀጥሎ በፀናፅልና በከበሮ እየታጀበ የሚባል ዜማ። 2. የዜማ መፅሃፍ ስም።

**ዚቅ አወረደ** በከበሮና በፀናፅል እየታጀበ አዜመ (ዚቅን)።

**ዚቀኛ** ቅ ተረበኛ፥ ተረብ አዋቂ።

**ዚፕ** ስ ብዙውን ጊዜ እንደሱሪ፥ ጃኬት ያሉ ልብሶችን ለመቆለፍ ወይም እንደሻንጣ፥ ቦርሳ የመሳሰሉትን ለመዝጋት የሚያገለግል ተወሳሳቢ ወይም እርስ በርሱ የሚሰካካ ጥርስ ያለው መቆለፊያ፤ ቻርኔላም ይባላል።

**ዛ** የ"ዘ" ፊደል ራብእ ዘር።

**ዛህርት** ስ ትልቅ ሆድ።

**ዛህርታም** ቅ ሆዳም።

**ዛለ** ግ ደከመ፥ አቅም አጣ፥ ተልፈሰፈሰ።

**ዝለት** ስ ድካም፥ አቅም ማጣት።

**አዛለ** ግ አደከመ፥ አቅም አሳጣ፥ አልፈሰፈሰ።

**ዛላ** ስ 1. ፍሬ ያዘለ የስንዴ፥ የገብስ፥ ... ራስ፤ እልፍ። 2. የሰውነት አቋም፤ ቁመና።

**ዛላ በርበሬ** ስ የበሰለ ወይም የቀላ ቃሪያ።

**ዛራም** "ዛር" ስር ተመ.

**ዛሬ** ስ 1. በትናንትናና በነገ መሃል ያለ ጊዜ፥ ያለንበት ቀን። 2. የአሁኑ ዘመን። *በዛሬው ጊዜ እህል ተወደደ።*

**ዛሬ ነገ አለ** አመነታ፤ ቀጠሮ አበዛ፥ በተፈለገው ጊዜ፥ ቀን፥... ሳያደርግ፥ ሳይፈፅም ቀረ (ጉዳዩን፥...)።

**ዛር** ስ ውቃቢ፥ የሚያስጓራ ክፉ መንፈስ።

**ዛር አንጋሽ** ቅ ጠንቋይ፥ ቃልቻ፤ የዛር ባለሟል፥ ዛር አነጋጋሪ ነኝ የሚል።

**የዛር ውላጅ** ስ ዛር የወለደው፥ ስጋ የለበሰ ጋኔን ነው ተብሎ የሚታመን (ርኩስ መንፈስ)።

**የዛር ፈረስ** ቅ ዛር የያዘው (ሰው)።

**ዛራም** ቅ 1. ዛር ያለበት። 2. ክልፍልፍ፥ ቀዥቃዣ። 3. ቁጡ፥ ነጭናጫ።

**ዛቀ** ግ 1. አፈሰ፥ በብዛት ወሰደ። 2. ቧጠጠ፥ ሿጠጠ፥ ጠረገ። 3. ደነቆለ፥ ጠነቆለ (አይንን)።

**መዛቂያ** ስ እንደ አካፋ፥ ማንኪያ ያለ ማፈሻ፥ ማንሻ እቃ ።

**ዝቆሽ ነው** በትንሽ ዋጋ የተገዛው ነገር በጣም ብዙ ነው።

**ተዛቀ** ግ 1.ታፈሰ፥ በብዛት ተወሰደ። 2. ተሿጠጠ፥ ተጠረገ። 3. በርካሽ ተገኘ።

**ዛቀጠ** ግ ለፋ፥ ማሰነ።

**ዛቆነ**[1] ግ ዲያቆን ሆነ፥ ዳቆነ።

**አዛቆነ** ግ ዲያቆን አደረገ፤ አዳቆነ።

**ዛቆነ**[2] ግ ለፋ፥ ደከመ።

**አዛቆነ** ግ አለፋ፥ አደከመ።

**ዛበረ** ግ 1. ለፋ፥ ባከነ። 2. ቃዠ፥ ለፈለፈ።

**ዛባሪ** ቅ ለፍላፊ፥ ቀላማጅ።

**አዛበረ** ግ 1. አለፋ፥ አደከመ። 2. አቃዠ፥

አስለፈለፈ::

**ዛቢያ** ስ 1. የመጥረቢያ፥ የዶማ፥... እጀታ:: 2. መሬትን መሃል ለመሃል ሰንጥቆ የሚያልፍና መሬት የምትሽከረከርበት የሃሳብ መስመር::

**ዛቢያ ገንጥል** ጉልበታም፥ ፈርጣማ ጡንቻ ያለው (ሰው)::

**ዛባሬ** "**ዛበረ**" ስር ተመ.

**ዛብ** ስ የበቅሎ ወይም የፈረስ ልጓም ቋድ፥ ጠፍር::

**ዛተ** ግ አስፈራራ፥ ጉዳት እንደሚያደርስ ተናገረ፤ ፎከረ::

**ዛቻ** ስ የማስፈራራት ንግግር፤ ፉከራ::

**ዛቲ** ስ በቤተክርስቲያን ለሰዎች የሚታደል ከየቤቱ የመጣ የዳቦ፥ የአነባበሮ፥ የእንጀራ ቁራሽ፥...፤ ጣዲቅ::

**ዛቻ** "**ዛተ**" ስር ተመ.

**ዛኒጋባ** ስ ጣሪያው ባለ አንድ አቅጣጫ ወይም ተፉሰስ የሆነ አነስተኛ ቤት::

**ዛንታ** ስ ወግ፥ ታሪክ::

**ዛዛቲያም** "***ዛዛ**" ስር ተመ.

**ዛዛቴ** ዝ.ክ.

**ዛዘለ** ግ ረዘመ፥ ተጎተተ፥ተግዠለገዠለ::

**ዛዘነ** ግ 1 ዞረ፥ ባዘነ፥ናበዘ:: 2 ሻፈደ፥ ፈለገ(ዝሙት)::

**ዛዛኝ** ቅ ሻፋዳ::

### *ዛዛ

**ዛዛቴ** ስ የተንዛዛ፥ ከልክ ያለፈ ወሬ፥ ነገር::

**ዛዛቴያም** ቅ ነገር ቶሎ የማይቆርጥ፥ ወሬኛ::

**ተንዛዛ** ግ ከመጠን አለፈ ፥ በጣም በዛ::

**አንዛዛ** ግ ከመጠን አሳለፈ፥በጣም አበዛ::

**ዛዛኝ** "**ዛዘነ**" ስር ተመ.

**ዛገ** ግ አፈር ላይ በመውደቁ ወይም እርጥበት በማግኘቱ፥ ሳይሰራበት በመቆየቱ፥... መልኩ ተቀየረ፥ ተበላሸ፥ አፈር መሰለ(ብረት)::

**ዝገት** ስ አፈር ላይ ከመውደቅ፥ እርጥበት ላይ ከመቆየት፥... የተነሳ ብረታ ብረት በሆኑ ነገሮች ላይ የሚደርስ አፈር የመምሰልና የመበላሸት ሁኔታ::

**አዛገ** ግ አበላሸ፥ ዝገት እንዲይዝ አደረገ(ብረታ ብረትን)::

**ዛጎለ** ግ ዛጎል መሰለ፥ እንደመንጣት አለ::

**ዛጎል** ስ በባህር ውስጥ የሚኖሩ አንዳንድ ነፍሳት በህይወት እያሉ ለሰውነታቸው ጠንካራ ልባስ ሆኗቸው የሚኖርና ከሞቱ በሂላ እንደ ጌጥ የሚያገለግል ጠጣር አካል::

**ዛጎል ጣለ** ዛጎል መሬት ላይ በመጣል ጠነቆለ::

**ዛጎል ጣይ** ስ ዛጎል በመበተን የሚጠነቁል ጠንቋይ፤ ሟርተኛ::

**ዛጎል በርበሬ** ስ ቀይ ጣላ በርበሬ፥ በቀይ ቀለሙ ላይ ነጭ የጣለበትና ጥራቱ ዝቅተኛ የሆነ በርበሬ::

**ዛጎልማ** ቅ መልኩ፥ ቀለሙ ዛጎል የሚመስል::

**ዛፍ** ስ 1. ግንድና ቅርንጫፎች ያሉት፥ መጠኑ ትልቅና ትንሽ የሆነ፥ ለረጅም ጊዜ ሊቆይ የሚችል የእፅዋት አይነት:: 2. (ዘይ.) ረጅም (ለሰው)::




*ዛፍ 1ኛ ፍቺ*

**ዛፍ ቆራጭ** ስ ስራው ዛፍ መቁረጥና መፍለጥ የሆነ ሙያተኛ ::

**ዜ** የ "**ዘ**" ፊደል ሃምስ ዘር ::

**ዜማ** "***ዘየመ**" ስር ተመ.

**ዜሮ** ስ ባዶ፥ ምንም፤ በአሃዝ ሲፃፍ "0" ነው:: *ተወዳዳሪዎቹ ያለ ውጤት ዜሮ ለዜሮ ተለያዩ::*

**ዜሮ ሻማ** ስ እጅግ በጣም አነስተኛ የሆነ ብርሃን ያለው የኮረንቲ አምፑል::

**ዜና** ስ ወሬ::

**ዜና መዋእል** ስ የቀድሞ ነገስታት የእለት ወይም የጦርነት ውሎአቸው ተመዝግቦ የሚገኝበት መፅሃፍ::

**ዜና ማሰራጫ** ስ እንደሬዲዮ፥ ቴሌቪዥን፥ ጋዜጣ ያለ ዜና ማስተላለፊያ::

**ዜና እረፍት** ስ የአንድ ሰው የመሞቱ ወሬ::

**ዜጋ** ስ በአንድ ሃገር ውስጥ በመወለዱ ወይም ፈቃድ በማግኘቱ የተወላጅነት መብት ያለው ሰው::

**ዜግነት** ስ በአንድ አገር ውስጥ በተወላጅነት ወይም በፈቃድ የሚገኝና ሰውዬው የዚያ አገር ሰው የመሆኑ መገለጫ::

**ዝ** የ "**ዘ**" ፊደል ሳድስ ዘር::

**ዝሃ(ዘሃ)** ስ ድር::

**ዝሃ አዘጋ** ድር አደራ::

**ዝሃ በዝሃ** ድር በድር፥ ማጉም ድር የሆነ (ልብስ)::

**ዝሆኔ** ስ እግር የሚያሳብጥ በሽታ፤ ኮብሽ።

**ዝሆን (ዘሆን)** ስ በጣም ትላልቅ የሆኑና ከከንፈሩ ወደ ውጪ የወጡ ሁለት ጥርሶች፥ ሰፋፊ ጆሮዎችና አንድ ኩምቢ ያለው፥ ምግቡ በአብዛኛው ሳርና ቅጠላቅጠል የሆነ ግዙፍ እንስሳ (ስእሉን የዱር እንስሳ ስር ተመ.)።።

**የዝሆን ጥርስ** ስ በላይ በኩል ከከንፈሩ ውጪ የሚታይና 5 ሜትር ያህል ርዝማኔ ያለው፥ ብዙውን ጊዜ በጌጥነት የሚያገለግል፥ ነጭ ሆኖ ወፍራምና ረጅም ቀንድ የሚመስል የዝሆን የውሻ ክራንቻ።

**ዝለቅ** "ዘለቀ" ስር ተመ.

**ዝለት** "ዛለ" ስር ተመ.

**ዝላይ** "ዘለለ[1]" ስር ተመ.

**ዝልል** "ዘለለ[2]" ስር ተመ.

**ዝልንግድ** ቅ 1. ረዥም፥ ቀውላላ። 2. የማይረባ፥ ሰነፍ ።

**ዝልዝል** "ዘለዘለ" ስር ተመ.

**ዝልጉስ** "ዘለጎሰ" ስር ተመ.

**ዝልጊት** ስ የጠላ፥ የጠጅ ማጥለያ ወንፊት፤ ወንጠፍት።

**ዝልግልግ** "*ዘለገለገ" ስር ተመ.

**ዝልፊያ** "ዘለፈ[1]" ስር ተመ.

**ዝልፍልፍ** "*ዘለፈለፈ" ስር ተመ.

**ዝሙተኛ** "ዘሞተ" ስር ተመ.

**ዝሙት** ዝ.ከ.

**ዝማሜ** "ዘመመ[1]" ስር ተመ.

**ዝማም[1]** ስ እንዳይበላ ወይም እንዳይጠጣ በከብት አፍ ላይ የሚጠለቅ ቅርጫት መሰል መሸበቢያ፥ ልጓም።

**ዝማም[2]** ቅ ያማረ፥ የተዋበ፥ የተወለወለ።

**ዝማም ወርቅ** ስ 1. በተደጋጋሚ የተነጠረ ወርቅ። 2. በጆሮ ወይም በአፍንጫ ላይ የሚንጠለጠል ወርቅ።

**ዝማሬ** "ዘመረ" ስር ተመ.

**ዝም**

**_ብሎ ዝም ነው** ጥሩ፥ የሚደነቅ፥... ነው። *መፅሃፍ ብሎ ዝም ነው።*

**ዝምታ** ስ 1. አለመናገር። 2. ፀጥታ።

**ዝምተኛ** ቅ ብዙ የማይናገር፤ ጭምት።

**ዝም አለ** ግ 1. ሳይናገር ቀረ፥ ጭጭ አለ። 2. መልስ ሳይሰጥ ቀረ። 3. ምንም አይነት ርምጃ፥ እንቅስቃሴ ሳያደርግ ቀረ፥ ተወ።

**ዝም ብሎ** 1. ያለምክንያት። *ዝም ብሎ ቆጣው።* 2 ባለማቋረጥ። *ዝም ብሎ ይፈሳል።* 3. ምንም ሳይናገር፥ ሳያደርግ፥...። *ዝም ብሎ ሄደ።*

**ዝም አሰኘ** ግ ዝም እንዲል፥ እንዳይናገር፥ ድምፅ እንዳያሰማ አደረገ፥ ፀጥ አደረገ።

**ዝምባም** "ዝንብ" ስር ተመ.

**ዝምብ** ዝ.ከ.

**ዝምተኛ** "ዝም" ስር ተመ.

**ዝምታ** ዝ.ከ.

**ዝምዝማት** "ዘመዘመ" ስር ተመ.

**ዝምዝም** "ዘመዘመ" ስር "ዝምዝማት"ን ተመ.

**ዝምድና** "*ዘመደ" ስር ተመ.

**ዝሪት** "ዘራ" ስር ተመ.

**ዝራንጭ** ስ የቁንጮ አይነት።

**ዝር** "ዘራ" ስር ተመ.

**ዝርክራኪ** "*ዘረከረከ" ስር ተመ.

**ዝርክርክ** ዝ.ከ.

**ዝርዝር** "ዘረዘረ" ስር ተመ.

**ዝርያ** "ዘራ" ስር ተመ.

**ዝርግ** "ዘረጋ" ስር ተመ.

**ዝርግፍ** "ዘረገፈ" ስር ተመ.

**ዝርጥርጥ** "*ዘረጠ" ስር "ዘረጥራጣ"ን ተመ.

**ዝርጥጥ** "ዘረጠጠ" ስር ተመ.

**ዝርፊያ** "ዘረፈ[1]" ስር ተመ.

**ዝርፍጥ** "*ዘረፈጠ" ስር ተመ.

**ዝቃቅቤ** "ዘቃቅቤ" ን ተመ.

**ዝቃጫም** "ዘቀጠ" ስር ተመ.

**ዝቃጭ** ዝ.ከ.

**ዝቅ**

**ዝቅታ** ስ ታችኛ ቦታ፤ የከፍታ ተቃራኒ።

**ዝቀተኛ** ቅ 1. አነስተኛ። *ዝቅተኛ ደመወዝ ያላቸው።* 2. ጎድጓዳ፥ ረባዳ፥ ዘባጣ (ቦታ)። 3. የበታች።

**ዝቅ አለ** ግ 1. ወደ ታች ወረደ። 2. አነሰ።

**ዝቅ አደረገ** ግ 1. ወደ ታች አወረደ። 2. አሳነሰ ።3. ከደረጃ፥ ከማእረግ አወረደ።

**ዝቅ አድርጎ ተመለከተ** በማኮሰስ፥ በንቀት ተመለከተ ።

**ዝቅዝቅ** "ዘቀዘቀ" ስር ተመ.

**ዝቅጥቃጭ** "ዘቀጠ" ስር ተመ.

**ዝቡጥቡጥ** "*ዘቦጠቦጠ" ስር ተመ.

**ዝባዝንኬ** ስ 1. ዝግንትል፥ ኮተት። ቅ 2. የማይረባ (ለነገር)።

**ዝባዝንኪያም** ቅ ዝግንትላም፥ ኮተታም ።

**ዝባድ** ስ ጥርኝ ከሚባል አውሬ የሚገኝና ሽቶ ለመስራት የሚያገለግል እንደ ጆሮ ኩክ ያለ የወዝ ወይም የላበት ግግር።

**ዝብርቅርቅ "ዘባረቀ"** ስር ተመ.

**ዝብብት "ዘበተ"** ስር ተመ.

**ዝብድይ** ስ እግራም ጣባ፥ ወጭት።

**ዝተት** ስ 1. ከበግ ፀጉር የሚሰራ (እንደባና፥ ማቅ፥...ያለ) የብርድ ልብስ አይነት። ቅ 2. (ስድብ) የማይረባ፥ ቅልጥፍና የሌለው። 3. የተቀዳደደ፥ የተጣጣፈ አሮጌ ልብስ፤ ቡትቶ።

**ዝተታም** ቅ (ስድብ) ዝተት ወይም አሮጌና የተቀደደ ልብስ የሚለብስ፤ ቅርንጥሳም።

**ዝነኛ "ዝና"** ስር ተመ.

**ዝና** ስ 1. ታዋቂነት። 2. ታሪክ። *ትልቅ ዝና ያለው ሰው ነው።* 3. ወሬ። *በዝና አውቀዋለሁ* ።

**ዝነኛ** ቅ ታዋቂ፥ ስመጥር ።

**ዝናር** ስ ዙሪያውን የጥይት መያገርያዎች ያሉት፡ ብዙውን ጊዜ ወታደሮች ወገባቸው ላይ የሚታጠቁት ሰፌ ቀበቶ።

**ዝናም "ዘነበ"** ስር "ዝናብ"ን ተመ.

**ዝናባማ "ዘነበ"** ስር ተመ.

**ዝናብ** ዝ.ከ.

**ዝንቅ "ዘነቀ"** ስር ተመ.

**ዝንባሌ "ዘነበለ"** ስር ተመ.

**ዝንባም "ዝንብ"** ስር ተመ.



**ዝንብ(ዝምብ)** ስ ከንብ አነስ የምትልና ቆሻሻ ባለበት አካባቢ የምትገኝ በራሪ ነፍሳት።

**ዝንበ በል** ስ መጠኑ የመስቀል ወፍ የሚያህል፥ ዝንብ ጭራው ረዥም፥ ጭንቅላቱ ጥቁር ሰማያዊ የሆነና ቁንጮ ያለው፥ በወንዝ አካባቢ የሚኖርና ነፍሳትን የሚመገብ ወፍ።

**ዝንበ ከልክል** ስ ሌማት፤ የመሶብ አይነት።

**ዝንባም(ዝምባም)** ቅ 1. (ስድብ) ንፅህና የሌለው፥ ቆሻሻ። 2. ፈዛዛ፥ ገልጃጃ።

**ዝንተ አለም** ተው.ግ. ዘለአለም፥ ሁልጊዜ።

**ዝንኪላ** ስ ፍሬው ለማቅለሚያነት የሚያገለግል ደም የሚመስል ቀለም ያለው እሾሃማ የእፀዋት አይነት ።

**ዝንዘና "ዘነዘነ"** ስር ተመ.

**ዝንጀሮ(ጅንጀሮ)** ስ 1. ከትከሻው ከፍ ከወደ ዳሌው አጠር የሚል፥ በአንገቱና በትከሻው አካባቢ ያለው ፀጉር ጎፈርማ የሆነ፥ ፊቱና መቀመጫው ላይ ፀጉር የሌለው፥ በቆላም በደጋም መኖር የሚችል የዱር አውሬ (ስእሉን የዱር እንስሳ ስር ተመ.)። 2. (ስድብ፥ ዘይ.) መልከ ጥፉ።

**ዝንጅብል(ጅንጅብል)** ስ እንደ ድንች በመሬት ውስጥ የሚንሰራፉ፥ ስሩ በቅመምነት የሚያገለግል ተክል፤ ከስሩ የሚገኘውና በቅመምነት የሚያገለግለው ክፍልም ዝንጅብል ይባላል።

**ዝንጉ "ዘነጋ"** ስር ተመ.

**ዝጉርጉር "*ዘጎረጎረ"** ስር ተመ.

**ዝንጋታ "ዘነጋ"** ስር ተመ.

**ዝንጣይ "ዘነጠለ"** ስር ተመ.

**ዝንጣፊ "ዘነጠፈ"** ስር ተመ.

**ዝንጥል "ዘነጠለ"** ስር ተመ.

**ዝክር "ዘከረ"** ስር ተመ.

**ዝክዝክ "ዘከዘከ"** ስር ተመ.

**ዝውውር "ዘወረ"** ስር ተመ.

**ዝየራ "ዘየረ"** ስር ተመ.

**ዝይ** ስ ዳክዬ የሚመስል፥ ዝንጉርጉር ግራጫ ቀለም ያለው፡ አፉ ከዳክዬ አፍ ጠበብ የሚል፡ በወንዝና በባህር አካባቢ የሚኖር የአሞራ አይነት(ስእሉን አሞራ ስር ተመ.)።

**ዝይን "ዘየነ"** ስር ተመ.

**ዝጎት "ዛገ"** ስር ተመ.

**ዝግ**

**ዝግታ** ስ ቀስታ፡ ፍጥነት የሌለው ሁኔታ።

**ዝግተኛ** ቅ ቀስተኛ፡ የማይቸኩል፡ ረጋ ያለ።

**ዝግ አለ** ግ ቀስ አለ፡ ፍጥነት ቀነሰ ።

**ዝግ አደረገ** ግ ቀስ አደረገ፡ ፍጥነቱን ቀነሰ ።

**ዝግ "ዘጋ"** ስር ተመ.

**ዝግባ** ስ በደጋ ወይም በወይና ደጋ የሚበቅል፥ ሁልጊዜ ልምላሜ የማይለየው፡ በጣም ወፍራም የሆነና ቀጥ ብሎ የሚወጣ ረዥም ግንድ ያለው ዛፍ።

**ዝግባ ያህላል** በጣም ግዙፍ ነው (ለሰው)።

**ዝግታ "ዝግ"** ስር ተመ.

**ዝግን "ዘገነ"** ስር ተመ.

**ዝግንትል** ስ የማይረባ፡ ኮተት።

**ዝግንትላም** ቅ ኮተታም።

**ዝግኝ "ዘገነ"** ስር ተመ.

**ዝግጁ "*ዘገጀ"** ስር ተመ.

**ዝግጅት** ዝ.ከ.

**ዝጥር "ዘጠረ"** ስር ተመ.

**ዝፍቅ** “ዘፈቀ” ስር ተመ.

**ዝፍት**[1] ስ ከእንጨት የሚገኝ ቅጥራን፣ መጣብቅ የሚሆን ሙጫ ::

**ዝፍት**[2] ስ 1. አተላ፥ ዝቃጭ። ቅ 2. (ዘይ.) ሰነፍ።

**ዝፍዝፍ** “ዘፈዘፈ” ስር ተመ.

**ዝፍጥጥ** “*ዘፈጠጠ” ስር “ዘፍጣጣ”ንተመ.

**ዞ** የ“ዘ” ፊደል ሳብእ ዘር።

**ዞሳ** ስ ስራ መፍታት፥ ቦዘን።

**ዞሳ ዋለ** ግ ቦዘነ፥ ስራ ፈታ።

**ዞማ** ቅ ለስላሳ፥ ያማረ (ፀጉር)።

**ዞረ** ግ 1. በአንድ ነገር ዙሪያ ሄደ፣ ከበበ። *ታቦቱ ቤተክርስቲያኑን ሰስት ጊዜ ዞረ*፡ 2. ተሽከረከረ፥ ክብ ሰራ፥ ሾረ። 3. የነበረበትን ቦታ፥ አቅጣጫ ቀየረ፣ ከአንድ ቦታ ወደ ሌላ ተሳለፈ። 4. ብዙ ቦታ ሄደ፥ ደረሰ። *ሓለምን ዞረ*፡ 5. ወዲያና ወዲህ ሄደ፥ ተንቀዋለለ። 6. ወደ ሌላ ተሳለፈ፥ ተሸጋገረ።

**ዞረሽ እቀፌኝ(አዙረሽ እቀፌኝ)** ስ በተሞቀ አሬራ (ወገሚት) ላይ ወተት ተጨምሮ የሚዘጋጅ የአይብ አይነት ::

**ዞረበት** 1. ግራ ተጋባ፥ ተምታታበት። 2. አተኮረበት፥ አጥብቆ ያዘው፥ ጠመደው።

**መዞሪያ** ስ መታጠፊያ።

**ዘዋራ** ቅ 1. ሰዋራ (ቦታ)። 2. ጠመዝማዛ (መንገድ)።

**ዙሪያ(ዙርያ)** ቅ 1. ክብ። ስ 2. አካባቢ። 3. ዳር፥ የአንድ አካል ጠርዝ።

**ዙሪያ ነው** ጠመዝማዛ ነው (መንገድ፥ ነገር)።

**ዙሪያ ገባው** አካባቢው በሞላ።

**ዙሪያ ጋሜ** ስ መሃሉ ተላጭቶ በራስ ዙሪያ የሚቀር ፀጉር (ስእሉን ፀጉር አሰራር ስር ተመ.)።።

**ዙሪያ ጥምጥም** ቅ ቀጥተኛነት የሌለው፥ ጠመዝማዛ የሆነ ረዥም (መንገድ)።

**ዙር** ቅ 1 ክብ። ስ 2 አንድ የደርሶ መልስ ጉዞ። 3 አንድ የተወሰነ ድርጊት የሚከናወንበት ጊዜ። *1ኛ ዙር/ 2ኛ ዙር*። 4. ተራ።

**ዙረት** ስ 1. የተወሰነ አላማ ሳይኖር ከቦታ ወደ ቦታ መሄድ፥ መንሸራሸር። 2. ኡደት፣ በአንድ አካል ዙርያ የመሄድ፥ የመንቀሳቀስ ድርጊት።

**ዟሪ** ቅ 1. ከአንድ ቦታ ወደ አንድ ቦታ ወይም ወደተለያየ ቦታ የሚሄድ፥ አንድ ቦታ ረግቶ የማይቀመጥ። 2. የተላለፈ፥ የሚተላለፍ (ከአንድ ገፅ ወደሌላው) ::

**ዞር አለ** ግ 1. ገለል አለ። 2. ጠምዘዝ አለ ::

**ዞር አለበት** 1. አመመው። 2. ግራ ተጋባ፥ ተምታታበት።

**ዞር አደረገ** ግ 1. ገለል አደረገ። 2. አሸሸ። 3. ጠምዘዝ አደረገ፣ አቅጣጫውን ቀየረ።

**ዘወርዋራ** ቅ ጠመዝማዛ፥ ቀጥተኛነት የሌለው።

**ዝውውር** ስ ቅያሬ፣ ልውውጥ፣ እንቅስቃሴ።

**ተዘዋዋረ** ግ 1. ከአንድ ቦታ ወደ ሌላ ሄደ። 2. ተለዋወጠ፥ ተቀያየረ። 3. ተዟዟረ፥ ተጠማዘዘ (ቦታውን ለቆ)። 4. ወዲያና ወዲህ ሄደ፣ ዞረ።

**ተዘዋዋሪ** ቅ 1. ከአንድ ቦታ ወደ ሌላ የሚሄድ፣ ተንቀሳቃሽ፥ ዟሪ። 2. ቋሚ አድራሻ የሌለው። *ተዘዋዋሪ ነጋዴ።*

**በተዘዋዋሪ** ተው.ግ. 1. በሌላ ሰው አማካኝነት፥ በእጅ አዙር። 2. በሌላ አባባል። 3. ስልክ ደዋዩ ሳይሆን የተደወለለት ሰው ሂሳቡን የሚከፍልበት የስልክ ጥሪ።

**ተዛወረ** ግ 1. ተቀየረ፥ ተለወጠ። 2. ተላለፈ፥ ተጋባ (በሽታ)። 3. ወደ ሌላ ቦታ ተመደበ (ለስራ፥ ለኑሮ)። 4 ከአንድ ደረጃ ወደሌላ ደረጃ፥ ከክፍል ወደክፍል አለፈ፥ ተሸጋገረ (ለተማሪ)።

**ተዟዟረ** ግ 1. ወዲያና ወዲህ አለ፥ ተንቀሳቀሰ። 2. ተቀያየረ፥ ተለዋወጠ ::

**ተዟዟሪ** ቅ 1. ቋሚ አድራሻ የሌለው። *ተዟዟሪ ነጋዴ*።2. ተቀያያሪ።

**አዘዋወረ** ግ 1. አቀያየረ፥ አለዋወጠ። 2. ወደ ሌላ ስራ፥ ስፍራ መደበ። 3 ወዲያ ወዲህ ወሰደ፥ አንቀሳቀሰ፥ አጓጓዘ። 4. አቀያየረ።

**አዛወረ** ግ 1. ቀየረ፥ ለወጠ። 2. አስተላለፈ (በሽታን)። 3. ወደ ሌላ ስራ መደበ፥ ክፍል አሳለፈ ::

**አዞረ** ግ 1. አሽከረከረ፥ ጠመዘዘ። 2. ጠመጠመ። 3. አንቀዋለለ፥ አንከራተተ። 4. አሄደ፥ አበራየ። 5.አጥወለወለ፥ አመመ (ራስን)። 6. ከአንድ ቦታ ወደ ሌላ ቦታ ወሰደ። 7. አቅጣጫ ቀየረ፥ አስቀየረ። 8. አስተላለፈ፥ አሻገረ። *በጀቱን አዞረ።*

**አዙሮ አየ** አመዛዘነ፥ አስተዋለ።

**አዞረበት** 1. አምታታበት፥ ግራ አጋባው። 2. መተት አደረገበት።

**ማዞሪያ** ስ 1. ከቅል ወይም ከቆርቆሮ የሚሰራና ሊጥን ምጣድ ላይ በክብ ቅርፅ እያሰፉ ለመጋገር የሚያገለግል እቃ። 2. ከተለያዩ ቦታዎች የሚመጡትን የስልክ ጥሪዎች በመቀበል

ከሚፈለገው መስመር ጋር የማገናኘት ስራ የሚካሄድበት የስልክ ክፍል። 3. የትራንስፖርት መስመር መነሻ÷ መድረሻ፣ መታጠፊያ።

**ኣዙሪት** ስ 1. በወራጅ ውሃ ወይም በወንዝ ላይ ክብ እየሰራ የሚሽከረከር ውሃ። 2. ኣእምሮ የሚያስት፣ የሚጥል በሽታ ።

**ኣዟሪ** ስ የሚሸጡ እቃዎች በመያዝ ወዲያና ወዲህ እየተዘዋወረ የሚሸጥ ነጋዴ ።

**ኣዟዟረ** ግ ኣለዋወጠ÷ ኣቀያየረ።

**ዦግ** ስ ወገን÷ ነገድ ።

**ዦፍ** ስ1. ከእንግዴ ልጅ ጋር የሚወጣ ሽል የተጠቀለለበት ልፋጭ መሰል ነገር። 2. የማዠማ ማር ሽፋን። 3. በእንቁላል ውስጥ በኣስኳሉ ዙሪያ የሚገኝ ነጭ ዝልግልግ ፈሳሽ።

**ዦጼ(ዦጺ)** ስ በበረሃ የሚበቅል÷ እንጨቱ ጥቁርና ጠንካራ የሆነ የእፀዋት ኣይነት።

**ዧ**[1] የ"ዠ" ፊደል ፍንፅቅ ዘር።

**ዧ**[2]

**ዧ ብሎ ተኛ** ተዘርግቶ÷ ተመቻችቶ ተኛ።

**ዧ ብሎ ወደቀ** በቁመቱ÷ እንጻለ ዘፍ ብሎ ወደቀ ።

**ዧሪ** "ዞረ" ስር ተመ.

# ዠ

**ዠ** ከ"ዘ" ፊደል ዘር ቀጥሎ የሚመጣ የአማርኛ ፊደል (ግእዙ ሆሄ)፡፡

**ዠለተ "ጀለተ"** ን ተመ.

**ዠለጠ(ጀለጠ)** ግ1. በዱላ መታ (ወደ ጀርባ፥ ቂጥ ወይም ጎን አካባቢ)፡፡ 2.አለፋ(ለምሳሌ ልብስን አዘውትሮ በመልበስ፥ያልተለፉ ቆዳን በእግር በመርገጥ፥...)፡፡

**ዠመገገ** ግ ሸመጠጠ፤ ፍሬ የተሸከመውን ዛላ በመዳፉና በጣቶቹ መሃል አስገብቶ ወደታች በመሳብ፥በመጎተት (በማለብ አይነት) ፍሬውን እየለየ አራገፈ፥ ወሰደ፡፡

***ዠሞለሞለ**

**ዥሙልሙል** ቅ ሞላላ ቅርፅ ያለው፡፡

**ተዥሞለሞለ** ግ 1. ሞላላ ቅርፅ ያዘ፡፡ 2. ተትጎለጎለ (ጪስ)፡፡

**አዥሞለሞለ** ግ ሞላላ አደረገ፡፡

***ዠረረ**

**ዠረር አለ** ግ በብዛት ፈሰሰ፥ ወረደ፡፡

**ዠረር አደረገ** ግ በብዛት አፈሰሰ፥ አወረደ፡፡

**ዠረገደ**[1] ግ መታ፥ደበደበ፡፡

**ዠረገደ**[2] ግ ፈለፈለ ፥ብዙ ወለደ፡፡

**ዠረገደ**[3] ግ አረዘመ፡፡

**ዠርጋዳ** ቅ ቁመቱ ትልቅ የሆነና የሚያምር ፣ መለሎ፡፡

**ተዠረገደ** ግ ቁመታም ሆነ፡፡

**ዠረገገ(ጀረገገ)** ግ ዠመገገ፥ ሸመጠጠ (ፍራፍሬን ከዛፍ ላይ)፡፡

**ዥርግግ አለ** ግ በብዛት አፈራ፥ ፍሬው ተንጠለጠለ፡፡

**ተንዠረገገ** ግ በብዛት ተንጠለጠለ (ፍራፍሬ፥...)፡፡

**አንዠረገገ** ግ በብዛት አንጠለጠለ፡፡ *ጌጣጌጥ ነገሮች አንገቷ ላይ አንዠርግጋለች/ወይም አንዠርግጓል፡፡*

**ዠርባ "ጀርባ"**ን ተመ.

***ዠቀዠቀ**

**ዠቅዠቃ** ቅ በብዛት የሚያፈስ፡፡

**ተንዠቀዠቀ** ግ 1. በብዛት ወረደ፥ ፈሰሰ (ፈሳሽ)፡፡ 2. ተርበደበደ፥ ፈራ፥ ራደ፡፡

**አንዠቀዠቀ** ግ 1. በብዛት አወረደ፥ አፈሰሰ (ፈሳሽን)፡፡ 2. አርበደበደ፥ አስፈራራ፥ አራደ፡፡

***ዠበረረ**

**ዠብራራ(ጀብራራ)** ቅ 1. ነሁላላ፥ ነገሮችን ልብ ብሎ የማያስተውል ፡፡ 2. ሰካራም፡፡

**ዥብርር አለ** ግ 1. በጣም ተንዠባረረ፡፡ 2. ሰከረ፡፡

**ዥብርር አደረገ** ግ 1. በጣም አንዠባረረ፡፡ 2. በጣም አሰከረ፡፡

**ተንዠባረረ** ግ 1. ነሆለለ፥ ነገሮችን ልብ ብሎ የማያስተውል ሆነ ፡፡ 2. በጣም ሰከረ፡፡

**አንዠባረረ** ግ 1. አነሆለለ፥ አጃጃለ፡፡ 2. በጣም አሰከረ፡፡

**ዠበበ** ግ ሸለብ አደረገ፥ ዘመመ፡፡

**ዠበብ አደረገ** ግ ሸለብ አደረገ፥ አንቀላፋ፡፡

***ዠበበ**

**ዠባባ** ስ የሚንዣበብ(አሞራ፥..)፡፡

**ተንዣበበ** ግ ተዘረጋ፥ ተንሳፈፈ( በክንፍ...)፡፡

**ዣበበ** ግ ክንፉን ዘረጋ፥ ወጠረ፡፡

**ዠበደ(ጀበደ)** ግ ዠለጠ፡፡

**ዠበድ አደረገ** ዝ.ከ.

**ዠብራራ "*ዠበረረ"** ስር ተመ.

**ዠብዱ(ዠብድ) "ጀብዱ"** ን ተመ.

**ዠተሬ "ዦተሬ"** ን ተመ.

**ዠንዲ "ጀንዲ"** ን ተመ.

***ዠወለለ**

**ዠውላላ** ቅ ጉትት፥ ረዥም ፡፡

**ዥውልል አለ** ግ ተንዠዋለለ ፡፡

**ተንዠዋለለ** ግ ተጎተተ፥ ወደጎን ረዘመ ፡፡

**አንዠዋለለ** ግ ጎተተ፥ አረዘመ፡፡

**ዠውዣዋ "ጀውጃዋ"** ን ተመ.

**ዠገዠገ**[1] ግ የፍየል የበግ አንጀትን ፣ጅማትን አከረረ (ለከራር፥ ለደጋን)፡፡

**ዠገዠገ**[2] ግ አለመጠን ረዘመ፤ ቅጥ ቢስ ሆነ፡፡

***ዠጎረጎረ**

**ዥጉርጉር** ቅ ዝጉርጉር፥ ቡራቡሬ፥ ነብርማ ፡፡

**ተዥጎረጎረ** ግ ተዝጎረጎረ፥ በተለያዩ ቀለማት ቀለመ ፡፡

**አዥጎረጎረ** ግ አዝጎረጎረ፥ በተለያዩ ቀለማት አቀለመ፥ ሸለመ ፡፡

**ዠጠዠጠ** ግ ገጠገጠ፥ በብዛት ተከለ፥ ደረደረ፡፡

**ዡ** የ"ዠ" ፊደል ካእብ ዘር ፡፡

**ዢ** የ"ዠ" ፊደል ሳልስ ዘር ፡፡

**ዣ** የ"ዠ" ፊደል ራብእ ዘር ፡፡

ዠንደረባ "ጀንደረባ" ን ተመ.
ዠንጥላ "ጀንጥላ" ን ተመ.
ዠገረ ግ አንስቶ ያዘ ፥ ተሸከመ::
ዠግሬ ስ 1፡ የሚሸከም:: 2. መሳሪያ ይዞ ሂላ ሂላ የሚከተል ሎሌ::
ዤ የ"ዠ" ፊደል ሃምስ ዘር ::
ዥ የ"ዠ" ፊደል ሳድስ ዘር ::
ዥሙልሙል "*ዠሞለሞለ" ስር ተመ.
ዥማት "ጅማት" ን ተመ.
ዥምባዥቦ ስ ወሳንሳ፤ በመተባበር በትክሻ የሚያዝ ሸክም ማንጠልጠያ ::
ዥረት "ጅረት" ን ተመ.
ዥራት "ጅራት" ን ተመ.
ዥብራ "ጅብራ" ን ተመ.
ዥንፎ "ጅንፎ" ን ተመ.
ዥጉርጉር "*ዠጎረጎረ" ስር ተመ.
ዥዋዥዌ "ጅዋጅዌ" ን ተመ.
ዥው "ጅው" ን ተመ.
ዥግራ "ጅግራ" ን ተመ.

ዦ የ"ዠ" ፊደል ሳብእ ዘር::
ዦተሬ(ዠተሬ፥ጆተሬ) ስ ራብ ብትን የዘንጋዳ ሰብል አይነት::
ዧ[1] የ "ዠ" ፊደል ፍንፅቅ ዘር::
ዧ[2]
ዧ ብሎ ዘነመ በሃይል ዘነመ::
ዧ ብሎ ፈሰሰ ግልብጥ ብሎ ፈሰሰ::
ዧ መንዧለ ግ 1.እንደልቡ ሆነ::2.በገፍ ሰጠ፥ ቸረ::

# የ

**የ** ከ "ገር" ፊደል ዘር ቀጥሎ የሚመጣ የአማርኛ ፊደል (ግእዙ ሆሄ) ።

**የ—** 1. ባለንዝብነትን የሚያመለክት ወይም በገላጭነት የሚያገለግል ቅፅላዊ ሃረግ ለመመስረት የሚያስችል ምእላድ። *የእኔ መፅሃፍ/ የፕሬዚዳንቱ ጽማካሬ*፡ 2. ከ—የመጣ፡ የተገኘ፡ በ—ውስጥ የተሰራ፡ የተመረተ ለማለት የሚያገለግል። *የጎጃም ጤፍ/የኢትዮጵያ ቡና*። 3. በ—የተሰራ፡ የተደረገ፡ የተከናወነ፡ የቀረበ ወይም ስርቶ ያወጣው፡ ያስገኘው፡ ያቀረበው። *የሸማኔ ጥበብ /የፋብሪካ ውጤት/የተማሪዎች መዝሙር*። 4. በ—ላይ ያለ፡ የሚታይ፡ የሚገኝ ወይም—ያለው። *የመኪናው ቀለም/ የመንገዱ ርዝመት/ የቤቱ ግራይ*፡ 5.— የሚገኝበት፡ የሚቀመጥበት፡ የሚኖርበት። *የገንዘብ ቦርሳ/ የከብት ማደሪያ* ። 6. ከ—የተሰራ፡ የተዘጋጀ ለማለት የሚያገለግል። *የወርቅ ቀለበት/ የገብስ ጠላ*። 7. —ን ንብረቱ ያደረገ፡ የሚያዘወትር፡ አጥብቆ የሚይዝ፡ የሚያንፀባርቅ፡— የሚታይበት። *የስራ ሰው/ የሞቅሞቅ ቤት*፡ 8.—ን በተመለከተ ያለ ለማለት የሚያገለግል። *የዘመድ ናፍቆት/የሃገር ፍቅር/ የመኖሪያ ቤት ችግር*። 9. በ—ሁኔታ ላይ ያለ፡ —ያደረገ፡ የስራ፡ ያከናወነ በማለት በቅፅል መልክ ለመግለፅ ወይም በመስተአምርነት የሚያገለግል። *የቸከለ ሰው ችግረኛን የረዳ*፡ 10. በ —ሁኔታ፡ መልክ የተከናወነ፡ የተደረገ፡ የተሰራ ለማለት ወይም ውልድ ተውሳከ ግስን ለመመስረት የሚያገለግል። *የእምብርክ/ የፊጥኝ*። 11. ለ— ሲባል። *የኑሮ/ የአገልግሎት* ።

**የለ** ግ አለመኖርን ለመግለፅ የሚያገለግል የ"አለ" አፍራሽ፡ ተቃራኒ፡ "አይደለም" ለማለት በአፍራሽነት ለመናገር የሚያገለግል። *እመጣለሁ አልከኝ እንዴ? የለም አላልኩህም*። በሚያስር ጊዜ "ም"ን ይጨምራል (ለምሳሌ፡ እኔ የለሁም፡ አንተ የለህም፡ እሱም የለም፡ …)፡ ከጥገኛ መስተፃምር "የ" ጋር ሲነገር "የሌለው"፡ "የሌለህ"፡ "የሌለ"፡… እያለ ይዘረዝራል። የሩቅ ሃላፊው "አልነበርኩም"፡ "አልነበርክም"፡ አልነበረም…ይላል። የትንቢት አንቀፁ አልኖርም፡ አትኖርም፡ አይኖርም፡… እያለ ይዘረዝራል።

**—የለሽ ____** የሌለው ለማለት የሚያገለግል። *ስርኣት የለሽ* ።

**የለሙ አገሮች "ለማ"** ስር ተመ.

**የላም ጨው "ላም"** ስር ተመ.

**የሎሚ እሽት "ሎሚ"** ስር ተመ.

**የሎስ** ስ ግልገል አንሳ፡ ግዙፍ የአሞራ አይነት።

**የምር "መረረ"** ስር ተመ.

**የምስራች "ምስራች"** ስር ተመ.

**የብስ** ስ በሰፊ ውሃ ያልተሸፈነው፡ ውቅያኖስ ያልሆነው፡ ደረቁ የመሬት ክፍል።

**የቦ** ስ ትንሽ ጦር ።

**የተፀውኦ ስም** ስ (ሰዋ.) ሰው፥ ድርጅት፡ ሃገር፡… የሚጠራበትና ተለይቶ የሚታወቅበት ስም።

**የት** ተው.ስ. አቅጣጫን፡ ቦታን ለማወቅ የሚቀርብ መጠየቂያ።

**የቱ (የትኛው)** ተው.ስ. ማንነቱን፡ አንዱን ከሌላው ለይቶ ለማወቅ፡ ለመጠየቂያ የሚያገለግል ቃል። *ስራ አስኪያጁ የቱ ነው?*

**የትም የት** የትም ቢሆን፡ በማንኛውም ቦታ። *የትም የት ብትሄድ አታመልጠኝም*።

**የትና የት** 1. አይመጣጠንም፡ ይለያያል ለማለት የሚያገለግል ቃል። *እዚህ የሚሸጠውና እዚያ የሚሸጠው የትና የት፡ አይገናኝም*። 2. በጣም ሩቅ ለማለት የሚያገለግል። *ቤቱ ቅርብ እንዳይመስልህ፡ የትና የት ነው*።

**የትየለሌ(የት እየለሌ)** በጣም ሩቅ ወይም በጣም ብዙ ለማለት የሚያገለግል አባባል።

**የኔ ቢጤ "እኔ"** ስር ተመ.

**የኔታ(የንታ)** ቅ (ቤ.ክህ.) መምህሬ፡ አስተማሪዬ ለማለት የሚያገለግል የአክብሮት አጠራር ።

**የአዋይ "ዋለ[1]"** ስር ተመ.

**የካቲት** ስ ከጥር ቀጥሎ የሚመጣ የአመቱ ስድስተኛ ወር ስም ።

**የክት "ከተተ"** ስር ተመ.

**የወል "ወል"** ስር ተመ.

**የዋህ** ቅ 1 ገር፡ ቅን። 2 ሞኝ፡ ተላላ ።

**የዪ** ስ ተኩላ ።

**የጉድፍ "ጎደፈ"** ስር ተመ.

**የፊጥኝ "ፊጥኝ"** ን ተመ.

**ዩ** የ"የ" ፊደል ካእብ ዘር ።

**ዩራኒየም** ስ የአቶሚክ ሃይልን ለማመንጨት የሚያገለግል የማእድን አይነት ።

**ዩኒቨርሲቲ** ስ ከፍተኛ ትምህርት በዲግሪ ደረጃ የሚሰጥበት የትምህርት ተቋም ።

**ዩኒፎርም** ስ በአንድ አይነት የስራ መስክ የተሰማሩ ሰዎች ወይም በአንድ ትምህርት ቤት ውስጥ

የሚማሩ ተማሪዎች ከሌላው እንዲለዩበት ታስቦ የሚለብሱት አንድ አይነት ስፌትና ቀለም ያለው ልብስ።

**ዪ** የ"የ" ፊደል ሳልስ ዘር።

**ያ**[1] የ"የ" ፊደል ራብእ ዘር።

**ያ**[2] (ብ.ቁ. እኒያ፣ እነዚያ፣ እነዛ፣ አን.ዖ.ያቺ) የሩቅ አመልካች ተውላጠ ስም። *ያ መፅሃፍ የኔ ነው።*

**—ያ (—ኢያ)** በአርእስታዊ ስሞች መድረሻ ላይ እየተቀጠለ አንድ ነገር የሚፈፀምበትን ጊዜ፣ ቦታ፣ መሳሪያ፣ ዘዴ፣... የሚያመለክቱ የማድረጊያ ስሞችን ለመመስረት የሚያገለግል ምእላድ (ለምሳሌ፦ መጥረግ ›መጥረጊያ፣ መስበር ›መስበ ርያ)።

**ያህል(ያክል) "አክለ"** ስር ተመ.

**ያለ– "አለ–"** ን ተመ.

**ያለበለዚያ "አለበለዚያ"** ን ተመ.

**ያለዚያ** ዝ.ከ.

**ያመራማሪ "መረመረ"** ስር ተመ.

**__ያን** "—ዊ" ን በመቀጠል በተመሰረቱ ቅፅሎች ላይ እየገባ የብዙ ቁጥር ስምን ለመመስረት የሚያስችል ምእላድ (ለምሳሌ፦ ኢትዮጵያ ኢትዮጵያውያን፣ ሃሳባዊ ›ሃሳባውያን።

**ያዘ** ግ 1. ለቀም፣ አፈፍ አደረገ፣ በእጁ አስገባ፣ ጨበጠ። 2. ተሸከመ፣ አነሳ፣ ታቀፈ። 3. አቆረ፣ ቋጠረ። *መግል ያዘ*፣ 4. ቻለ፣ አከተተ። *እንስራው ሁለት ገንቦ ውሃ ያዛ*፣ 5. በቁጥጥር ስር አዋለ። *ወንጀለኛ ያዘ/ ጠላት ከተማውን ያዘ*፣ 6. አቆመ፣ አገደ፣ እንዳይሰራ፣ እንዳይሄድ አደረገ። *በወሬ ያዘኝ*፣ 7. ማቀጣጠል፣ ማብቀል፣ ማፍራት፣... ጀመረ። *ብርቱካኑ ይዟል*። 8. አንድን የተወሰነ ድርጊት በማከናወን ላይ ሆነ፣ ተሰማራ። *ጨዋታ ያዘ/ ስራ ያዘ*፣ 9. ንብረትን፣ ገንዘብን ወይም ሌላ ነገርን አኖረ፣ አስቀመጠ። 10. በአእምሮው መዘገበ፣ አስታወሰ። 11. በእጁ ኖረው፣ በእጁ አደረገ። *ገንዘብ ይዟል/ መታወቂያ ይዟል*። 12. ከ—ጋር አብሮ ሆነ። *ልጆቹን ይዞ ሄደ/ ሰው ይዤ እከራከራለሁ*። 13. አመመ። *ጉንፋን ያዘው*። 14. እጁን በአንድ ነገር ላይ አሳረፈ። *ወገቡን ይዞ ቆመ/ በመገረም ራሱን ያዘ*፣ 15. በአንድ አይነት ደረጃ፣ ሁኔታ፣... ተገኘ። *የአንደኛነትን ደረጃ ያዘ*። 16. አደረ(በት)። *ፍርሃት ያዘው።*

**ያዘች** ግ ፀነሰች፣ አረገዘች።

**ያዝ ለቀቅ አደረገ** ግ 1. አጥብቆ ሳይከታተል ቀረ (ጉዳይን)። 2. አንድ ጊዜ ጤንነት ሌላ ጊዜ ደግሞ ህመም ተሰማ።

**ይዞህ ይሂድ**(እር.) ለሞት ይዳርግህ።

**መያዣ** ስ 1. እጀታ፣ መጨበጫ። 2. እቃ መከተቻ፣ ማስቀመጫ (መቋጠሪያ፣ ከረጢት፣...)። 3. እንደዋስትና የሚያገለግል እቃ፣ ገንዘብ። 4. ከነጭ ጨፍ እንጀራ ስር ተደርጎ የሚቀርብ የቅይጥ ወይም የጥቁር ጤፍ እንጀራ።

**ይዘት** ስ 1. በአንድ ነገር ውስጥ ያሉ፣ የሚገኙ ነገሮች በጥቅል። 2. በአንድ ፅሁፍ ውስጥ የሚገኝ ርእስ ጉዳይ፣ መልእክት፣...። 3. ባለአንድ ነጥብ ያራዳዊ የዜማ ምልክት፣ ምልክቱ (.) ነው።

**ይዞታ** ስ 1. በንብረትነት ያለ እቃ፣ ነገር፣ ሃብት፣... (በዚውን ጊዜ መሬት)። 2. አኳኋን፣ ሁኔታ፣...።

**ተያዘ** ግ 1. በፖሊስ ወይም በህዝብ ቁጥጥር ስር ዋለ፣ ታሰረ። 2. ያመለጠ፣ የሸሸ፣...ሰው ወይም እንስሳ በቁጥጥር ስር ሆነ፣ እጅ ገባ። 3. በትድሚያ ለመጣ ሰው ወይም በሌላ ሁኔታ ቦታው፣ መቀመጫው፣ እቃው፣... ለሌላ ተቀመጠ፣ ተከበረ፣ ቆየ። *በትያትር ቤቱ ወንበር ተይዞልሃል*። 4. ተለከፈ(በበሽታ)። 5. ተጠመደ(በስራ፣...)። 6. በመያዣ መልክ ተቀመጠ (እቃ፣ ገንዘብ፣...)።

**ተያዥ** ስ ዋስ፣ አንድ ሰው ጥፋት ቢያደርስ ስለሰውዬው ተጠያቂ ለመሆን በፈቃደኝነት ሃላፊነቱን የሚወስድ ሰው።

**ተያያዘ** ግ 1. ተሳሰረ፣ ተቆላለፈ፣ ተጣመረ፣ ተጣበቀ። 2. ተቀጣጠለ፣ ነደደ (እሳት)። 3. ተጣመደ፣ ተጣላ። 4. ተናነቀ፣ ግብግብ ገጠመ። 5. ፈር ያዘ፣ ተጀመረ፣ በመከናወን ላይ ሆነ (ስራ፣...)።

**አያያዘ** ግ 1. አነደደ፣ አቀጣጠለ(እሳትን)። 2. አጣላ። 3. አገዘ፣ ስራው እንዲጀመር አደረገ። 4. አጣበቀ፣ አቆላለፈ፣ አጣመረ፣ አስተሳሰረ። 5. ረዳ፣ አገዘ (በሸክም)።

**አያያዝ** ስ የስራ አጀማመር፣አንድን ድርጊት የማከናወን ዘዴ፣ አኳኋን፣...። *አያያዙ አያምርም/እንደአያያዙ ስራውን ቶሎ ይጨርሳል።*

**አያያዥ** ቅ አጣይ፣ ነገረኛ።

**አስያዘ** ግ 1. በቁጥጥር ስር እንዲሆን አደረገ። 2. አንድን እቃ፣ ገንዘብ በመያዣ ሰጠ።

**ዬ** የ"የ" ፊደል ሃምስ ዘር።

**—ዬ "—ኤ"** ን ተመ.

**ይ** የ"የ" ፊደል ሳድስ ዘር ።

**ይህ**(ብ.ቁ.**እነዚህ/እኒህ፤** አን.ዖ. **ያቺ**) የቅርብ አመልካች ተውላጠ ስም ወይም ቅፅል። *ስፌው ጠረጴዛ ይህ ነው/ ይህ ጠረጴዛ ስፊ ነው።*

**ይሆናል "ሆነ"** ስር ተመ.

**ይለይለት "ለየ"** ስር ተመ.

**ይሉኝታ "አለ"** ስር ተመ.

**ይሉኝ አይል** ዝ.ከ.

**ይልቅ "ላቀ"** ስር ተመ.
**ይሙት በቃ "ሞተ"** ስር ተመ.
**ይርጋ "ረጋ"** ስር ተመ.
**ይቅርታ "ቀረ"** ስር ተመ.
**ይበል "አለ"** ስር ተመ.
**ይብላኝ "በላ"** ስር ተመ.
**ይቶት** ስ መነኩሲት ወይም እቃቢት የምትጠራበት ስም፡ እማሆይ።
**ይድረስ "ደረሰ"** ስር ተመ.
**ይግባኝ "ገባ"** ስር ተመ.

**ይፋ** ቅ ገሃድ፡ ግልፅ።
**በይፋ** በገሃድ፡ በግልፅ።
**ይፋ ወጣ** 1. ሁሉም እንዲያውቀው ተደረገ፡ ተነገረ። 2. ታየ፡ ተገለጠ።
**ዮ** የ"ዮ" ፊደል ሳብእ ዘር።
**—ዮሽ** አንድ ነገር ስንት እጅ፡ የስንት ወገን፡ የምን ወገን እንደሆነ ለማሳየት ከቁጥር በስተመድረሻ የሚገባ ምእላድ። *ሁለትዮሽ/ ዶጋርዮሽ፡*
**ዮጋ** ስ የራሱ ፍልስፍናና አስተምህሮ ያለው የሂንዱ ስፖርታዊ የሰውነት እንቅስቃሴ።

# ደ

**ደ** ከ "የ" ፊደል ዘር ቀጥሎ የሚመጣ የአማርኛ ፊደል (ግእዙ ሆሄ)::

**ደሀየ** ግ ተቸገረ፡ ለኑሮ አስፈላጊ የሆኑ ነገሮችን አጣ::

**ደሃ (ድሃ)** ቅ 1. ችግረኛ:: ስ 2. በቂ መተዳደሪያ የሌለው ሰው:: 3. ለማኝ::

**ደሃ ነቀል** ስ የአረም አይነት፡ አቀንጭራ::

**የደሃ አባት** ስ ለደሃ የሚያዝን፡ ደሃን የሚረዳ፡ ቸር፡ ለጋስ ሰው::

**ደሃ አደግ** ቅ እናት አባቱ የሞቱበት፡ በችግር ያደገ::

***ደሃረ**

**ደሃራይ(ደሃራ÷ዳህራይ÷ዳራ)** ስ በስተኋላ ያለ የከርቻ ላይ ድጋፍ፡ መደገፊያ(ስእሉን ከርቻ ስር ተመ.)::

**ድህረ___** ከ_ በኋላ፡ የ "ቅድመ_" ተቃራኒ:: *ድህረ ወሊድ/ድህረ ሳብዮት::*

**ድህረ ምረቃ** ስ ከመጀመሪያ ዲግሪ በኋላ የሚሰጥ የትምህርት መርሃ ግብር::

**ደህና** ቅ 1. ጥሩ፡ መልካም:: 2. ሰላም፡ ጤና:: *ደህና ነህ ?*

**ደህንነት** ስ 1. በጥሩ፡ በመልካም ሁኔታ ላይ መሆን:: 2. ጤንነት:: 3. የአንድን አገርና ህዝብ ሰላም፡ ፀጥታ፡ ጥቅም፡... ለማስከበር ተፃራሪ ሁኔታዎችን በምስጢር የሚከታተልና መረጃዎችን የሚሰበስብ (ሰው ወይም ድርጅት)፡ ነጭ ለባሽ፡ ሰላይ::

**ደለሀ** ግ ድልሀ አዘጋጀ::

**ድልሀ** ስ 1. ተፈጭቶ በውሃ የተላቆጠ በርበሬ:: 2. የተፈጨ በርበሬ::

**ድልሀ መሰለ** ቀላ፡ በርበሬ መሰለ::

**ደለለ[1]** ግ አባበለ፡ሸነገለ፡ አሞኘ፡ አታለለ::

**መደለያ** ስ መሸንገያ፡ ማባበያ::

**ደላይ** ቅ ሸንጋይ፡ አታላይ::

**ድለላ** ሽንገላ::

**ድልል** ቅ በቀላሉ የሚታለል፡ የሚሸነገል::

**ተደለለ** ግ ተሸነገለ፡ ተታለለ::

**ደለለ[2]** ግ ገንዘብ እየተከፈለው ተፈላላጊዎችን (ሻጭና ገዥን፡አከራይና ተከራይን፡...) አገናኘ፡ አስማማ::

**ደላላ** ስ 1. በመደለል ስራ ላይ የተሰማራ ሰው:: ቅ 2. አታላይ፡ በውሸት አግባብቶ ለማሳመን የሚሞክር::

**ድለላ** ስ ተፈላላጊዎችን የማገናኘት፡ የማስማማት ስራ::

**ድላል** ስ ለደላላ የሚከፈል ገንዘብ::

**ደለለ[3]** ግ ቀለለ፡ ከመረ (ጎርፍ አፈርን፡አሸዋን፡...)::

**ደለል ስ** ከነበረበት ቦታ በዝናብ ወይም በጎርፍ ተሸክሚነት ተጠርጎ ሌላ ቦታ የሚከመር አፈር፡ አሸዋ፡...::

**ደለላም** ቅ ብዙ ጊዜ ደለል የሚገኝበት (ቦታ)::

**ደለመ** ግ 1. ጠለመ፡ ጨለመ:: 2. ጠፋ፡ ተደመሰሰ (አይን፡ ስለት፡ ትዳር፡...)::

**ደለማ** ስ ጨለማ::

**ደላማ** ቅ ለምጣጣ፡አይን የሌለው(እንጀራ)::

**ደለመጠ** ግ ወፈረ፡ፈረጠመ::

**ድልማጣ** ቅ ፍርጥም ያለ፡ወፍራም::

**ድልምጥ** ዝ.ከ.

**አደለመጠ** ግ ወፈረ፡ ፈረጠመ::

**ደለማ "ደለመ"** ስር ተመ.

**ደለሰ** ግ 1. ቀባ፡ ለከከ (ቅቤን፡...):: 2.አስተኛ፡ መጨለስ(ቡትርን):: 3. ጠፈጠፈ፡ ደለሽ አበጀ::

**ደለሽ** ስ የተለያዩ የእህል አይነቶችን በአንድ ጎተራ ውስጥ እያነባበሩ ለማስቀመጥ ሲያስፈልግ፡ አንዱ አይነት እህል ከሌላው ጋር እንዳይቀላቀል በየመካከላቸው የሚደረግ ስፌድ መሰል የጭቃ ጥፍጥፍ::

**ደለቀ** ግ 1. ደቃ፡ ጎሰመ፡ መታ:: 2. ዘለለ፡ ጨፈረ::

**ድለቃ(ድልቂያ)** ስ ጭፈራ::

**ተደለቀ** ግ ተጨፈረ::

**ደለቀቀ** ግ ዝቆ አነሳ (ወጥን፡ገንፎን፡...)::

***ደለቀቀ**

**ደለቀቅ(ደልቃቃ)** ቅ 1. ቅምጥል፡ የደላው፡ ቀብራራ:: 2. ሞልቃቃ::

**ድልቅቅ አለ** ግ ተንደላቀቀ ::

**ድልቅቅ አደረገ** ግ አንደላቀቀ::

**ተንደላቀቀ** ግ 1. ተቀማጠለ፡ተንቀባረረ:: 2. ተሞላቀቀ::

**አንደላቀቀ** ግ 1. አቀማጠለ፡ አንቀባረረ:: 2. አሞላቀቀ::

**ደለበ** ግ 1. ለብዙ ጊዜ ተቀመጠ፡ ተከማቸ፡ ተከበተ፡ ተጠራቀመ:: 2. ሻገተ፡ ዛገ(ተከማችቶ ብዙ ጊዜ ከመቀመጡ የተነሳ):: 3. ወፈረ፡ ሰባ::

**ድልብ** ቅ 1. የሰባ፡ በጣም የወፈረ(ከብት):: 2. በብዛት ተከማችቶ ብዙ ጊዜ የተቀመጠ::

**ደለንቲ (ደለንቲ)** ቅ ደነዝ፡ፈዛዛ::

**ደለዘ**[1] ግ ሰረዘ፥ አጠፋ፥ ደመሰሰ (ፅሁፍን በቀለም)::

**ድልዝ** ቅ 1. ስርዝ:: 2. ፊት የነበረው ፅሁፍ ተፍቆ ወይም ቅርፁን እንዲለውጥ ተደርጎ በላዩ ላይ ሌላ ሃሳብ የሰፈረበት (ፅሁፍ)::

**ተደለዘ** ግ ተሰረዘ፥ጠፋ፥ተደመሰሰ(ፅሁፍ)::

**ደለዘ**[2] ግ 1. መታ፡ ደለቀ፥ ነረተ:: 2. በርበሬን ከሽንኩርት፥ ከዝንጅብል፡ ከጨው፡... ጋር በማደባለቅ አብሮ ወቀጠ::

**ድልዝ** ቅ ከሽንኩርት፡ ከዝንጅብል፡ከጨው፥... ጋር አብሮ የተወቀጠ(በርበሬ)::

**ደለይ[ነፋስ]** ስ በጥር ወር የሚወጣ የኮከብ አይነት፥ በተጨማሪ **"ኮከብ ቆጠራ"** ን ተመልከት::

**ደለደለ** ግ 1. አስተካከለ፡ አመቻቸ:: 2.መደበ፡ ከፋፈለ:: 3. ወፈረ፥ ፈረጠመ:: 4. ድልድይ ሰራ፡አበጀ:: 5. ከተረ፥ ገደበ (ውሃን ባፈርና በድንጋይ)::

**ድልዳል** ስ 1. ለመኝታ፥ ለመቀመጫ እንዲመች ሆኖ የተዘጋጀ ጉዝጓዝ፥ ምንጣፍ:: 2. በጭነት ከብት ጀርባ ላይ ከጭነቱ ስር የሚደረግ ጉዝጓዝ፥ መደላድል::

**ድልድይ** ስ በወንዝ ወይም በወንዝ ቅርፅ ባለው መሬት ላይ ከእንጨት፡ ከድንጋይ፡ ከብረት፥.. የሚሰራ መሻገሪያ ፥ መሸጋገሪያ::

**መደላድል** ስ ድልዳል::

**ተደለደለ** መደላድል ተበጀ፥ጉዝጓዝ ተደረገ::

**ድልዳላ** ቅ 1. አባጣ ጎባጣ የሌለበት፡ የተስተካከለ (ቦታ፥ መሬት፡...):: 2. የተመጣጠነ አካላዊ አቋም ያለው(ሰው):: 3. (ዘይ.) በእድሜና በአስተሳሰብ የበሰለ::

**ድልድል** ቅ የተደለደለ፥ የተስተካከለ (መሬት)::

**ድልጅል** ስ 1. ክፍፍል:: 2. ምድብ፥ ምደባ::

**ድልጅል አለ** ግ በጣም አበጠ (ሰውነት በህመም ምክንያት) ::

**ተደላደለ** ግ 1. ተከፋፈለ:: 2. (ዘይ.) ረጋ፥ ተመቻቸ (በኑሮ፡...)::

**አደላደለ** ግ 1. አከፋፈለ:: 2. አመቻቸ፥ አስፈላጊውን አሟላ::

**ደለፈሰ** ግ 1. አፈሰ፥ ዛቀ:: 2. ጨፈለቀ፥ ረገጠ (ጭቃን፥...)::

**ደላ** ግ ተመቸ፥ ተስማማ::

**ድሎት** ስ ምቾት::

**ተድላ** ዝ.ከ.

***ደላ**

**አደላ** ግ 1. አድልዎ ፈፀመ:: 2. ወደ አንድ ፊት፡ በኩል፥ አቅጣጫ፥ ወገን፡... አጋደለ፡ በለጠ፥ ረዘመ፥ በዛ፥... ::

**አዳላ** ግ አደላ ::

**አድልዎ(መድሎ)** ስ ይሁነኝ ብሎ አንዱን ወገን በመጉዳት ሌላውን ወገን የመጥቀም ዝንባሌ፥ ድርጊት ::

**ደላላ "ደለለ[2]"** ስር ተመ.

**ደላማ "ደለመ"** ስር ተመ.

**ደላይ "ደለለ[1]"** ስር ተመ.

**ደላጎ** ስ 1. ድብዳብ፥ የበግ ቆዳ:: 2. የቁርበት፥ የነት እላቂ:: 3. (ዘይ.፥ ስድብ) ቂል፥ ሞኝ::

**ደልማጣ "ደለመጠ"** ስር ተመ.

**ደልቃቃ "*ደለቀቀ"** ስር ተመ.

**ደመለለ** ግ ጠቀለለ፥ ሸመለለ::

**ተደመለለ** ግ ተጠቀለለ፥ ተሸመለለ::

**ደመመ** ግ አፈር አለበሰ፥ በአፈር ሸፈነ::

**መደምም(መደንን)** ስ ድራር፥ አስከሬኑን አፈር እንዳይነካው ከጉድጓዱ አፍ ዝቅ ብሎ የሚደረግ ርብራብ፥ ግጣም::

***ደመመ**

**ተደመመ** ግ 1. ተደነቀ፡ ተገረመ:: 2. ዝም አለ፥ ፀጥ አለ::

**አስደመመ** ግ አስደነቀ፡ አስገረመ ::

**ደመረ** ግ 1. ሰበሰበ፡ አከበ፥ አከማቸ፥ ቆለለ:: 2. አንድ ላይ አጠቃለለ (የተለያዩ ነገሮችን፡ ቁጥሮችን፡...):: 3. ደመራ ሰራ፥ አበጀ::

**መደመር** ስ ከአራቱ የስሌት መደቦች አንዱ የሆነና ልዩ ልዩ መጠን ያላቸውን አሃዞች በአንድ ላይ አጠቃሎ የመቀመር ዘዴ::

**የመደመር ምልክት** ስ የመስቀል ቅርፅ ያለው የስሌት ምልክት፥ ምልክቱም (+) ነው::

**ደመራ** (ኢ.ኦ.ተ.ቤ.) ስ 1. መስከረም 16 ቀን የሚከበር የመስቀል በአል ዋዜማ:: 2. ከላይ የተጠቀሰውን በአል አስመልክቶ በስነ ስርአቱ ላይ እንዲነድ የሚደረግ የእንጨት ቁልል፥ ስብስብ::

**ድምር** ስ 1. ክምችት፥ ጥቅል:: 2. በአንድነት የተሰላ፥ የተቀመረ የብዙ ቁጥሮች ጥቅል ውጤት::

**ደመሰሰ** ግ 1. አጠፋ፡ እንዳልነበር አደረገ:: 2. ገደለ፥ በሙሉ ጨረሰ::

**ድምስስ አለ** ግ ተደመሰሰ::

**ተደመሰሰ** ግ 1. ጠፋ፡ ተበላሸ፡ እንዳልነበር ሆነ:: 2. ተገደለ፥ ተጨረሰ (ሙሉ በሙሉ)::

**ደመቀ** ግ 1. ጎላ፡ በግ አለ (ቀለም፥...) :: 2. ተሟሟቀ፡ ተጋጋለ (ጨዋታ፥ ወሬ፥...) ::

3. አማረ፣ ተዋበ፣ ተሽላለመ። *የሰው ወርቅ አያደምቅ*።

**ደማቅ** ቅ 1. የጎላ፣ በግ ያለ (ቀለም፣...)። 2. የሞቀ፣ የተጋጋለ (ጨዋታ፣ ዘፈን፣...)።

**አደመቀ** ግ 1. አሟሟቀ፣ አጋጋለ (ጨዋታን፣ ወሬን፣...)። 2. ተውቦ፣ አምሮ፣ ጎልቶ እንዲታይ አደረገ።

**ደመና** "ዳመና" ስር ተመ.

**ደመኛ** "ደማ" ስር ተመ.

**ደመወዝ(ደሞዝ)** ስ 1. አሰሪው ወገን ለሰራተኛው በየተወሰነ ጊዜ የሚከፍለው የተወሰነ የገንዘብ መጠን፣ የጉልበት፣ የስራ፣ የድካም ዋጋ። 2. ቀለብ ።

**የደመወዝ ጭማሪ** ስ ቀድሞ በነበረው ደመወዝ ላይ የታከለ፣ የተጨመረ ገንዘብ።

**ደመወዝ ከፋይ** ስ ለሰራተኞች ደመወዝ እንዲከፍል የተመደበ ሰራተኛ ።

**ደመደመ** ግ 1. ደፈነ፣ ተመተመ። *ቁስሉን በመድሃኒት ደመደመው* ። 2. ጨረሰ፣ ፈፀመ። 3. በእጅ እየተጫነ አስተካከለ፣ አበጃጀ፣ ከመከመ (ፀጉርን)።

**ድምድማት** ስ የግንብ ወይም የግድግዳ አናት፣ መጨረሻው፣ ክፈፉ።

***ደመጠ**

**ድምጥ** "ድምፅ" ን ተመ.

**ድምጥማጥ** በፊደል ተራው ተመ.

**ተደመጠ** ግ ሰሚ አገኘ፣ ተሰማ።

**ተደማጭ** ቅ ተሰሚ፣ ሃሳቡ ተቀባይነት ያለው።

**ተደማመጠ** ግ አንዱ ሌላው የሚለውንሰማ።

**አደመጠ(አዳመጠ)** ግ በጆሮው ሰማ፣ ሰምቶ ልብ አደረገ።

**አድማጭ** ስ ሰሚ።

**ደማ** ግ 1. ደም ወጣው፣ ደሙ ፈሰሰ። 2. (ዘይ.) ለሃገሩ፣ ለወገኑ መስዋእትነት ከፈለ፣ ታገለ።

**አይደማውም** ስስታም ነው፣ አይሰጥም።

**ደም** ስ 1. በሰው፣ በእንስሳትና በነፍሳት አካላት ውስጥ የሚዘዋወር ቀይ ፈሳሽ። 2. ወዘና፣ ላህይ።

**[ደሙ]ደመከልብ ሆነ** በደረሰበት አደጋ የፈሰሰው ደሙ እንደ አልባሌ ነገር በከንቱ ቀረ፣ ብድር መሳሽ አጣ (በፈፃሚው የፍርድ ወይም የበቀል እርምጃ ባለመወሰዱ)።

**ደሙ ደረቀ** በገዳይና በሟች ቤተሰብ መካከል ተፈጥሮ የነበረው ጠብና ቂም በእርቅ አማካኝነት ቀረ፣ ተተወ።

**ደሙ ሳይደርቅ** የተፈፀመው በደል ሳይቆይ፣ ሳይረሳ፣ በትኩሱ።

**ደሙ ፈላ** በጣም ተናደደ።

**ደም ፍላት** ድንገት የሚያጋጥም ሃይለኛ ንዴት፣ ቁጣ።

**ደሙን መለሰ/ተወጣ** ለተሰነዘረበት ጥቃት ብድሩን መለሰ፣ ተበቀለ ።

**ደም መላሽ** በሌላ ሰው ላይ የተፈፀመን ግፍ የሚበቀል፣ ብድር የሚመልስ።

**ደም መልስ** በሰውነት ውስጥ ያለን ደም ወደ ልብ የሚወስድ ትልቅ የደም ቧንቧ።

**ደሙን አዘራ** ደሙን አፈሰሰ።

**ደሙን አፈሰሰ** ተዋጋ፣ ተጋደለ፣ መስዋእት ሆነ።

**ደም መታት** ከማህፀኗ ብዙ ደም ፈሰሳት።

**ደም ረገጠ** 1. ለጭዳ ተብሎ የፈሰሰ ደም በመርገጡ በበሽታ ላይ ወደቀ፣ ደንቃራ ገባ (አምልኮ)። 2. ወደ ቤቱ ሲገባ እርድ ታረደለት (አዲስ ቤት ለሚገባ፣ ለሙሽራ፣...)።

**ደም ሸተተው** ጠብ፣አምባጓሮ አሰኘው።

**ደም ተቃባ /ተጋባ** ጠላት ተኳሃኝ (በነፍስ ግድያ ምክንያት)።

**ደም ተፋ** በጣም ደከመ፣ ለፋ፣ ተሰቃየ፣ ጣረ (አንድን ነገር ለማከናወን)።

**ደም ተፋሰሰ** 1. ደም ተቃባ። 2. ተጋደለ።

**ደም አስተፋው** 1. በጣም ደበደበው። 2.እጅግ በጣም አሰቃየው (ስራ፣...)።

**ደም አስተፊ** ስ ስሩ ቀይ ቀለም የሚመስል ፈሳሽ ሊወጣው የሚችል የእፅዋት አይነት።

**ደም አስተፊት** ስ መርዛማ በመሆኑ የማይበላ የእንጉዳይ አይነት፣ ምላስ ጎልጉል።

**ደም አፈታበት** ደሙ ከመፍሰስ አላቆም አለ።

**ደም ደም አለው** ቀፈፈው፣ ደስ የማይል ስሜት ተሰማው።

**ደም ጎረሰ** በደም ተለወሰ፣ ደም ሰረበ።

**ደም ጠማው** የመግደል ፍላጎት ያዘው።

**ደም ጠራው** በሄደበት ድንገተኛ ሞት ሞተ።

**ደም ፈሰሰ** 1. ነፍስ ጠፋ፣ ግድያ ተፈፀመ። 2. እንደዶሮ፣ በግ ያለ እንሰሳ ታረደ።3. ሰው ተፈነከተ፣ቆሰለ፣...።

**ደም አፈሰሰ** 1. ዶሮ፣ በግ፣... ከቤቱ አረደ። 2. ሰው ፈነከተ፣ አቆሰለ፣ አደማ። 3. ሰው ገደለ፣ ነፍስ አጠፋ።

**ደም አፋሰሰ** አጋደለ፣ መሳሪያ እንዲማዘዙ፣ እንዲጣሉ፣ እንዲመታቱ ምክንያት ሆነ።

**ደም አፋሳሽ** ቅ ለሌሎች መጣላት፣ መደባደብ፣ መገዳደል ምክንያት የሆነ ወይም

የሚሆን።

**ደሟ ቀረ** ፀነሰች።

**ደሟ ጠራ** የወር አበባዋ ቆመ።

**ደሟ ፍልቅ ያለ** የተዋበች፣ ያማረች።

**የደም አበላ ወሰደው** ብዙ ደም ፈሰሰው።

**ደመ መራራ** ቅ የሚናገረውን፥ የሚያደርገውን ነገር ሁሉ ሰዎች በክፉ የሚተረጉሙበት፥ ነገር የሚነግስበት፥ የሚገንበት (ሰው)።

**ደመ ሞቃት** ቅ ቅንዝረኛ።

**ደመ ሞቃት እንስሳት** ስ በአካላቸው ውስጥ ያለው ደም ሞቃት የሆነና በየትኛውም የአየር የጠባይና አካባቢ የደማቸው ሙቀት የማይለዋወጥ እንስሳት።

**ደመ ቀዝቃዛ** ቅ 1. ቅንዝረኛ ያልሆነ። 2.ቶሎ የማይቆጣ፥ ረጋ ያለ።

**ደመ ቀዝቃዛ እንስሳት** ስ በአካላቸው ውስጥ ያለው ደም ቀዝቃዛ የሆነና በተለያየ የአየር ጠባይና አካባቢ የደማቸው ሙቀት ከፍ ወይም ዝቅ በማለት የሚለዋወጥ እንስሳት።

**ደመ ነፍስ(ደማዊት ነፍስ)** ስ 1. የእንስሳት ነፍስ። 2. (ስድብ) የማያስብ፡ የማያመዛዝን (ሰው)።

**በደመ ነፍስ** 1. ባለማመዛዘን፡ ባለማስተዋል። 2. በተፈጥሮ በተገኘ እውቀት (የሚያከናውኑት ድርጊት)።

**ደመ ግቡ** ቅ መልከ መልካም፥ ውብ፣ ማራኪ ገፅታ ያለው።

**ደም ግባት** ስ ውበት፡ ቁንጅና፥ ወዘና።

**ደም ቅዳ** ስ ከልብ ወደ ሌላው የሰውነት ክፍል የሚሰራጨውን ደም የሚወስድ ትልቅ የደም ቧንቧ።

**[የ] ደም ግፊት/ብዛት** ስ የግፊቱ መጠን መሆን ከሚገባው በላይ ከፍ ብሎ በደም ስሮች ውስጥ የሚካሄድ የደም ዝውውር ሂደት፣ በዚህ የተነሳ የሚፈጠረው ህመምም ደም ግፊት ይባላል።

**ደም ጥሪ** የወር አበባ የሚቆምበት ጊዜ ወይም እንደቆመ ያለው ጊዜ።

**የደም ስር** ስ 1. በሰውነት ውስጥ ደም የሚዘዋወርበት ቀጫጭን ቧንቧ። 2. ዋና፣ በጣም አስፈላጊ ነገር። *ቡና ለአገሪቱ ኢኮኖሚ የደም ስር ነው።*

**የደም አይነት** ስ በሰዎች ደም ንጥረ ነገርና አይነት መካከል ያለውን ልዩነት መሰረት በማድረግ የተከፋፈሉት የደም አይነቶች፣ የደም አይነቶቹም ኤቢ፥ ኤ፣ ቢ እና ኦ ናቸው።

**የደም ገንቦ** ደማም፡ ቆንጆ፡ ውብ (ለሴት)።

**የደም ጋን** ስ በሽንጥና በዳሌ መገጣጠሚያ አካባቢ ያለ የሰውነት ክፍል።

**ደመኛ (ደበኛ)** ቅ ጠላት፥ ባላጋራ።

**ደማም** ቅ የደስ ደስ ያለው፥ ውብ (ሰው)።

**ተዳማ** ግ ደም ተፋሰሰ።

**አዳማ** ግ ደም አፋሰሰ።

**ደማሚት (ድማሚት)** ስ ተራራ ለመፈንቀል፥ የማእድን ጉድጓድ ለመቆፈር፡… የሚያገለግል ሃይለኛ ፈንጂ።

**ደማም "ደማ"** ስር ተመ.

**ደማቅ "ደመቀ"** ስር ተመ.

**ደም "ደማ"** ስር ተመ.

**ደምበኛ "ደነባ"** ስር **"ደንበኛ"** ን ተመ.

**ደምበጃን(ደንበጃን)** ስ የተለያየ መጠን ያለውና ብዙ ፈሳሽ ሊይዝ የሚችል በጣም ትልቅ የሆነ ጠርሙስ።

**ደምባራ "ደነበረ"** ስር **"ደንባራ"**ን ተመ.

**ደምብ "ደነባ"** ስር **"ደንብ"** ን ተመ.

**ደሞዝ "ደመወዝ"** ን ተመ.

**ደረመሰ** ግ ጠረመሰ፡ ናደ፡ አፈረሰ።

**ድርምስ አለ** ግ ተደረመሰ።

**ተደረመሰ** ተጠረመሰ፡ ተናደ፥ ፈረሰ።

**ደረመን** ስ 1. እከክ፡ ፎከት። 2. የቁምጥና በሽታ።

**ደረመናም** ቅ 1. (ስድብ) እከካም፡ ፎከታም። 2. የቁምጥና በሽታ የያዘው።

**ደረሰ**[1] ግ 1.ቀረበ፣ ተጠጋ። 2. መጣ፡ ከች አለ። *በጧት ደረሱ፡* 3. ሄደ። *ሃኪም ቤት ደርሶ መጣ፡* 4. ገባ። *መንገደኛው በሶስት ሰአት ደሴ ደረሰ፡* 5. በቃ። *ልጁ ለወግ ደረሰ።* 6. አደገ፡ ጎለመሰ። *ቤቴን የሚጠብቅ የደረሰ ልጅ አለኝ።* 7. ሆነ፡ ተፈፀመ። *ንግርቱ ደረሰ። 8.* ዝግጁ ሆነ (ለመበላት፡ ለመታጨድ፡ ለመጠጣት፡ ለመሰብሰብ፡…)።

**ደረሰለት** 1. መጣለት፡ ተገኘለት፡…። 2. አለቀለት፡ ተጠናቀቀለት (ስራ)።

**ደረሰበት** 1. አገኘው፡ አጋጠመው። *መከራ ደረሰበት።* 2. ተተናኮለው፥ ነገር ፈለገው። 3. ተጠጋው፥ ቀረበው።

**ደረሰባት** በግብረ ስጋ ተገናኛት።

**ደረሰው** አገኘ፥ ተረከበ፡ ወሰደ። *ሎተሪ ደረሰው፡*

**አያድርስ** አያምጣው፡ አይጣል (ክፉን ነገር)።

**መድረሻ** ስ 1. መግቢያ፡ መጠጊያ፡ 2. አንድ ነገር ከአንድ ቦታ ተነስቶ ሂደቱን የሚያቆምበት፥

የሚያርፍበት ቦታ።

**መድረሻ ቢስ** መጠጊያ የሌለው።

**ደረሰኝ** ስ አንድ ግለሰብ ወይም ድርጅት አንድን እቃ ወይም ገንዘብ ከአንድ ድርጅት ወይም ግለሰብ መረከቡን የሚያረጋግጥበትና ለአስረካቢው የሚሰጠው የፅሁፍ ማስረጃ።

**ደራሽ ውሃ** ስ ድንገተኛ የውሃ ሙላት።

**ደርሶ** ያለምክንያት ዝም ብሎ። *ደርሶ መታኝ*።

**ደርሶ መልስ**፣ውሎ ገብ። 2፣ከሄዱበት ቦታ ሳይሰነበቱ ፈጥኖ መመለስ

**ደርሶ መልስ ቲኬት** ስ ወደ አንድ ቦታ ለመሄጃና ለመመለሻ የሚያገለግል የመጓጓዣ ቲኬት።

**-ድረስ** መዋ የቦታን፥ የጊዜንና የሃሳብን የተወሰነ መድረሻ፥ ልክ ለመግለፅ የሚያገለግል መስተዋድዳዊ ምእላድ። *ከአዲስ አበባ ደሴ ድረስ/ማታ ድረስ/ እስከዚህ ድረስ አትጨነቅ።*

**ድራሽ** ቅ 1. አድራሻ፥ የደረሰበት፥ የሄደበት። *ሰውየው ድራሹ ጠፋ።* 2. ድምጥማጥ፥ ማንነት። *ድራሽህ ይጠፋ!*

**ድራሹ ጠፋ** ያለበት፥ የሚገኝበት የማይታወቅ ሆነ፥ ደብዛው የለም፥ ያለበት አልታወቀም።

**ድርስ** ስ 1.ለመወለድ የተቃረበች ሴት። 2. ያሬዳዊ የዜማ ምልክት።

**ድርሱን** ቁርጡን፥ የመጨረሻውን (ለዋጋ)። *ድርሱን ንገረኝ።*

**ድርስ እርጉዝ** ቅ ለመውለድ ጊዜዋ የደረሰ።

**ድርስ ጥርስ** ስ የመነቀያው ጊዜ በመድረሱ ሊነቀል የተቃረበ ጥርስ።

**ድርሻ** ስ እድል፥ ፋንታ፥ እጣ። *ድርሻውን ወሰደ።*

**ተደረሰ** ግ 1.ተቀረበ፥ መጠጋት ተቻለ። *እዚያ መቼ ተደረሰና ነው?* 2. ሆነ፥ ተደረገ። ስምምነት ላይ ተደረሰ። 3. ተገባ፥ መገኘት ተቻለ። *ልክ በሁለት ሰአት ከተባለው ቦታ ተደረሰ።* 4. ተበቃ።*ለዚህም ተደረሰ እንዴ?*

**ተዳረሰ** ግ 1. ለሁሉም በቃ። ወረቀቱ ለሁሉም ተዳረሰ። 2. ተገባደደ፥ ቀረበ፥ ተጠጋ። *ጊዜው ተዳርሷል*። 3. ተሰራጨ፥ ተናኘ። *ወሬው በአንዴ ተዳረሰ።* 4. ተነካካ፥ ተገናኘ፥ ተጣላ። *በምን ተዳረሱ?* 5. ሊስማማ ቀቃረበ(በዋጋ)።

**መዳረሻ** ስ 1. መቃረቢያ፥ መድረሻ። 2. መቆያ (ምግብ)።

**አደረሰ** ግ 1. አቀረበ፥ አስጠጋ ። 2. አመጣ። *ሰውዬው እዚህ አድርሰኝ ተመለሱ*። 3. ወሰደ። *ቧት በመኪና አደረሰች*። 4. አበቃ። *በሽታው ለሞት አደረሰው*። 5. *ፈፀመ*፥ አጠናቀቀ፥ አገባደደ። *የልቡን አደረሱ*። 6. አስከተለ። *ጎርፉ ከፍተኛ ጉዳት አደረሱ*። 7. ሰውነቱ ሞላ፥ አደገ፥ ጎለመሰ። *አካለ መጠን አደረሱ*። 8. ለአካለ መጠን፥ ለሙሉ ሰውነት አበቃ። *ወንድ ልጅ አደረሱ*።

**አድርሰናል** ቀደም ብሎ ለመጣ ለማኝ ወይም ለጨፋሪ ሰጥተናልና አትቁም፥ የምንሰጥህ የለንም ለማለት ክበር ለቆመ ለማኝ ወይም ለጨፋሪ የሚነገር ቃል።

**አድራሻ** ስ 1. አንድ ሰው ወይም አንድ ነገር በጊዜያዊነት ወይም በቋሚነት የሚገኝበት፥ የሚኖርበት የተወሰነ ቦታ። 2. አንድ ደብዳቤ ወይም እቃ የትና ለማን መሰጠት እንዳለበት የሚያመለክት፥ በደብዳቤው ወይም በእቃው ላይ የሚሰፍር፥ የፅሁፍ መግለጫ።

**አድራሻውን አጠፋ** የሚኖርበት፥ የሚገኝበት ቦታ እንዳይታወቅ አደረገ።

**አደራረሰ** ግ አነካካ፥ አጣላ። *ምን አደራረሳችው*።

**አዳረሰ** ግ 1. ለሁሉም በስፋው ሰጠ፥ ናኘ። 2. ሁሉም ዘንድ እንዲደርስ አደረገ (ወሬ)። 3.ለሁሉም በማብቃቃት ሰጠ። 4. ለሁሉም ደረሰ፥ በቃ። 5. አገባደደ፥ ለፍፃሜ አቃረበ። 6.አነካካ፥ አጣላ።

**አዳራሽ** ስ በአንድ ጊዜ ብዙ ሰው ሊይዝ የሚችል ሰፊ የሆነ ቤት ወይም የቤት አንድ ክፍል። 2 ሰፊ።

**ደረሰ[2]** ግ ድርሰት አዘጋጀ፥ ፃፈ።

**ደራሲ** ስ ድርሰት አዘጋጅ፥ ፀሃፊ።

**ድርሰት** ስ 1. በስድ ንባብ፥ በግጥም፥ በቅኔ፥... መልክ የሚዘጋጅ ስነፅሁፍ። 2. (ኢ.ኦ.ተ.ቤ.) መፅሃፍ ቅዱስን ሳይጨምር በድርሳን፥ በገድል፥ በታምር፥... መልክ የተዘጋጀ የቤተክርስቲያን መፅሃፍ።

**ድርሳን**(ብ.ቁ.**ድርሳናት**) ስ ስለመላእክት፥ ስለቅዱሳን፥... የተደረሰ መንፈሳዊ መፅሃፍ። *ድርሳነ ሚካኤል*።

**አደራረስ** ስ (ኢ.ኦ.ተ.ቤ .) በታላቅ በአል ጊዜ ብቻ የሚዘመር ያሬዳዊ የዜማ ድርሰትና ስርአተ ማህሌት።

**ደረሰኝ** "ደረሰ[1]" ስር ተመ.

**ደረቀ** ግ 1 እርጥበት አጣ፥ ከሸለለ። 2 (ዘይ.) ሃሳበ ግትር ሆነ።

**ደረቅ** ስ 1 እርጥበት፥ ልምላሜ የሌለው። 2 (ዘይ.) ከቻቻ፥ ለዛቢስ፥ እፍረተቢስ።

**በደረቁ** ተው.ግ. ያለምንም ማዋዣ (እህል ውሃ)። *በደረቁ ያደከመኛል* ።

**በደረቁ ሳጨ** አታለለ፥ ሸነገለ።

**በደረቅ አፉ** ምንም ሳይበላ፥ ሳይቀምስ።

**ደረቅ ሌሊት** ስ ውድቅት።

**ደረቅ ምች** ስ ሃይለኛ ምች፣ ከፀሃይ ሙቀት የተነሳ የሚመጣ ህመም።

**ደረቅ ሳል** ስ አክታ የሌለው ሳል።

**ደረቅ ስንቅ** ስ እንደኮቸሮ፣ በሶ፣ ቋንጣ ያለ ለብዙ ጊዜ ሳይበላሽ የሚቆይ ምግብ።

**ደረቅ ትንቢት** ስ መልእክቱ ስውርነት የሌለው፣ ግልፅ የሆነ ትንቢት ወይም ንግር።

**ደረቅ እርሳስ** ስ ቀለምነት የሌለውና (ኮፒ እርሳስ ያልሆነ) ለመፃፊያ የሚያገለግል እርሳስ።

**ደረቅ እንጀራ** ስ ወጥ የሌለው እንጀራ።

**ደረቅ ወንዝ** ስ ውሃ የሌለው ወንዝ።

**ደረቅ ወዝ** ስ ፎረፎር።

**ደረቅ ጉንፋን** ስ አክታ የሌለው ጉንፋን።

**ደረቅ ግንባር** እድለቢስ።

**ደረቅ ጠጅ** ስ የበሰለ ወይም የቆየ ጠጅ ።

**ደረቅ ጣቢያ** ስ ለተሳፋሪ ምንም የሚበላ የሚጠጣ የሌለበት የባቡር ጣቢያ።

**ደረቅ ጦር** ስ የጦር መሳሪያ ያልያዘ ዘማች።

**ደረቅ ጭነት** ስ ፈሳሽ ነክ ያልሆነ የጭነት አይነት ።

**ደረቆት** ስ ገብስ ወይም በቆሎ ተቀቅሎ ወይም በውሃ በደምብ ርሶ ከተቆላ በሗላ ተፈጭቶ የሚዘጋጅ የጠላ እህል።

**ደራቂቻ** ቅ 1. ከሲታ፣ ጠሚጋ። 2.እርጥብነት፣ ልምላሜ የሌለው።

**ደራቃ** ዝ.ከ.

**ድርቅ** ስ ዝናም የጠፋበት ወቅት፣ ጊዜ።

**ድርቅ መታው** ዝናብ አጣ፣ በና ሆነ።

**ድርቅ ገብቷል** በዝናብ መታጣት ምክንያት ረሃብ፣ ችግር ገብቷል።

**ድርቄ** ስ ጌጥ ያልተሰራለት ወይም በባህር አረብ ያልተሸለመ ሰገባ፣ አፎት።

**ድርቀት** ስ 1. እርጥበት አልባነት። 2. የሆድ ወይም የአንጀት ልስላሴ ማጣት የሚያስከትለው ህመም። 3 (ዘይ.) ከንቱ መፈጨፈጨህ፣ ውጤት ለሌለው ነገር መለፍለፍ።

**ድርቅና** ስ ለባቢነት፥ ችኮነት፥ አይን አውጣነት።

**ድርቆሽ** ስ 1.ታጭዶ የደረቀ ሳር። 2. ሆን ተብሎ እንዲደርቅ የተደረገ እንጀራ (የተወቀጠ ወይም ያልተወቀጠ)።

**ድርቅ አለ** ግ በጣም ደረቀ።

**ተዳረቀ** ግ 1. (ዘይ.) ተነታረከ፥ ተጨቃጨሀ፥ ተለፋለፈ፥ ተጨቃጨቀ። 2. ተሰላቸ፥ ታከተ (በነገር፥ በጭቅጭቅ)።

**አደረቀ** ግ (ዘይ.) አሰለቸ፥ አታከተ (በነገር፥ በጭቅጭቅ)።

**አድርቅ (ልብ አድርቅ)** ቅ 1. ነዝናዛ፥ ጨቅጫቃ። 2. በተደጋጋሚ ቢነገረውም፥ ቢመከርም ለውጥ የማያሳይ፥ የሚነገረውን ተግባራዊ የማያደርግ፣ ልብ አውልቅ።

**ደረበ** ግ 1. አንዱን በሌላው ላይ አደረገ፥ ጨመረ፥ ጫነ፥ አነባበረ። 2. በለበሰው ልብስ ላይ ሌላ ልብስ ጨምሮ ለበሰ። 3. ጨመረ፥ ደአከለ። *ይህ ቃል ሌላ ፍች ደርቦ ይዟል።*

**መደረቢያ (ድራብ)** ቅ እንደኩታ፥ ቡሉኮ ወዘተ. ያለና ከልብስ በላይ የሚለበስ ልብስ።

**ደርብ** ስ በድሮ ጊዜ የሚሰራ ባለአንድ ፎቅ ቤት።

**ድርብ** ቅ 1. እጥፍ ። 2. የተደረበ። 3. ስ ሰፊ ጥበብ ያለውና የማእረግ ልብስ የሆነ ኩታ (ጥንድ ድርብም ይባላል)። 4. የሸማ ጥበብ አሰራር አይነት።

**ድርብ ሰረዝ** ስ ከስርአተ ምልክቶች አንዱ ምልክቱም (፤) ነው።

**ድርብ ቃል** ስ ጥምር ቃል።

**ድርብ ታቦት** ስ በአንድ ቤተክርስቲያን ውስጥ በደባልነት የሚገኝ ሌላ ታቦት፤ ደባል ታቦትም ይባላል።

**ድርብ ትርጓሜ** ስ አንድምታ።

**ድርብ ዜማ** ስ ንባቡ አንድ አይነት ሆኖ ዜማ ወይም ምልክቱ ከአንድ በላይ የሆነ።

**ድርብ ጃኖ** ስ የጥለቱ ጻርና ጻር በድርብ ጥበብ አሰራር የተከበበ ጃኖ።

**ድርብ ጥርስ** ስ በጥርስ ላይ ተደርቦ የሚወጣ ጥርስ።

**ተደረበ** ግ 1. በእግር ኳስ ጨዋታ ላይ የተመታችን ኳስ አቅጣጫዋን እንድትስት አደረገ። 2. አበረ፥ አገዘ። *ተደርቦ መታው።*

**ተደራቢ** ቅ ተጨማሪ።

**ተደራረበ** ግ 1. አንዱ በሌላው ላይ ሆነ፥ ተነባበረ። 2. ተጨማመረ፥ በላይ በላዩ ሆነ።

**ተደራራቢ** ቅ ተደጋጋሚ፥ አንዱ በሌላው ላይ የመጣ፥ የሆነ፥ የተደረገ።

**አደራረበ** ግ አንዱን በሌላው ላይ አደረገ፥ ጫነ፥ አነባበረ።

***ደረበበ**

**ደርባባ** ቅ 1. ሰውነቱ ወፈር፥ ደልደል ያለ (ሰው)። 2. ረጋ ያለ፥ ጭምት፥ ዝምተኛ።

**ድርበብ** ስ የመስፈሪያውን እቃ (ቀና፥...) እስከ አፉ ድረስ ብቻ የሚሞላ የጥራ ጥሬ ወይም የደረቅ ነገር የአሰፋፈር አይነት፤ ተቆልሎ ያልተሰፈረ።

**በድርበቡ** በልኩ፥ በመጠኑ፥ እንደነገሩ።

ፍቅራችን በድርበቡ ነው።

**ተንደረበበ** ግ 1. እስከመስፈሪያው እቃ አፍ ድረስ ብቻ ሞላ፥ ተሰፈረ። 2. ጨመተ፥ ዝም አለ።

**አንደረበበ** ግ እስከመስፈሪያው እቃ አፍ ድረስ ብቻ አስተካክሎ ሰፈረ።

**ደረባ** ስ በጣሪያ መልክ የተዘጋጀ የጎተራ ክዳን።

**ደረ̈ባ** ግ ናደ፥ አፈለሰ፥ አፈረሰ።

**ደረተ** ግ 1. አንድን ጨርቅ በሌላው ላይ እየደረበ መሳልሶ ሰፋ። 2. ደራረበ።

**ድሪቶ** ስ 1. ተደራርቦ ብዙ ቦታ ላይ የተሰፋ አሮጌ ጨርቅ። 2. የተቀዳደደና ቡትቶ የሆነ ልብስ። 3. (ዘይ.) የተደጋገመ (ሃሳብ)። 4. (ስድብ) ፊቱ ላይ ጠቃጠቆ (ጠባሳ) የበዛበት (ሰው)።

**ድሪቷም** ቅ 1.(ስድብ) ድሪቶ ለባሽ። 2. ደሃ።

**ድርት** ቅ ተደራርቦ የተሰፋ፥ ቡትቶ።

**ደረት** ስ 1. በስተፊት በኩል ከአንገት በታች ከሆድ በላይ ያለ የሰውነት ክፍል። 2. ያሬዳዊ የዜማ ምልክት/ ᐟ/።

**ደረቱን ገልብጦ** ያለፍርሃት፥ በትእቢት።

**ደረቷን ደቃች** ደረቷን መታች (በልቅሶ ጊዜ)።

**ደረቷን ጣለች** በሃዘን ምክንያት ደረቷን አራቁታ ሃዘኗን ገለፀች።

***ደረከከ**

**ደረከከ (ደርካካ)** ቅ አጭር ወፍራም።

**ድርክክ አለ** ግ 1. በጣም በሰለ (ፍሬ)። 2. ፋመ፥ ፍም ወረደው (እሳት)። 3. አጭርና ወፍራም ሆነ።

**ተንደረከከ** ግ 1. አጭርና ወፍራም ሆነ።2. በጣም በሰለ፥ ጎመራ (ፍሬ)። 3. በጣም ፋመ፥ ፍሙ መረተ (እሳት)። 4. ቀስ ብሎ በአጭር ተራመደ (አጭር ወፍራም ሰው)።

**አንደረከከ** ግ 1. አጭርና ወፍራም አደረገ። 2. አበሰለ (ፍሬን) ። 3. ፍም እንዲወጣው፥ እንዲወርደው አደረገ።

**ደረዘ** ግ 1. ለጎመ፥ ከፈፈ (ሰፌድን፥ መሶብን፥...)። 2. አንዴ በተሰፋው የስፌት መስመር አስጠግቶ እንደ ገና ሰፋ፥ ደርዝ አበጀ።

**ደርዝ** ስ 1. ክፈፍ (የሰፌድ፥ የመሶብ፥...)። 2.ስፌት ተደጋግሞ የሄደበት የልብስ ዳርቻ።

**ደርዝ ያለው ንግግር** ውል፥ መልክ፥ ጭብጥ፥... ያለው ንግግር።

**ደርዘኛ** ቅ 1. አነጋገር አዋቂ። 2. እምነተ ጠባቃ።

**ደረደረ** ግ 1 በተራ፥ በረድፍ አደረገ፥ ሰደረ፥ ኮለኮለ፥ አሰለፈ። 2. አነባበረ፥ ቆለለ፥ ከመረ። 3.ሃሳብን አንድ ባንድ ገለፀ፥ አሰማ። *ግጥም ደረደረ/ሰበብ ደረደረ።* 4.መታ፥ ገረፈ፥ *ነዘረ(በገናን)* ።

**መደርደሪያ** ስ ከእንጨት፥ ከብረት፥... በተለያየ መጠንና ቅርፅ የሚሰራና ልዩ ልዩ እቃዎችን በረድፍ ለማስቀመጥ የሚያገለግል እቃ። *መፃህፍት መደርደሪያ/እቃ መደርደሪያ።*

**ድርድር** ስ በረድፍ የተቀመጠ እቃ።

**ድርድ̈ር** ስ አንድን ነገር ወይም ሁኔታ አስመልክቶ ስምምነት ላይ ለመድረስ የሚደረግ፥ ውይይት።

**ተደረደረ** ግ በረድፍ፥ በተራ ተሰደረ፥ ተኮለኮለ።

**ተደራደረ** ግ ተዋዋለ፥ ተስማማ፥ ተነጋገረ (እንደዚህ ይሁን ወይም አይሁንም፥ እንደዚያ ነው ወይም አይደለም እየተባባለ በመከራከር)።

**ተደራዳሪ** ቅ 1. ውል ተዋዋይ። 2. አንድን ጉዳይ አስመልክቶ ከሌላ ወገን ጋር እንዲነጋገር፥ እንዲከራከርና ስምምነት እንዲያደርግ ውክልና የተሰጠው (ሰው)።

**አደራደረ** ግ አዋዋለ፥ አስማማ።

**አደራዳሪ** ስ አዋዋይ፥ አስማሚ።

***ደረደረ**


**ተንደረደረ** ግ 1. ከከፍተኛ ወደ ዝቅተኛ ቦታ ሮጠ። 2. ተፈተለከ፥ በሃይል ሮጠ።

**መንደርደሪያ** ስ 1. ለመሮጥ አመቺ የሆነና ተዳፋትነት ያለው ቦታ። 2. መነሻ፥ መጀመሪያ (የሃሳብ)። 3. ለማረፍ ወይም ለመነሳት የሚያገለግል ማኮብኮቢያ (ለአውሮፕላን)።

**አንደረደረ** ግ አሮጠ።

**ደረጀ** ግ 1. ጠና፥ ጠነከረ። 2. ተደላደለ፥ ሀብት ያዘ፥ ንብረት አበጀ።

**ደረጃ** ስ 1. ለመውጫና ለመውረጃ የሚያገለግል እርከን (በአብዛኛው ለፎቅ ቤቶችና ከፍታ ላይ ለሚገኙ ቦታዎች)። 2. ማእረግ (የትምህርት፥ የሹመት፥...)። 3. ቅደም ተከተል። *ጉዳዩን ደረጃ በደረጃ እናየዋለን።* 4. ጥራት። *ለውጭ ገበያ የሚቀርበው ቡና ደረጃው ከፍ ያለ ነው።* 5. አቅም፥ ችሎታ። *የሶስተኛው አለም ህዝብ የኑሮ ደረጃ ዝቅተኛ ነው።* 6. ክብር፥ ልክ። ደረጃህን ጠብቅ።



*ደረጃ 1ኛ ፍቺ*

**ድርጅት** ስ 1. የተወሰነ የስራ አይነት የሚካሄድበት ወይም የሚከናወንበት የስራ ተቋም (ፋብሪካ፥ ሆቴል፥...)። 2. ዝግጅት። 3. የተወሰነ አላማን ለማራመድ ሰዎች በአባልነት የሚሰበሰቡበት ማእከል፥ ማህበር፥...።

**ተደረጃጀ** ግ ተዘገጃጀ፥ ተሰነዳዳ።

**ተደራጀ** ግ 1. ተጠናከረ፥ ተደላደለ። 2. ተዘጋጀ፥ ተሰናዳ። 3. ተሰባሰበ፥ አባል ሆነ (በፖለቲካ ድርጅት፥ በሙያ ማህበራት፥ ...)።

**አደረጀ** ግ አጠና፥ አጠነከረ፥ አጎለበተ።

**አደራጀ** ግ 1. አዘጋጀ። 2. ሰዎች በፖለቲካ ድርጅት፥ በማህበር፥... እንዲሰባሰቡ አደረገ።

***ደረገ**

**ድርጊት** ስ ተግባር፥ ስራ፥ ክንውን።

**ተደረገ** ግ 1. ተከናወነ። 2. ተፈፀመ፥ ተሰራ። 3. ሆነ።

**ተደራጊ** ቅ (ሰዋ.) የድርጊት ተቀባይነትን የሚያመለክት (ግስ፥ ቅፅል)።

**ተደራራጊ** ቅ (ሰዋ.) እርስበርስ አንዱ በሌላው ላይ ድርጊት መፈፀሙን የሚያመለክት (ግስ፥ ቅፅል)።

**ተደራጊ** ዝ.ከ.

**አደረገ** ግ 1. አከናወነ፥ ፈፀመ፥ ሰራ። 2.አኖረ፥ አስቀመጠ። *ደብተሩን ጠረጴዛ ላይ አደረገ*። 3. ለበሰ፥ አጠለቀ፥... (ልብስን፥ ሰአትን ጫማን፥...)።

**ቁርስ አደረገ** በላ፥ ተመገበ፥...።

**አድራጊ** ቅ (ሰዋ.) 1. ድርጊት ፈፃሚነትን የሚያመለክት (ግስ .ቅፅል)። 2. ፈፃሚ፥ አከናዋኝ።

**አድራጊ ፈጣሪ** ሁሉን ነገር የሚያደርግ፥ ምንም የማይሳነው፥ አዛዥ።

**አደረገ** ግ 1. በድርጊት፥ በስራ አገዘ፥ ረዳ። 2. አገናኘ (በጋራ እንዲሰሩ)።

**አደራራጊ** (ሰዋ.) 1. የድርጊት አጋዥነትን የሚያመለክት (ግስ፥ ቅፅል)። 2. ሁለት ነገሮች እርስ በርስ አንዱ በሌላው ላይ አንድ ድርጊት እንዲፈፅምበት ማስደረጉን የሚያመለክት (ግስ፥ ቅፅል)።

**አዳረገ** ግ አደራረገ።

**አዳራጊ** ቅ አደራራጊ።

**አስደረገ** ግ 1. አሰራ፥ አሰበጀ። 2. አስፈፀመ (አንድን ድርጊት) ።

**አስደራጊ** ቅ (ሰዋ.) ለአንድ ድርጊት መፈፀም ምክንያት መሆኑን የሚያመለክት (ግስ፥ ቅፅል)።

**ደረገመ** ግ 1. አጠፋ፥ እልም አደረገ (መብራትን፥ አይንን፥...)። 2. በሃይል ዘጋ (መዝጊያን)። 3. *መታ* (በጥፊ)። 4. (ዘይ.) ከሚፈለገው በላይ ጨመረ። *ወጡ ውስጥ ጨው ደረገመችበት*።

**ተደረገመ** ግ 1. ጠፋ፥ እልም አለ። 2. በሃይል ተዘጋ።

***ደረፎጠ**

**ድርፏጫ(ድርፋጭ)** ቅ አጭርና ጎነ ሰፊ የሆነ።

**ድርፋጭ አለ** ግ ደርፏጫ ሆነ።

**ድርፋጭ አደረገ** ግ ደርፏጫ አደረገ ።

**ደራ[1]** ግ ዘበጠ፥ ተለመጠ።

**ድራት** ስ ዝብጠት፥ ለማጣነት።

**ደራ[2]** ግ 1. ጋለ፥ ሰማ(ምጣድ)። 2. ሞቀ፥ ደመቀ (ገበያ፥ ጨዋታ)።

***ደራ[1]**

**ደራች** ግ የግብረ ስጋ ግንኙነት ፈለገች (ለእንስሳ)።

**ድሪያ(ድሪ)** ስ ለፍቅር የሚፈላለጉ ሴትና ወንድ የሚያደርጉት ልፊያ፥ ጨዋታ።

**ተዳራ** ግ ተላፋ፥ ተቃበጠ።

***ደራ[2]**

**ድር** ስ ዘሃ፥ ቀጭንና ጠንካራ የሆነ ፈትል ።

**ድርና ማግ ሆኑ** የግብረ ስጋ ግንኙነት አደረጉ፥ መርፌና ክር ሆኑ።

**ተደራ** ግ ተተረተረ፥ ተዘረጋ(ድር፥...)።

**አደራ** ግ ተረተረ፥ ዘረጋ (ድርን፥...)

**ደራሲ** "**ደረሰ[2]**" ስር ተመ.

**ደራሽ** "**ደረሰ[1]**" ስር ተመ.

**ደራቁቻ** "**ደረቀ**" ስር ተመ.

**ደራች** "***ደራ[1]**" ስር ተመ.

**ደራጎን** ስ በጥንታዊ ታሪኮች ውስጥ የሚጠቀስ (አብዛኛውን ጊዜ ክንፍ ያለው እሳት የሚተፋ፥ አጫጭር እግሮች ያሉት) ዘንዶ መሰል አውሬ።



*ደራጎን*

**ደሬ** ስ በቆላ የሚገኝ፥ እንጨቱ ጠንካራ የሆነ የዛፍ አይነት ።

**ደርበት** ስ ሁለት እንስራ ያህል ውሃ ሊይዝ የሚችል የሸክላ እቃ።

**ደርባባ** "***ደረበበ**" ስር ተመ.

**ደርብ** "**ደረበ**" ስር ተመ.

**ደርካካ** "*ደረከከ" ስር "ደረከከ" ን ተመ.
**ደርዘን** ስ ብዛቱ 12 የሆነ ተመሳሳይ እቃ።
**ደርገ** "ደረዘ" ስር ተመ.
**ደርግ** ስ ኮሚቴ።
**ደርፏጫ** "ደረፎጨ" ስር ተመ.
**ደሰመ** ግ ገጨ፥ ለተመ፥ መታ።
**ደሰሰ** ግ ዘመመ፥ ዘንባላ ሆነ።
**ደሳሳ** ቅ ያዘመመ፥ ያጎነበሰ (ጎጆ)።
**ተንዳሰሰ** ግ ደሳሳ ሆነ።
***ደሰሰ**
**ተንዳሰሰ** ግ አዘገመ፥ ተንቆረሰሰ።
**አንዳሰሰ** ግ አንቆረሰሰ፥ በዝግታ አስኬደ።
**ደሰቀ** ግ 1. መታ፥ ደቃ (በክርን፥ በጡጫ)። 2. ተጫጫነ፥ ደበተ (እንቅልፍ)።
**ደሰቅ** ስ የሚደብት፥ የሚጫጫን እንቅልፍ።
**ደሰቃም** ቅ የሚያስፈራ፥ የሚቀፍ፥ የሚደብት በታ።
***ደሰተ**
**ደስታ** ስ ፍስሃ፥ ሃሴት፣ ፈንጠዝያ የሞላበት ወይም ሃዘን፥ ትካዜ፥... የሌለበት ሁኔታ።
**በደስታ ሰከረ** በጣም ተደሰተ።
**በደስታ ዋኘ** በጣም ተደሰተ።
**ደስተኛ** ቅ 1. በአንድ ነገር ወይም ድርጊት የተደሰተ። 2 በአኗኗሩ፥ በህይወቱ ርካታ ያገኘ፥ ብዙ ጊዜ የሃዘን ስሜት የማይታይበት።
**ደስ አለ** ግ ቆንጆ፥ ማራኪ፥ አስደሳች፥... ሆነ።
**ደስ አለው** ግ ተደሰተ።
**ደስ የሚል** ቅ ቆንጆ፥ ማራኪ፥ አስደሳች።
**ደስ አሰኘ** ግ አስደሰተ።
**ደስ ደስ አለው** ግ ተደሰተ።
**የደስ ደስ** የተገኘውን ደስታ ምክንያት በማድረግ የሚደረግ ግብዣ ወይም ስጦታ።
**የደስደስ ያለው** 1. ቆንጆ፥ ውብ፥ ማራኪ የሆነ። 2. ደስታ የተሰማው፥ በደስታ የተሞላ።
**ተደሰተ** ግ ደስታ ተሰማው፥ ፈነደቀ።
**ተደሳች** ቅ ህይወት የፈካችለት፣ ችግር፥ ጭንቀት፥ ብስጭት፥ ሃዘን፥ ትካዜ፥... የማይታይበት።
**አስደሰተ** ግ ደስታ እንዲሰማው፥ እንዲያገኝ አደረገ።
**አስደሳች** ቅ ውብ፥ ማራኪ፣ ደስታ የሚሰጥ።
**ደሳሳ** "ደሰሰ[1]" ስር ተመ.
**ደሴት** ስ በውሃ (በባህር) የተከበበ መሬት ።
**ደስቃም** "ደሰቀ" ስር ተመ.
**ደስቅ** ዝ.ከ.
**ደስተኛ** "*ደሰተ" ስር ተመ.
**ደስታ[1]** ዝ.ከ.
**ደስታ[2]** ስ 1. የከብት በሽታ አይነት። 2. በቆሎ የምትለቅ የኩፍኝ በሽታ አይነት።
***ደሸደሸ**
**አደሸደሸ** ግ አዘጠዘጠ፥ አደዘደዘ፥ አውደለደለ።
**አደሽዳሽ** ቅ(ስድብ) አዘጥዛጭ፥ አውደልዳይ።
**ደቀለ** ግ ዲቃላ ወለደ።
**ዲቃላ** ስ 1. ከጋብቻ ውጭ የተወለደ ልጅ። 2. የተለያየ ዘር፥ ቀለም ካላቸው ሰዎች የተወለደ ልጅ (ለምሳሌ ጥቁር ከነጭ) 3. መጢቃ፣ ክልስ። 4. (ዘይ.) የተለየ፥ የማይገጥም።
**ተደቀለ** ግ ከጋብቻ ውጪ ተወለደ።
**ተዳቀለ** ግ 1. ተዛመደ (በመውለድ)። 2. ከሁለት የተለያዩ ዘሮች ተፈጠረ፥ ተወለደ (ለአዝርእት፥ ለእፀዋት፥ ለእንስሳት፥...) ።
**አዳቀለ** ግ ሁለት የተለያዩ ዘሮችን በማገናኘት ለየት ያለ ዘር እንዲፈጠር አደረገ።
**ደቀመዝሙር**(ብ.ቁ.ደቀመዛሙርት) ስ 1. (ቤ.ክ.) ተማሪ። 2. የአላማ ተከታይ።
**ደቀቀ** ግ 1. ለዘበ፥ ላመ፥ 2. ተሰበረ፥ ነከተ፥ መሸከ። 3. ትናንሽ ሆነ፥ ረቀቀ (ዕሁፍ፥...)። 4.ጫጨ፥ ቆረቆዘ። 5. (ዘይ.) ደከመ፥ ዛለ። *ሰውነቱ ደቀቀ*።
**ደቂቃ** ስ የአንድ ሰአት 1/60ኛ የሆነ የጊዜ ክፍልፋይ።
**ደቂቅ** ቅ 1. በጣም ትንሽ፥ ለአይን ጎልቶ የማይታይ። ስ 2. ልጅ። *ከሊቅ እስከ ደቂቅ* ።
**ደቃቃ** ቅ 1. በጣም ትናንሽ የሆነ። 2. (ዘይ.) ደካማ፥ አቅመቢስ።
**ደቃቅ** ቅ 1. ልም፥ ልዝብ፥ የተሰለቀ። 2. በጣም ጥቃቅን የሆነ።
**ድቃቂ** ቅ ስብርባሪ፥ ንኩትኳች።
**ተዳቀቀ** ግ ተዳከመ፥ አቅም አጣ።
**አደቀቀ** ግ 1. ፈጨ፥ አለዘበ፥ አላመ። 2. ሰባበረ፥ አመሸከ። 3. አደከመ፥ አቅም አሳጣ። 4. አቀጨጨ፥ አረቀቀ(ዕሁፍን)።
**ደቀነ** ግ 1. ከሚወርደው ወይም ከሚፈሰው ነገር ስር መቀበያ የሚሆን እቃ አስጠጋ፥ አስቀመጠ፥ ለገተ። *ከቧንቧው ስር ባልዲ ደቀነ*። 2. ጀመረ፥ ወጠነ። 3. ደገነ፥ አነጣጠረ፥ አለመ። 4. ጋረጠ።
**ድቅን** ጅምር፥ ውጥን።

**ተደቀነ** ግ ተጋረጠ:: እፊቴ እየተደቀነ አስቸገረኝ::

**ደቀደቀ** ግ 1. ጠቀጠቀ፥ ተመተመ:: 2. መታ፥ ደበደበ:: 3. ቆፈረ::

**መደቅደቂያ** ስ የጠመንጃን አፈሙዝ (ቧንቧውን) ለመጥረግ የሚያገለግል ቀጭን ብረት::

**ድቅድቅ** ቅ 1. የተጠቀጠቀ፥ ጥቅጥቅ:: 2. አንድ ጊዜ የታረሰ (መሬት):: 3. ቁፍር::

**ድቅድቅ ጨለማ** ድፍን ያለ፥ ምንም የማይታይበት ጨለማ::

***ደቀደቀ**

**ተንደቀደቀ** ግ 1. ደቅ፥ ደቅ የሚል ድምፅ ሰጠ፥ ተንበቀበቀ:: 2. የፉከራ ድምፅ አሰማ::

**አንደቀደቀ** ግ 1. ደቅ ደቅ የሚል ድምፅ እንዲሰጥ አደረገ፥ አንበቀበቀ:: 2. የፉከራ ድምፅ አሰማ::

**ደቂቃ** "ደ ቀቀ" ስር ተመ.

**ደቂቅ** ዝ.ከ.

**ደቃ** ግ መታ (በጡጫ፥ በከርን፥...)::

**ደቅ አለ** ግ ጓ፥ ደቅ የሚል ድምፅ አሰማ::

**ደቅ አደረገ** ግ ደቃ::

**ደቃቃ** "ደቀቀ" ስር ተመ.

**ደቃቅ** ዝ.ከ.

**ደቅ** ስ ከጣባ የሚበልጥ፥ ከዋዲያት የሚያንስ የሸክላ እቃ::

**ደቆሰ** ግ 1. በመደቆሻ አደቀቀ፥ አላመ:: 2. ጨፈለቀ:: 3. (ዘይ.) ደበደበ መታ::

**መደቆሻ** ስ 1.አነስተኛ የድንጋይ ወፍጮ:: 2. ለመደቆስ የሚያገለግል ጠፍጣፋ እንጨት::

**ድቁስ** ስ የበርበሬ ዱቄት::

**ተደቆሰ** ግ 1 ላመ፥ ደቀቀ:: 2 ዛለ፥ ደከመ::

**ተዳቆሰ** ግ ተማታ፥ ተደባደበ::

**ደበለ** ግ 1. ጨመረ፥ ደረበ:: 2. ቀየጠ፥ ደባለቀ፥ ቀላቀለ:: 3. ሸረበ፥ ጠመረ፥ በአንድነት ፈተለ (የተለያዩ ክሮችን፥...)::

**ደባል** ስ 1.የሌላ ሰው ይዞታ በሆነ ቤት ውስጥ ተደርቦ የሚኖር ሰው:: 2. በአንድ ቤተ ክርስቲያን በድርብነት የሚገኝ ታቦት:: ቅ 3. ተጨማሪ፥ ተቀፅላ፥ ተደራቢ፥ በፊት ያልነበረ:: *ደባል ባህርይ አወጣ::*

**ድብል** ስ ወፍራም ሸርብ ገመድ::

**ተዳበለ** ግ 1. ደባል ሆነ:: 2. አንድ ነገር ከሌላ ነገር ጋር ባንድ ላይ እንዲቀመጥ ተደረገ::

**አዳበለ** ግ 1. ከቤቱ ደባል አስቀመጠ:: 2. አንድን ነገር ከሌላ ነገር ጋር ባንድነት አስቀመጠ::

**ደበለለ**[1] ግ ጣለ፥ አንከባለለ::

**ተንደባለለ** ግ ተንከባለለ::

**አንደባለለ** ግ አንከባለለ::

**ደበለለ**[2] ግ አከበደ፥ ትልቅ አ ደረገ (ሸክምን)::

**ድብል** ቅ ትልቅ ሸክም::

**ተደበለለ** ግ ትልቅ ሸክም ተሸከመ::

**ደበለቀ** "ደባለቀ" ን ተመ.

***ደበለበለ (*ደቦለቦለ)**

**ድብልብል(ድቡልቡል)** ቅ 1. እንደአለሎ፥ እንደኳስ ያለ፥ ክብ፥ እንክብል:: 2. መላ አካሉ የወፈረ::

**ድብልብል(ድቡልቡል)አለ** ግ ተድበለበለ::

**ድብልብል(ድቡልቡል) አደረገ** ግ አድበለበለ::

**ተድበለበለ(ተድቦለቦለ)** ግ 1. ድብልብል ሆነ:: 2. ወፈረ (መላ አካሉ)::

**አድበለበለ(አድቦለቦለ)** ግ 1. ድብልብል አደረገ:: 2. አወፈረ (መላ አካሉን)::

**ደበላ** ስ እንደኛሸ፥ መጋረጃ፥... ሆኖ ሊያገለግል የሚችል ስስ የአቡጀዲ አይነት::

**ደበላለቀ** "ደባለቀ" ስር ተመ.



ደበሎ

**ደበሎ** ስ 1. ከነጠጉሩ ከተለፋ በኋላ በክብ ቅርፅ ተቀጣጥሎ የተሰፋ የቆሎ ተማሪዎች የሚለብሱት የበግ ቆዳ:: 2. ከነጠጉሩ ከተለፋ በኋላ በለምድ መልክ ትከሻ ላይ የሚለበስ የበግ ቆዳ::

**ደበረ**[1] ግ ደብር ወይም ገዳም አደረገ፥ የደብርነት ወይም የገዳምነት ማእረግ ሰጠ::

**ደብር(ብ.ቁ.አድባራት)** ስ 1. በአስተዳደር እርከን፥ በካህናት፥ በመፃህፍት፥ በመምህራንና በሃብት ብዛት አንፃር ማእረጉ ከገጠር ቤተክርስቲያን የላቀና እንደ መወድስ፥ ሰአታት፥ ማህሌት፥ ቅዳሴ፥... የመሳሰሉት መንፈሳዊ ተግባራት በተወሰኑ ጊዜያት ተዘውትረው የሚከናወኑበት ቤተክርስቲያን:: 2. ገዳም::

**ደብረ በጥብጥ** ረባሽ፥ በጥባጭ::

**አድባር** ስ 1. ብዙውን ጊዜ በሴት የምትጠራ የመናፍስት አይነት፥ ቆሌ:: 2. የአካባቢው ቆሌ ወይም መንፈስ የሚኖርበት ነው በሚል እምነት ሰዎች ቅቤ በመቀባት፥ ቡና በማፍላት፥... የሚያከብሩትና አምልኮ የሚያደርጉበት ዛፍ፥ ድንጋይ፥...::

**አድባር ነው** በሚኖርበት አካባቢ በከበሬታ አይን የሚታይ ታላቅ አዛውንት ነው:: እከሌ

አድባር ነው።

**ደበረ[2]** ግ 1. ደረበ፥ አነባበረ፥ ደበለ። 2. ሰደረ፥ ደረደረ፥ በተርታ አስቀመጠ።

**ደበረ[3]** ግ (የአራዳ አነ.) አስጠላ፥ ተጫጫነ፥ ቀፈፈ።

**ደባሪ** ቅ አስጠሊታ፥ ቀፋፊ።

**ድብርት** ስ የመቅፈፍ፥ የመክበድ፥ የመጫጫን ሁኔታ።

**ድብር አለ** ግ ተደበረ ወይም ደበረው።

**ተደበረ** ግ ቅፍፍ አለው፥ አስጠላው፥ ደስ የሚል ስሜት አጣ።

**ደበሰ** ቅ ነበዘ፥ ደበዘዘ፥ ቆሸሸ፥ ቁልጭ ብሎ አልታይ አለ (ዕሁፍ፥ ስእል፥...)።

**ድብስብስ(ደበስባሳ)** ቅ 1.ቁልጭ ብሎ የማይታይ፥ ጭፍንፍን፤ የደበዘዘ። 2. በጥራት ያልተሰራ።

**ተድበሰበሰ** ግ 1.ተሸፋፈነ፥ ተለባበሰ (ነገርን፥...)። 2. በጥራት፥ በደንብ ሳይሰራ ቀረ።

**አድበሰበሰ** ግ ሸፋፈነ፥ አለባበሰ (ነገርን፥...)።

***ደበሰሰ**

**ደበሰሰ(ደብሳሳ)** ቅ ቆርሳሳ፥ ጎታታ።

**ተንደበሰሰ** ግ ተንቆረሰሰ፥ ተጎተተ፥ አዘገመ።

**አንደበሰሰ** ግ አንቆረሰሰ፥ ጎተተ።

**ደበስባሳ** "**ደበሰ**" ስር "**ድብስብስ**" ን ተመ.

**ደበሸ(አዲበሸ)** ቅ 1. ፈዛዛ፥ ንቃት የሌለው። 2.ግድየለሽ፥ ሰነፍ ቸልተኛ። 3. ወፍራም (ለህፃን)።

**ደበቀ** ግ 1. ሰወረ ፥ሸሸገ። 2. እንዳይታወቅ አደረገ።

**ደበቅ** ቅ ስውር፥ ስዋራ (ቦታ)።

**ደበቅ ጦር** ስ ያሸመቀ ጦር።

**ደባቃ** ቅ ስዋራ (ለቦታ)።

**ድብቅ** ቅ ስውር፥ ምስጢር የሆነ።

**ድብብቆሽ** ስ 1. የተደበቀውን ልጅ ፈልጎ ለማግኘት የሚደረግ የልጆች ጨዋታ ። 2. ነገሩ ለሁሉም ወገን ግልፅ ሆኖ ሳለ አንዱ ሌላውን ለማሞኘት የመሞከር ድርጊት።

**ተደበቀ** ግ ተሰወረ፥ ተሸሸገ፥ ምስጢር ተደረገ።

**ተደባበቀ** ግ 1. ተደበቀ። 2. አንዱ ለሌላው ግልፅ የሆነ ሃሳብ ነፈገ።

**ደበበ** ግ ጠየመ፥ ደበሰ።

**ደባባ** ቅ ጠይም።

**ደበተ[1]** ግ 1. ተጫነ፥ ከበደ፥ ገረዘዘ (እንቅልፍ)። 2. አንዱን በሌላው ላይ ጫነ፥ ቆለለ።

**ደበተ[2]** ግ 1. እንዲርስ እንዲለሰልስ በጭቃ ውስጥ ቀበረ (የእንጨት ልጥን)።2. በአዛባ አጅሉ አቆየ (ገበታን፥ ቆሬን፥...)።

**ደበተረ** ግ የድብትርናን ትምህርት ተማረ፥ አወቀ።

**ደብተራ** ስ 1. የዜማ፥ የአቋቋም፥ የቅኔ፥... ምሁር፤ መዘምር። 2. መፅሃፍ ገላጭ፥ ኮከብ ቆጣሪ ።

**ድብትርና** ስ የደብተራነት ሙያ፥ ትምህርት፤ ስራ ።

**ደበነ** ግ 1. በጣም ጠበቀ፥ ከረረ። 2. በጣም አጠረ፥ ከረረ። 3. አረረ፥ ተቃጠለ፥ ደረቀ። 4.በጣም ተናደደ።

**ድብን አድርጎ ቆነጠጠ** አጥብቆ በሃይል ቆነጠጠ።

**ድባኖ** ቅ በጣም አጭር፥ ከራራ።

**ደበኔ** ስ ዋኔ፥ ቡላል።

**ደበን[1]** ቅ ቆሻሻ፥ እድፍ።

**ደበን[2]** ስ ፀጉር።

**ደበን[3]** ቅ ሞኝ፥ ነሆለል።

**ደበን አንሳ** ስ (የማንኳኳሰስ አነ.) ባለእጅ።

**ደበኛ** "**ዶማ**" ስር "**ደመኛ**" ን ተመ.

***ደበከበከ**

**ድብክብክ** ቅ1.ዝቡጥቡጥ፥ ድፍርስ፥ አተላ የበዛበት። 2.በጣም ወፍራም (ሰው፥...)።

**ድብክብክ አለ** ግ ተድበከበከ።

**ተድበከበከ** ግ 1.ተዝቦጠቦጠ፥ አልጠራ አለ፥ አተላው ከጥሩው አልለይ አለ።.2. በጣም ወፈረ (ሰው፥...)።

**አድበከበከ** ግ 1.አዝበጠበጠ፥ አተላ አደረገ። 2. አወፈረ (ሰው፥...)።

**ደበዘዘ** ግ 1. ብሩህነት፥ ደማቅነት አጣ። 2.ደከመ፥ ፈዘዘ። 3. (ዘይ.) ጎልቶ የማይታይ፥ የማይታወቅ ሆነ፡

**ደብዛዛ** ቅ 1. ብሩህነት፥ ደማቅነት የሌለው (ቀለም)። 2. ደካማ፥ ፈዛዛ (ብርሃን)።

***ደበዘዘ**

**ደበዘዝ** ቅ ቀርፋፋ፥ ጎታታ።

**ተንደበዘዘ** ግ ቀስ አለ፥ ተንቀረፈፈ።

**አንደበዘዘ** ግ አንቀረፈፈ፥ ቀስ አደረገ።

***ደበየ[1]**

**ድባያት(ደበያት)** ስ በቀል።

**ደባይ** ቅ 1. ወራሪ፥ ዘራፊ። 2. ድንገተኛ አደጋ።

**አደባየ** ግ 1. አሸነፈ፥ ረታ። 2. ጣለ፥ ረገጠ፥ አፈር አስጋጠ።

***ደበየ**[2]

**ደባ** ስ ተንኮል፥ ሴራ።

**አደባ** ግ አደፈጠ፥ አሸመቀ (ለመጥፎ ስራ)።

**ደበያት**[1] **(ደባያት፥ ደብያት)** ስ ወንፈል፥ ደቦ፥ ጅጊ።

**ደበያት**[2] "*ደበየ[1]" ስር "ደባያት" ን ተመ.

**ደበደበ**[1] ግ 1. መታ፥ ቀጠቀጠ። 2. አበሰበሰ፥ አራሰ፥ መታ (ዝናብ) ።

**ደብዳቢ** ቅ መቺ።

**ድብደባ** ስ የመምታት ወይም የመመታት ድርጊት።

**ድብድብ** ስ 1. እርስ በርስ መመታታት፥ የአካል ግጭት፥ መፈናከት። 2. ልፊያ ትግል።

**ተደበደበ** ግ 1. ተመታ፥ ተቀጠቀጠ። 2. በሰበሰ፥ ራሰ (በዝናብ)።

**ተደባደበ** ግ 1. መታ። 2. ተማታ፥ ተቀጣቀጠ፥ ተናረተ (እርስ በርስ)። 3. ተላፋ።

**ተደባዳቢ** ቅ ዱለኛ፥ ዘወትር ከሰው የሚጣላና የሚደባደብ።

**አደባደበ** ግ አጣላ፥ አማታ።

**አስደበደበ** ግ አስመታ፥ አስቀጠቀጠ።

**ደበደበ**[2] ግ 1. ጠቀመ፥ ጣፈ፥ ደረተ። 2.ደፈነ፥ መረገ፥ ቆረቆረ (የእቃ ሽንቁርን)።

**ደባደቦ** ስ የተጣጣፈ፥ ድሪቶ።

**ድብድብ** ቅ ሽንቁሩ በሰም፥ በሙጫ፥... የተደፈነ የሸክላ እቃ።

***ደበደበ**

**ድብድብ** ስ መዘርዘር፥ ፍሬ መያዝ የጀመረ የአገዳ ወይም የብር እህል (ፍሬው ከድብድብ ደረጃ ሲያልፍ ጮርቃ ይባላል)።

**ተንደበደበ** ግ አተረ፥ አበጠ፥ ጉብጉብ አለ (ሰውነት ላይ)።

**አደበደበ** ግ ፍሬ መያዝ ጀመረ (ያገዳ ወይም የብር እህል)።

**አንደበደበ** ግ ሰውነትን አጉረበረበ፥ እትር እትር እንዲል አደረገ።

**ደቡብ** ስ በሰሜን ትይዩ የሚገኝ የመሬት አቅጣጫ ፥ የሰሜን ተቃራኒ።

**የደቡብ ዋልታ** ስ በደቡብ አቅጣጫ ያለው የምድር ጫፍ ።

**ደቡብ ምስራቅ** ስ በደቡብና በምስራቅ መካከል የሚገኝ አቅጣጫ።

**ደቡብ ምእራብ** ስ በደቡብና በምእራብ መካከል የሚገኝ የመሬት አቅጣጫ።

**ደቡባዊ** ቅ በስተደቡብ በኩል ያለ፥ የሚገኝ።

**ደባ** "*ደበየ[2]" ስር ተመ.

**ደባለቀ(ደበለቀ)** ግ ቀላቀለ፥ ቀየጠ፥ ዘነቀ።

**ድብልቅ** ቅ ቅልቅል፥ ቅይጥ።

**ደብለቅ አለ** ግ ተደባለቀ፤ አብሮ ሆነ፥ ተቀላቀለ (ከሰልፈኛ፥ ከተሰብሳቢ፤ ከለቀስተኛ፥... ጋር)።

**ደበላለቀ** ግ 1. ቀያየጠ፥ ቀላቀለ። 2.አመሰቃቀለ፥ አተረማመሰ።

**ድብልቅልቅ** ቅ 1. ቅይጥይጥ፥ የተደበላለቀ። 2. ትርምስምስ፥ ዝብርቅርቅ።

**ድብልቅልቅ ያለ** ቅ በጣም ከፍተኛ የሆነ (ጠብ፥ ድግስ፥...) ።

**ተደበላለቀ** ግ ተቀላቀለ፥ ተቀየጠ ።

**ተደበላለቀ** ግ 1. ተቀያየጠ፥ ተቀላቀለ። 2.ተመሰቃቀለ፤ ተተረማመሰ ተረበሸ።

**አደባለቀ** ግ 1.ቀላቀለ፥ቀየጠ። 2.አተራመሰ፥ በጠበጠ።

**ደባል** "ደበለ" ስር ተመ.

**ደባሪ** "ደበረ[3]" ስር ተመ.

**ደባቃ** "ደበቀ" ስር ተመ.

**ደባባ** "ደበበ" ስር ተመ.

**ደባያት**[1] "*ደበየ[1]" ስር ተመ.

**ደባያት**[2] "ደበያት[1]" ን ተመ.

**ደባይ**[1] "*ደበየ[1]" ስር ተመ.

**ደባይ**[2] ስ መረሬ አፈር ወይም መሬት።

**ደባይ**[3] ስ 1. ትልቅ ነጋሪት። 2. የከበሮ አፍ (ሰፊው ወገን)።

**ደባደቦ** "ደበደበ[2]" ስር ተመ.

**ደብር** "ደበረ" ስር ተመ.

**ደብሳሳ** "*ደበሰሰ" ስር "*ደበሰሰ" ን ተመ.

**ደብተራ** "ደበተረ" ስር ተመ.

**ደብተር** ስ 1. በፅሁፍ ማስታወሻ ለመያዝ የሚያገለግል፥ የተለያየ ቅርፅና መጠን ያለው፥ በመፅሃፍ ወይም በጥራዝ መልክ የሚዘጋጅ ወረቀት። 2. የባለቤትነት መታወቂያ ወይም ሊብሬ፤ መንጃ ፈቃድ፥ የመሳሰለና በአነስተኛ ጥራዝ የተዘጋጀ ህጋዊ ሰነድ።

**ድብዛ** ስ 1. መለያ ምልክት፥ መልክ። 2.አድራሻ። *ደብዛው ጠፋ።*

**ደብዛዛ** "ደበዘዘ" ስር ተመ.

**ደብያት** "ደባያት[1]" ን ተመ.

**ደብዳቤ** "ደበደበ[1]" ስር ተመ.

**ደብዳቤ** ስ በፅሁፍ የሚተላለፍ ሰላምታ፥ መልእክት፥ ትእዛዝ፥...

**ደቦ** ስ በልመና ወይም በወንፈል መልክ ሰዎች ተሰባስበው ለአንድ ግለሰብ የሚያከናውኑት ስራ፥ ጅጌ፣ ወንፈል::

***ደቦለቦለ** "ደበለበለ" ን ተመ.

**ደቦል** ስ 1. የአንበሳ ግለገል:: 2. አካሉ ፍርጥም ያለ የሰው ወይም የእንስሳ ልጅ::

**ደቼ** ስ አፈር::

**ደቼ ብላ** አፈር ብላ::

**ደቻኛ** ስ 1. ባለመሬት፥ ባላባት:: 2. እውቅ ሰው::

**ደነሰ** ግ በሙዚቃዊ ስልት እየተመራ ማራኪ የሆነ አካላዊ እንቅስቃሴ አደረገ፥ ተወዛወዘ፥ ጨፈረ::

**ዳንስ** ስ ከሙዚቃ ጋር በሚስማማ መልክ የሚደረግ አካላዊ እንቅስቃሴ፥ ስልታዊ ውዝዋዜ::

**ዳንሰኛ** ስ የዳንስ ባለሙያ::

**አስደነሰ** ግ አስጨፈረ:: *ሙዚቃው በደንብ ኣስደነሰን::*

***ደነሰረ**

**ደንሳራ(ድንስር)** ቅ ሰነፍ፥ ውዝፍ::

**ድንስር አለ** ግ ተደነሰረ::

**ተደነሰረ** ግ ተመቻችቶ ተቀመጠ፥ ተወዘፈ::

**ደነቀ** ግ ገረመ:: *ጉዳዩን ስሰማ በጣም ደነቀኝ:*

**ድንቅ** ቅ ግሩም፥ እፁብ::

**ተደነቀ** ግ 1. ተገረመ፥ እፁብ አለ:: 2. ግሩም፥ እፁብ ተባለ፥ ከፍተኛ አድናቆት ተሰጠው::

**ተደናቂ** ቅ ግሩም የሆነ፥ ከፍተኛ ዝና ያለው::

**አደነቀ** ግ ግሩም፥ እፁብ አለ፥ አሞገሰ፥ አመሰገነ::

**አድናቂ** አሞጋሽ፥ አወደሽ::

**አድናቆት** ስ 1. ምስጋና፥ ሙገሳ:: *ኣድናቆትን ኣገኘ:* 2.የመገረም፥የመደነቅ ስሜት::

**አዳነቀ** ግ (ዘይ.) አሟሟቀ፥ አጋነነ(ነገርን)::

**አዳናቂ** ቅ ነገር አጋኖ፥ ሞቅ አድርጎ የሚያወራ::

**አስደነቀ** ግ አስገረመ፥ እፁብ አሰኘ::

**አስደናቂ** ቅ አስገራሚ፥ እፁብ ድንቅ የሆነ::

**ደነቀረ** ግ 1. መዝጊያን እንዳይከፈት ከውስጥ በኩል በአጠና፥ በድንጋይ፥... ደገፈ፥ ዘጋ፥ ሸጎረ:: 2. መሰናከል፥ እንቅፋት የሚሆን ነገር አስቀመጠ፥ ጋረጠ:: 3. ከተተ፥ ሰካ፥ ቀረቀረ::

***መደንቀሪያ*** ስ የመዝጊያ መቀርቀሪያ፥ መሸጎሪያ (ድንጋይ፥ እንጨት፥...)::

**ደንቃራ** ስ 1. የገዛ ራስን በሽታ ወደ ሌላ ሰው በማስተላለፍ መዳን ይቻላል በሚል እምነት ብዙውን ጊዜ በመንገድ ላይ የሚጣል እንደሎሚ፥ እንቁላል፥ ቂጣ ያለ የሚርት አይነት:: 2.መሰናከል፥ እንቅፋት::

**ተደነቀረ** ግ 1.ተቀረቀረ፥ ተሰካ:: 2.ተጋረጠ::

***ደነቀፈ**

**ደነቀፈ(ደንቃፋ)** ቅ ሰንካላ፥ ወልካፋ::

**ደንቀፍቃፋ(ድንቅፍቅፍ)** ቅ ወልከፍካፋ፥ ሰንከልካላ::

**ተደነቃቀፈ** ግ ተወለካከፈ፥ ተሰነካከለ::

**ተደናቀፈ** ግ ተወላከፈ፥ ተሰናከለ፥ እንቅፋት አገኘው::

**አደነቃቀፈ** ግ አወለካከፈ፥ አሰነካከለ::

**አደናቀፈ** ግ 1. አወላከፈ፥ አሰናከለ፥ አነቀፈ:: 2. እንዳይከሄድ፥ እንዳይሳካ አደረገ::

**አደናቃፊ** ቅ መሰናከል፥ እንቅፋት የሆነ::

**ደነቆለ** ግ ጠነቆለ፥ ዘነቆለ፥ አነቆረ፥ ወጋ::

***መደንቆያ*** ስ ማንቆሪያ፥ መውጊያ::

**ደነቆረ** ግ 1. ጆሮው ተደፈነ፥ ድምፅ አልሰማው አለ:: 2. ጀለ፥ ፈዘዘ፥ ነሆለለ:: 3. እውቀት፥ ስልጣኔ የሌለው ሆነ::

**ደንቆሮ** ቅ 1. ጆሮው የማይሰማ:: 2. (ዘይ.) ደደብ፥ እውቀት የሌለው:: 3. ያልተማረ::

**ደንቆሮ እንስራ** ስ ጆሮው የተገነጠለ ወይም ጆሮ የሌለው እንስራ::

**ደንቆሮ ወፍጮ** ስ የሚለጠና ያልተወቀረ ባህላዊ የእጅ ወፍጮ::

**ድንቁርና** ስ 1. የጆሮ አለመስማት:: 2. ደደብነት፥ እውቀት የለሽነት:: 3. ማይምነት፥ ሂላቀርነት::

**ተደናቆረ** ግ 1. ደነቆረ:: 2. እያንዳንዱ በየበኩሉ እየጮሀ ለመደማመጥ በሚያውክ ሁኔታ ባንድ ጊዜ አወራ፥ ተነጋገረ::

**አደነቆረ** ግ በሰው ጆሮ ላይ አለአግባብ ጮሀ::

**አደናቆረ** ግ 1. አጯጯሀ፥ አለፋለፈ:: 2. አታለለ፥ አወናበደ::

**ደነበረ** ግ 1. ደነገጠ፥ ፈራ፥ ገረገረ:: 2. በረገገ፥ ዘለለ፥ ወገሽ፥ ሸሸ::

**ደንባሪ** ቅ ድንጉጥ፥ በርጋጌ::

**ደንባራ** ዝ.ከ.

***ደነበረ**

**ደንባራ (ደምባራ)** ቅ 1. በትክክል ማየት፥ ማድረግ፥... የማይችል:: 2. (ስድብ) እውር::

**ድንብርብር(ደንበርባራ)** ዝ.ከ.

**ድንብርብር ኣለ** ግ ተደናበረ።

**ተደናበረ** ግ 1. ተደናገረ፥ ግራ ተጋባ። 2. ታወረ፥ በትክክል ማየት ተሳነው።

**ኣደናበረ** ግ 1. ኣደናገረ፥ ግራ ኣጋባ። 2.ኣሳወረ፥ ኣጠናበረ።

***ደነበረ**[2]

**ድንበር (ድምበር)** ስ 1. የኣንድ የተወሰነ የመሬት ወይም የቦታ ክልል(ወሰን፥ ድካ፥...) ከየት እስከ የት እንደሆነ ለማመልከት ይረዳ ዘንድ በመሬቱ ወይም በቦታው ጠርዝ ላይ እንዲሆን የሚደረግ ምልክት ወይም ተፈጥሮኣዊ የሆነ ድንጋይ ፥ ኮረብታ፥ ወንዝ፥...። 2. የኣንድ ኣካል ጠረፍ፥ ጠረዝ፥ ዳርቻ፥ ወሰን፥ ድካ፥...። 3. ገደብ፥ መጠን፥ ልክ። *ንግግርህ በልክ ይሁን፤ ድንበር ኣትለፍ።*

**ድንበርተኛ (ድምበርተኛ)** ስ የተወሰነ የቦታ ክልልን የሚያጎራብት መሬት፥ ቦታ፤ ኣዋሳኝ፥ ወሰንተኛ።

**ደነበሸ** ግ ሻገተ፥ ታመገ(እህል)።

**ደንበሾ** ስ ሻጋታ።

**ደነበቀ** ግ መጥለቂያን ወይም መቅጃን ከውሃ ወይም ከፈሳሽ ነገር ውስጥ እያጠለቀ ቀዳ፥ ጠለቀ።

**ደነበዘ** 1. ፈዘዘ ፥ ደነዘዘ፥ ደነገዘ። 2. ጨለመ፥ ጠቆረ።

**ደነበዝ(ደንባዛ)** ቅ 1. ፈዛዛ፥ ደንጋዛ። 2. ጥቁር፥ ጨፋና።

**ደነባ** ግ ህግ፥ ደንብ ሰራ፥ ኣበጀ፥ ኣወጣ።

**ደንብ (ደምብ)** 1. የተወሰነ ህግ፥ ድንጋጌ፥ ስርኣት። 2. ወግ፥ ልማድ።

**ደንብ ኣወጣ** ደነገገ ፤ ስርኣት፥ ህግ ኣበጀ፥ ሰራ።

**የደንብ ልብስ** ስ 1. ወታደሮች ከሌላው ተለይተው የሚታወቁበትና በስራ ላይም ሆነ በሌላ ጊዜ የሚለብሱት ልብስ። 2. በኣይነቱ፥ በኣሰራሩና በመልኩ ተመሳሳይ የሆነ በኣንድ ት/ቤት ወይም ድርጅት ውስጥ የሚገኙ ሰዎች የሚለበሱት ኣንድ ኣይነት የሆነ ልብስ፤ ዩኒፎርም።

**ደንበኛ(ደምበኛ)** ቅ 1. ዋና፥ ዋነኛ። 2. ጥሩ፥ ሁነኛ፥ ኣይነተኛ። 3. መደበኛ። *ደንበኛ ወታደር*። 4. ስ ኣንድን ጉዳይ ወይም የጋራ ጥቅምን በተመለከተ ግንኙነቱን ኣዘውትሮ ከተወሰነ ግለሰብ ወይም ድርጅት ጋር የሚያደርግ ግለሰብ ወይም ድርጅት።

***ደነከረ**

**ደንካራ** ቅ ወንካራ፥ ወልጋዳ፥ ወልካፋ።

**ደንከር ደንከር ኣለ** ግ ወንከር ወንከር፥ ወልገድ ወልገድ ኣለ። (በኣካሄድ)።

**ተደናከረ** ግ ተወናከረ፥ ተወላገደ።

**ኣደናከረ** ግ ኣወናከረ፥ ኣወላገደ።

**ደነዘ** ግ 1. ጠረሰ፥ ዶለዶመ፥ ስለት ኣልባ ሆነ (የስለት መሳሪያ)። 2. (ዘይ.) ፈዘዘ፥ ደደበ፥ ደነቆረ፤ ንቃት፥ ቅልጥፍና ኣጣ።

**ደነዝ(ደናዛ)** ቅ 1. ጠራሳ፥ ዶልዷማ፥ ስለት የለሽ። 2. (ዘይ.) ንቃት፥ ቅልጥፍና የሌለው፥ ደደብ።

**ደነዘዘ** ግ በድን ሆነ፥ ደነገዘ፥ ፈዘዘ፤ ንቃት ቅልጥፍና፥ ኣጣ።

**ደነዝዝ(ደንዛዛ)** ቅ ፈዛዛ፥ በድን።

**ኣደነዘዘ** ግ በድን ኣደረገ፥ ኣደነገዘ፥ ኣፈዘዘ፥ ንቃት፥ ቅልጥፍና ኣልባ ኣደረገ።

**ማደንዘዣ** ስ ኣካልን ወይም ኣእምሮን የሚያፈዝ መድሃኒት፥ እፅ።

**ኣደንዛዥ** ቅ የሚያፈዝ (ኣካልን፥ ኣእምሮን)።

**ኣደንዛዥ እፅ** ስ ለጊዜው ስሜትን የማነቃቃትና የማስደሰት ባህርይ ያለው፥ እየዋለ እያደር ግን የተጠቃሚውን (የሱሰኛውን) ኣእምሮ የሚያፈዝና የሚያደነዝዝ፥ ሰውነትን የሚያዝል፥... እንደ ሃሺሽ ያለ ሱስ ኣስያዥ እፅ።

**ደነዝ** "ደነዘ" ስር ተመ.

**ደነደነ** ግ ወፈረ።

**ደንዳና** ቅ ወፍራም።

**ደንዳኔ** ስ ትልቁ ኣንጀት።

***ደነገረ**

**ደንጋራ** ቅ ደንባራ፥ ግራ የሚገባው፤ የተረጋጋ ኣስተውሎትና ነገሮችን ፈጠን ብሎ የመረዳት ችሎታ የሚያጥረው።

**ድንግርግር ኣለው** ግራ ተጋባ።

**ተደነጋገረ** ግ 1. ተደነባበረ፥ ግራ ተጋባ። 2.ተምታታ፥ ተዘበራረቀ።

**ተደናገረ** ዝ.ከ.

**ኣደነጋገረ** ግ 1. ኣደነባበረ፥ ግራ ኣጋባ። 2.ኣምታታ፥ ኣሳሳተ፥ ኣዘበራረቀ፥ ኣጭበረበረ።

**ኣደናገረ** ዝ.ከ.

**ኣደናጋሪ** ቅ ኣጭበርባሪ፥ ኣምታች፥ ኣውቆ ኣሳሳች።

**ደነገዘ** ግ 1. እንደ መጨለም ኣለ፥ ለኣይን ያዘ። 2. ፈዘዘ፥ ደከመ።

**ደነገዝ** ቅ ፈዛዛ።

**ድንግዝግዝ ኣለ** ግ ጨልምልም ኣለ።

**ኣደነገዘ** ግ 1.ኣደነዘዘ፥ ኣፈዘዘ። 2. ኣደከመ፥

አፈዘዘ።

**ደነገገ** ግ ወሰነ፣ ህግ፥ ደንብ አወጣ።

**ድንጋጌ** ስ ህግ፥ ደንብ፥ ስርአት።

**ተደነገገ** ግ ህግ፥ ደንብ ወጣ ወይም ተሰራ።

**ደነገጠ** ግ 1. ድንገት አእምሮው ተረበሸ፥ ታወከ (አንድ ነገር በማየቱ ወይም በመስማቱ፥... የተነሳ)። 2. ፈራ፥ ራደ።


**ደንጋጣ** ቅ ስጉ፥ ፈሪ፥ በርጋጋ።

**ድንጉጥ** ቅ 1. ስጉ፥ ፈሪ። 2. ሽቁጥቁጥ፥ ትሁት።

**ድንጋጤ** ስ ድንገት የሚያጋጥም ፍርሃት ወይም መረበሽ።

**ተደናገጠ** ግ ደነገጠ፥ ፈራ።

**ደነጎረ**[1] ግ በደንጎራ ቆፈረ፥ ደቀደቀ፥ ማሰ (መሬትን)።



**መደንጎሪያ** ስ ዛቢያው ቀጥ ያለና ወፍራም ሆኖ በጫፉ ላይ ማረሻ ወይም መጥረቢያ መሰል ዶማ የተዋደደበት መቆፈሪያ፥ ደንጎራ።

**ደንጎራ** ዝ.ከ.

መደንጎሪያ

**ደነጎረ**[2] ግ 1. መተላለፊያን ወይም በርን በእንጨት፥ በድንጋይ፥... ዘጋ፥ አገደ። 2. (ዘይ.) አንድን ነገር ካለቦታው አስገባ። 3. አባጣ ጎባጣ፥ ጉራንጉር አደረገ።

**ድንጉርጉር** ስ ጉራንጉር፥ ድንጋይ የበዛበት ቦታ።

**ድንጉርጉር አለ** ግ ተደነጓጎረ።

**ድንጉርጉር አደረገ** ግ አደነጓጎረ።

**ተደነጓጎረ** ግ ተመሰቃቀለ፥ ተደበላለቀ፥ ተተረማመሰ።

**ተደናጎረ** ዝ.ከ.

**አደነጓጎረ** ግ አመሰቃቀለ፥ አዘበራረቀ፥ አተረማመሰ።

**አደናጎረ** ዝ.ከ.

**ደነፈቀ** ግ በብዛት እንባ እያፈሰሰ አለቀሰ፥ ተንሰቀሰቀ፥ ነፈረቀ።

**አስደነፈቀ** ግ በጣም አስለቀሰ፥ አነፋረቀ።

**ደነፋ** ግ 1. እየተንጎራደደ የፉከራ ቃል አሰማ። 2. ዛተ፥ ፎከረ።

**ደንፊ** ቅ 1. ዛቺ፥ ፎካሪ ። 2. ጉረኛ።

**ድንፋታ** ስ 1. ፉከራ ። 2. ዛቻ።

**ደናዛ** "ደነዘ" ስር ተመ.

**ደናግል** "ድንግል" ን ተመ.

**ደን** ስ ጫካ፥ ዱር (ዛፍ፥ ቁጥቋጦ፥... በብዛት የሚገኝበት)።

**ደንሳራ** "*ደነሰረ" ስር ተመ.

**ደንሴ(ደንሶ)** ቅ አመለ ልስልስ፥ ገራም።

**ደንቀፍቃፋ** "*ደነቀፈ" ስር ተመ.

**ደንቃራ** "ደነቀረ" ስር ተመ.

**ደንቃፋ** "*ደነቀፈ" ስር "ደነቀፍ"ን ተመ.

**ደንቆሮ** "ደነቆረ" ስር ተመ.

**ደንበርባራ** "ደነበረ" ስር "ድንብርብር"ን ተመ.

**ደንበሾ** "ደነበሸ" ስር ተመ.

**ደንበኛ** "ደነባ" ስር ተመ.

**ደንበጃን** "ደምበጃን" ተመ.

**ደንባሪ** "ደነበረ" ስር ተመ.

**ደንባራ**[1] "ደነበረ[1]" ስር ተመ.

**ደንባራ**[2] "ደነበረ[2]" ስር ተመ.

**ደንባዛ** " ደነበዘ" ስር ተመ.

**ደንብ** "ደነባ" ስር ተመ.

**ደንታ** ስ ግድ፥ ቁብ።

**ደንታ ቢስ** ቅ ግድ የለሽ።

**ደንታ የለውም** ግድ የለውም፥ አይጨነቅም።

**ደንካራ** "*ደነከር" ስር ተመ.

**ደንዛዛ** "ደነዘዘ" ስር " ደነዘዝ" ን ተመ.

**ድንደሮ**[1] ቅ ወፍራም፥ ጠብደል ።

**ደንደሮ**[2] ስ የኮሸሽላ አይነት።

**ደንደስ** ስ 1. ማጅራት፥ ጫንቃ። 2. ከማጅራት እስከ ጭራ የሚዘልቅ ረዥምና ባለብዙ አጥንት፥ አከርካሪ።

**ደንደሳም** ቅ ማጅራቱ፥ ጫንቃው የወፈረ።

**ደንዳ(ዳንዳ)** ስ ማማ።

**ደንዳና** "ደነደነ" ስር ተመ.

**ደንዳኔ** ዝ.ከ.

**ደንገላሳ** ስ በሽምጥና በሶምሶማ መካከል ያለ የፈረስ ግልቢያ አይነት።

**ደንገል** ስ በወንዝ ዳርቻ፥ ውሃ በተኛበት ቦታ የሚበቅል፥ እንደ መቃ ያለና ለታንኳ የሚያገለግል ወፍራም ሳር።

**ደንገሎ** ስ ለውሻ፥ ለበቅሎ፥... መኖ እንዲሆን ዱቄቱ ከነአሰሩ ተቦክቶ የሚዘጋጅ ቂጣ።

**ደንገጡር(ደንገጥር)** ስ ቀደም ባለው ጊዜ የእመቤቷን ጌጥ ተሸክማ እመቤቷን ትከተል ወይም ታጅብ የነበረች ሴት።

**ደንገጥር**[1] ስ በሽማ ጥበብ ዳርና ዳር በክፈፍነት የሚጣል ጥለት።

**ደንገጥር**[2] "ደንገጡር" ን ተመ.

**ደንጊያ** "ድንጋይ" ን ተመ.

**ደንጋራ** "'ደነገረ" ስር ተመ.

**ደንጋጣ** "ደነገጠ" ስር ተመ.

**ደንግ** ስ ከብር÷ ከወርቅ÷... የሚሰራ የጌጥ አይነት::

**ደንጎለጥ(ደንጎሊጥ)** ቅ 1. ኣመሉ ኣስቸጋሪና መጥፎ የሆነ (ሰው):: 2. ትምህርት የማይገባው÷ ኣእምሮው ትምህርት የማይቀበል (ሰው)::

**ዶንጎላጉል(ደንጎለት)** ቅ ኣባጣ ጎባጣ÷ ኣስቸጋሪ÷ ኣጓጉል÷ የማይረባ::

**ደንጎሎ** ስ የአደንጓሬ ኣይነት:

**ደንጎራ** "ደነጎረ[1]" ስር ተመ.

**ደንፌ** "ደነፉ" ስር ተመ.

**ደከመ** ግ 1. ሃይል÷ ኣቅም÷ ብርታት ኣጣ፣ ጉልበቱ ኣለቀ:: 2. ፈዘዘ÷ ሃይሉ ቀነሰ:: 3. ዛለ÷ ተልፈሰፈሰ:: 4. ታከተ÷ ሰለቸ:: 5. ሰነፈ:: 6. ኣረጀ:: 7. ጣር ያዘው÷ ለሞት ተቃረበ: 8. ብዙ ጣረ÷ ጋረ÷ ለፋ::

**ደካማ** ቅ 1. ኣቅመቢስ:: 2. ሰነፍ:: 3. ኣካለ ስንኩል:: 4. ልል÷ ጠንካራ ያልሆነ:: 5. የኣስተሳሰብ ብቃት የሌለው÷ ኣስተሳሰቡ እንጭጭ የሆነ:: 6. ጥራት÷ ብቃት÷... የሌለው:: *የሰራው ስራ ደካማ ነው::*

**ደካማ ጎን** እንከን÷ ጉድለት (የኣስተሳሰብ÷ የኣድራጎት)::

**ድኩም** ቅ 1. ደካማ÷ ሰነፍ:: 2. (ብ.ቁ. **ድኩማን**) ኣካለ ስንኩል::

**ድካም** ስ 1. ሃይል÷ ኣቅም÷ ብርታት ማጣት:: 2. ልፋት÷ ጥረት::

**የድካም ዋጋ** ስ ለስራ÷ ለኣገልግሎት የሚደረግ ክፍያ::

**ድከመት** ስ 1. ሃይል÷ ኣቅም÷ ብርታት ማጣት:: 2. ስንፍና:: 3. እንከን÷ ጉድለት (የኣስተሳሰብ÷ የኣድራጎት)::

**ተደከመ** ግ ጥረት ተደረገ:: *ኣልተሳካም እንጂ ለዚህ ኣገር ብዙ ተደክሞ ነበር::*

**ተዳከመ** ግ 1. ሃይል÷ ኣቅም÷ ብርታት ኣጣ:: 2. ዛለ÷ ተልፈሰፈሰ:: 3. ሰነፈ:: 4. ኣረጀ:: 5. ጣር ያዘው÷ ለሞት ተቃረበ:: 6. ቀዘቀዘ÷ እንቅስቃሴው ቀነሰ:: *ገበያው ተዳከመ::*

**ኣደከመ** ግ 1. ኣለፋ:: 2. ብርታት÷ ሃይል ኣቅም ኣሳጣ::

**ኣድካሚ** ቅ ኣሰልቺ÷ ኣልፊ÷ኣዋኪ(ስራ÷...)::

**ኣዳከመ** ግ 1. ሃይል÷ ብርታት እንዲያጣ ወይም እንዲደክም ኣደረገ:: 2. በጥሩ ሁኔታ እንዳይሰራ÷እንዳይንቀሳቀስ÷...ኣደረገ:: *ድርጅቱን ያዳከሙ ተባረሩ::*

3. ኣሳነፈ::

**ደከረ** ግ 1. ኣቀረበ÷ ኣዘጋጀ÷ ደቀነ:: 2. ኣዘገበ÷ ኣነጣጠረ::

**ተደከረ** ግ 1. ቀረበ÷ ተዘጋጀ÷ ተደቀነ:: 2.ተዘገበ÷ ተነጣጠረ::

**ደከነ** ግ በትንሽ በትንሹ ከመረ÷ ቆለለ÷ (የታጨደ ሰብልን)::

**ድክን (ድክን)** ስ ኣነስተኛ ክምር (የሰብል)::

**ደከከ** ግ 1. ኣጠረ:: 2. ኣጭርና ወፍራም ሆነ::

**ደካካ** ቅ ኣጭረና ወፍራም::

**ተንዳከከ** ግ 1. ደካካ ሆነ:: 2. ተንቆረሰሰ÷ ፍጥነት ኣጣ (በኣካሄድ)::

**ኣንዳከከ** ግ ኣንቆረሰሰ÷ ፍጥነት ኣሳጣ (በኣካሄድ)::

**ደከደከ** ግ ራሰ÷ በሰበሰ::

**ደከደከ (ደከዳካ)** ቅ የራሰ÷ የበሰበሰ::

***ደከደከ**

**ዶኬ** ስ 1. ቅመምና ቅባት የሌለው መናኛ ወጥ:: 2. ወፍራም የሽሮ ወጥ::

**ደክ ደክ ኣለ** ግ ተንደከደከ::

**ተንደከደከ** ግ 1. ፈላ (ሽሮ ወጥ ):: 2.ወፍራም ሽሮ ሲንተከተክ የሚያሰማውን ኣይነት ድምፅ ኣሰማ::

**ኣንደከደከ** ግ ኣፈላ÷ ቀቀለ (ሽሮን)::

**ደከደክ** "ደከደከ" ስር ተመ.

**ደካ[1]** ግ ወሰነ÷ ክልል÷ ድንበር ኣበጀ::

**ዱካ** ስ ፈለግ÷ ኮቴ÷ ፋና::

**ድካ** ስ 1. ወሰን÷ ክልል:: 2. የወሰን÷ የክልል ምልክት (ድንጋይ÷ እንጨት÷...)::

**ተዳካ** ግ ተዋሰነ÷ ተካለለ::

**ደካ[2]** ግ 1.ገፈለጠ÷ ኣለፋ:: 2. ደቃ፣ መታ::

**ደኮ** ስ የለፋ ደበሎ÷ ድብዳብ::

**ደካማ** "ደከመ" ስር ተመ.

**ደካካ** "ደከከ" ስር ተመ.

**ደከዳካ** "ደከደከ" ስር "ደከደከክ ን ተመ.

**ደኳኳ(ድኳ)** ስ 1. የእንጨት ትራስ÷ ብርኩማ:: 2. በእጃቸው እየተረዱ ኣካለ ስንኩላን የሚጠቀሙበት የእጅ ብርኩማ ወይም መንፏቀቂያ:: 3. ለመቀመጫነት የሚያገለግል በርጩማ::

**ደወለ** ግ 1. ደወልን መታ ኣንቃጨለ÷ የደወል ድምፅ እንዲሰጥ ኣደረገ:: 2. የደወል ድምፅ ኣሰማ:: 3. መታ÷ ደቃ÷ ደለቀ (በቡጢ):: 4. የስልክ ጥሪ ኣደረገ÷ በስልክ ኣነጋገረ:: 5. በነፍስ ግዳይ ወይም በሌላ ከፍተኛ ጠብ ምክንያት ቂም

በቀል ከያዙበት ሰዎች ጋር እንዲያስታርቁት የቤተክርስቲያን ደወል በመደወል ካህናትን ተማጠኑ፥ ለመኑ።

**ደወል** ስ 1. ከእንጨት ወይም ከብረት ወይም ከድንጋይ፥... በተለያየ ቅርፅ ተሰርቶ በብረት ወይም በድንጋይ፥... ሲመቱት ድምፅ የሚሰጥ፥ ለጥሪ የሚያገለግል መረዋ (ብዙውን ጊዜ በቤተ ክርስቲያን፥ በት/ቤት የሚገኝ)። 2. በኤሌትሪክ ሃይል የሚሰራ፥ በጣት ሲጫኑት (የኤሌክትሪኩን ኡደት መስመሩን በማነካካት) ድምፅ የሚሰጥ መጥሪያ (በቢሮ፥ በመኖሪያ ቤት፥...የሚገኝ)።

**ደዋይ** ቅ 1. ተግባሩ በየወቅቱ ደወል መደወል፥ የደወል ጩሀት ማሰማት የሆነ (ሰው)። 2. የስልክ ጥሪ አድራጊ (ሰው)።

**ተደወለ** ግ 1. የደወል ድምፅ ተሰማ፤ ደወል ተመታ። 2. የስልክ ጥሪ ተደረገ።

**ተዳወለ** ግ ተማታ፥ ተዳለቀ /በቡጢ፥.../።

**ደወረ** ግ ጠመጠመ፥ ጠቀለለ፥ አጠነጠነ (ፈትልን፥ ክርን፥...)።

**መደወሪያ(ማዳወሪያ)** ስ ፈትልን፥ ክርን፥... ለማጠንጠን የሚያገለግል ባህላዊ የሸማኔ እቃ።

**ደዋሪ(አዳዋሪ)** ስ ድውር አጠንጣኝ።

**ድውር** ስ በቀሰም ላይ የተጠመጠመ፥ የተጠቀለለ ፈትል፥ ክር፥...።

**ተደወረ** ግ ተጠመጠመ፤ ተጠቀለለ፤ ተጠነጠነ (ፈትል፥ ክር፥...)።

**ተዳወረ** ዝ.ክ.

**አዳወረ** ግ ደወረ።

**ማዳወሪያ** "**ደወረ**" ስር "**መደወሪያ**"ን ተመ.

**አዳዋሪ** "**ደወረ**" ስር "**ደዋሪ**" ን ተመ.

**ደዋይ** "**ደወለ**" ስር ተመ.

**ደዌ(ዱያት)** ስ 1. ህመም። 2. የቆዳ በሽታ።

**ደዌ ስጋ** ስ ቁምጥና።

**ዱያታም** ቅ (ስድብ) የተለያየ በሽታ ያለበት (ሰው)።

**ድውይ** ቅ 1. (ስድብ) ቆማጣ። 2. በሽተኛ። 3. (ዘይ.) በጣም አጭር (ሰው)።

**ደውዳዋ** ቅ አውደልዳይ፥ አደዝዳዥ።

**ደዘደዘ** ግ 1. መታ፥ ጠለዘ። 2. ወቀጠ።

***ደዘደዘ**

**ደዘደዝ** ቅ አውደልዳይ፥ አደሸዳሽ፥ ስራ ፈት።

**አደዘደዘ** ግ አውደለደለ፥ አደሸደሸ፥ ስራ ፈታ።

**አደዝዳዥ** ቅ (ስድብ) አውደልዳይ፥ ስራ ፈት።

**ደየነ** ግ ኮነነ፥ ለመከራና ለስቃይ ዳረገ።

**ደይን** ስ የመከራና የስቃይ ቦታ፤ ሲኦል።

**ደይን(ደይኔን) አየሁ** ተሰቃየሁ፥ ተንገላታሁ።

**ደደሆ** ስ በቆላና በወይናደጋ አካባቢ የሚበቅል ትናንሽ ፍሬዎችን የሚያፈራ አነስተኛ ዛፍ።

**ደደረ** ግ ጠጠረ፥ ጠነከረ (ብዙውን ጊዜ የእጅ መዳፍ፥ ውስጥ እግር፥...)።

**ድድር** ቅ ጥጥር፥ ጠንካራ።

**ደደቀ** ግ በመደደቂያ መሬቱን እየወጋ ቆፈረ፥ አፈሩን ማሰ፥ ጓሉን ገለበጠ፤ ደነገረ።

**መደደቂያ** ስ ሹል የሆነ መንታ ጫፍ ያለው ብረት የተዋደደበት መቆፈሪያ፤ መደንገሪያ።

**ድድቅ** ቅ በመደደቂያ የተቆፈረ (መሬት)።



***መደደቂያ***

**ደደቆ** ስ 1. ኩልኩልት ። 2. የበግ አንገት የሚያሳብጥ በሽታ።

**ደደበ** ግ 1 ደነዘ፥ እውቀት የማይገባው ሆነ። 2. በድን ሆነ፥ ደነዘዘ (ሰውነት)።

**ደደብ** ቅ 1. (ስድብ) ደነዝ፥ እውቀት የማይገባው። ስ 2. ቆዳ ሲገፈፍ ከቆዳው ላይ ተለጥፎ የቀረ ስጋ።

**ደጀ ሰላም** "**ደጅ**" ስር ተመ.

**ደጀን** ስ በግንባር ከሚሰለፈው ወገን (ብዙውን ጊዜ የጦር ሃይል) ድጋፍ ሰጭ ወይም ተጠባባቂ እንዲሆን ከበስተሗላ በኩል የሚሰለፍ ሃይል።

**ደጅ** ስ 1. ከቤት ውጭ ያለ ቦታ። 2. የቤት በር፥ መዝጊያ። *ደጁን ዘጋው።*

**ደጅ ወጣ** 1. ለመፀዳዳት ወደ ጓሮ ሄደ። 2. ከህመሙ አገግሞ ደጅ ለደጅ መንቀሳቀስ ጀመረ። 3. የደረሰበትን ግፍ ለመበቀል ሸፈተ። 4. ይፋ ሆነ። *ነገሩ ደጅ ወጣ።*


**ደጅ ወጣች** 1. ግብር ውሃ ወጣች፥ ለመፀዳዳት ወደ ጓሮ ሄደች። 2. ከወሊድ በሗላ የሚያስፈልገውን የእረፍት ጊዜ ጨርሳ ተነሳች፤ ስራ ጀመረች።

**ደጅ ጠና** ጉዳዩን እንዲፈፅምለት ወደሚመለከተው ዘንድ እየተመላለሰ እጅ ነሳ፥ ተለማመጠ፥ ልመና አቀረበ።

**ደጅ ጠኚ(ደጀ ጠኚ)** ስ ጉዳዩን እንዲፈፅምለት ወደሚመለከተው ባለስልጣን ዘንድ እየሄደ የሚለማመጥ፥ እጅ የሚነሳ፥ ልመና የሚያቀርብ ሰው።

**ደጅ ጥናት** ስ አንድን ጉዳይ ለማስፈፀም ወደሚመለከተው ባለስልጣን ዘንድ እየተመላለሱ ልመና፥ አቤቱታ ማቅረብ፥ መለማመጥ።

**ደጅ አስጠና** በደጅ ጥናት አጉላላ፥ አለፋ።
**ደጀ ሰላም** ስ 1. በቤት ወይም በእድሞ መልክ ሆኖ የሚሰራ፥ ወደ ቤተ ክርስቲያን ግቢ ለመግባትና ለመጣት እንደመተላለፊያ የሚያገለግል የቤተክርስቲያን አጥር ዋና በር። 2. ካህናት መክፈልት የሚበሉበትና በቤተክርስቲያን ግቢ ውስጥ የሚገኝ ቤት።
**ደጀ ብርሃን** ስ ቤተልሄም።
**ደጃዝማች(ደጃማች፥ደጃች)** ስ 1.በቀድሞ ጊዜ የጦር የበላይ ሹም የማእረግ ስም። 2.በራስና በፊታውራሪ መካከል ያለ የማእርግ ስም።
**ደጃፍ** ስ 1. በመዝጊያ የሚከለል የቤት ክፍተት፥ መግቢያና መውጫ። 2. በቤት በር አካባቢ የሚገኝ ቦታ። 3. የቤት መዝጊያ።
**ደገለለ** ግ በወፍራሙ ጠቀለለ፥ ጠመጠመ።
**ደገሌ** ስ ማቶት።
**ደገመ[1]** ግ 1. አንድን ነገር እንደገና መልሶ አደረገ። 2. አከለ፥ ጨመረ። 3. ወደቀ። ፈተና ሳያልፍ በመቅረቱ እነበረበት ክፍል በመቆየት እንደገና እንዲማር ሆነ።
**ደጋሚ** ቅ ፈተና ሳያልፍ በመቅረቱ እነበረበት ክፍል በመቆየት እንደገና እንዲማር የሆነ።
**ደግሞ** 1. እንደገና። 2. በተጨማሪ።
**ዳግም(ዳግሚያ)** ዳግመኛ።
**ዳግም(ዳግማይ) ትንሳኤ** ስ ከትንሳኤ በሃላ ያለው የመጀመሪያው እሁድ።
**ዳግም [አረቄ]** ስ በድጋሚ እንዲጣራ ወይም ነጥሮ እንዲወጣ የተደረገ አረቄ።
**ዳግመኛ (ዳግሞሽ)** ተው.ግ. እንደገና፥ ለሁለተኛ ጊዜ።
**ዳግማዊ** ቅ ሁለተኛ። *ዳግማዊ ምኒልክ*፡
**ድጋሚ** ተው.ግ. 1. እንደገና፥ ለሁለተኛ ጊዜ። 2. በተጨማሪ።
**ደጋገመ** ግ አንድን ነገር መላልሶ አደረገ።
**ድግግም** ስ ተደጋጋሚ፥ የአንድ ድርጊት ምልልስ፥ ተደጋግሞ መሆን፥ መደረግ።
**ድግግሞሽ** ዝ.ከ.
**ተደጋገመ** ግ አንድ ነገር ተመላልሶ ተደረገ።
**ተደጋጋሚ** ቅ ተመላልሶ የሚደረግ፥ የተደረገ።
**አደጋገመ** ግ አንድ ድርጊት ከተከናወነ በሏላ ተመልሶ እንደገና እንዲደረግ አስፈለገ።
**አዳገመ** ግ አደጋገመ።
**አስደገመ** ግ እንደገና (በድጋሚ) አስደረገ።
**ደገመ[2]** ግ 1. በለሆሳስ አነበበ፥ አነበነበ (ፀሎትን)። 2. ተማረ፥ ጨረሰ (ደዊትን)።
**ደገመበት** ድግምት አደረገበት።
**ደጋሚ** ስ በንባብ ፀሎት የሚያደርስ፣ አነብናቢ።
**ድጋም** ስ በለሆሳስ የሚደረግ ፀሎት።
**ድግምት** ስ የአስማት መነባንብ።
**ድግምተኛ** ስ አስማተኛ፥ መተተኛ።
**ድግምታም** ዝ.ከ.
**አስደገመ** ግ 1. አስማት አስደረገ። 2.የፀሎት መፅሃፍ እንዲነበብ አስደረገ፥ አስፀለየ። 3. አስተማረ፥ አስጠና (ዳዊትን)።
**ደገሰ** ግ 1. አሰናዳ፥ አዘጋጀ (ምግብና መጠጥ ወይም ሌላ ነገር ለተጋባዦች)። 2. ጠነሰሰ፥ አዘጋጀ (ሴራ፥ ተንኮል፥...)።
**መደገሻ** ስ ድግስ የሚዘጋጅበት ገንዘብ፥ ቦታ፥...።
**ደጋሽ** ቅ ድግስ የሚያዘጋጅ።
**ድግስ** ስ 1. ለግብዣ፥ ለሰርግ፥... የሚዘጋጅ ምግብና መጠን። 2. አንድ ነገር ለማከናወን የሚደረግ ዝግጅት።
**ተደገሰ** ግ ተሰናዳ ፥ ተዘጋጀ (ድግስ ወይም ሌላ ነገር)።
**ደገነ** ግ 1. አጎበጠ (እንደደጋን) ። 2. አዘገበ፥ አነጣጠረ።
**ደጋን** ስ 1. ለጥጥ፥ ለሱፍ ፀጉር፥... መንደፊያ የሚያገለግል ጅማት የተወጠረበት ጎባጣ እንጨት። 2. እንደ ደጋን ሆኖ የተሰራ የቀስት ማፈናጠሪያ።




ደጋን 1ኛ ፍቺ

**ደጋን እግር** ቅ (ስድብ) የእግሩ ቅልጥም እንደ ደጋን የጎበጠ።
**ደጋን ወገብ** ቅ ከወደ ወገቡ ጎበጥ ያለ።
**ድግን መትረየስ** ስ ባለእግር መትረየስ።
**ድግን መጋዝ** ስ እጀታው በደጋን ቅርፅ የተሰራ መጋዝ።
**ደገኛ** " ደጋ" ስር ተመ.
**ደኅኛ** " ደግ" ስር ተመ.
***ደገዘ (*ደገዘገዘ)**
**ድግዝግዝታ** ስ ጭልምልም ያለ፥ ምሽት።
**ድንግዝግዝ አለ** ግ ጨለመ።

**ደገደገ**[1] ግ 1. ከሳ፥ ከሰሰ፥ መነመነ። 2. ፈዘዘ (አይን)።
**ደግዳጋ** ቅ ከሲታ፣ ከሳሳ።
**ደገደገ**[2] ግ አደፈ፥ ቸከ።
**ደግዳጋ** ቅ አዳፋ፥ የቸከ።
*ደገደገ
**ድግ** ስ ርዝመቱ ከ25 እስከ 30 ክንድ የሚሆን፥ በቀድሞ ጊዜ ወንዶች ወገባቸው ላይ ይጠመጥሙት የነበረ መታጠቂያ፤ በጣም ረጅም የሆነ መቀነት።
**ድግድግ** ስ ድግድጋት።
**ድግድጋት** ስ 1. ወደ ቤተክርስቲያን፥ ወደ ቤተ መንግስት ሲገባ ወይም ክብር ሊሰጠው ወደሚገባ ሰው ዘንድ ሲቀረብ የሚደረግ የተለየ የሸማ አለባበስ ስርአት። 2. በሃዘን ጊዜ ሴቶች የነጠላቸውን አንዱን ጫፍ በጥለቱ በኩል ወገባቸው ላይ አስረው ሌላውን ጫፍ በትከሻቸው በኩል በማጣፋት የሚያደርጉት የአለባበስ ስርአት።
**አደገደገ** ግ 1. ሸማውን በድግድጋት አለባበስ ስርአት ለበሰ። 2. (ዘይ.) ሀ. ታጠቀ፥ ተዘጋጀ፥ አሰፈሰፈ (አንድ ነገር ለማድረግ)። ለ. ተለማመጠ፥ አጎበደደ።
**አደገደገች** አሸረጠች።
**አደግዳጊ** ቅ (ዘይ.) ተለማማጭ፥ ሸርጉድ ባይ።
**አስደገደገ** ግ (ዘይ.) አስጨነቀ፥ አስፈራ፥ ሸርጉድ አስባለ።
**አስደግዳጊ** ቅ ሃይለኛ፥ አስፈሪ፥ አስጨናቂ፥ ሸርጉድ የሚያስብል።
**ደገፈ** ግ 1. ድጋፍ ሆነ። 2. ረዳ፥ አገዘ። 3. ቀደም ሲል የተሰነዘረን ሃሳብ መቀበሉን ወይም ትክክለኛ ሃሳብ መሆኑን በማጠናከር ተናገረ፥ ሃሳብ ሰጠ።
**ደገፉ** ስ 1.ወጋግራ፥ ምሰሶ። 2. የአልጋ ሸንኮር ወይም እግር።
**ደገፉ** ስ ቃሊብ፥ የወንዝ ዳርና ዳር። *ወንዙ ከላፍ እስከ ደገፉ ሞልቷል።*
**ደጋፊ** ቅ ረዳት፥ አጋዥ።
**በድግፍግፍ** በብዙ ድጋፍ፥ በእርዳታ።
**ድጋፍ** ስ 1. እርዳታ፥ እገዛ። 2. አንድ አካል ባለበት ቦታ ሳይነቃነቅ ወይም ሳይወድቅ እንዲቆይ ጥንካሬ የሚሰጥ ሌላ አካል። 3. መከዳ፥ ትራስ። 4. ማጠናከሪያ፥ ተጨማሪ ሃይል።
**የድጋፍ ሰልፍ** ስ አንድን አቋም በመደገፍ የሚደረግ ሰልፍ።
**ተደገፈ** ግ 1.ተረዳ፥ ታገዘ፥ ድጋፍ ተደረገለት። 2. ድጋፍ አገኘ።
**ተደጋገፈ** ግ 1. ተረዳዳ። 2. እርስ በርሱ፥ አንዱ ለሌላው ደጋፍ ሆነ።
**ተደጋጋፊ** እርስ በርስ የሚተጋገዝ፥ የሚረዳዳ።
**አስደገፈ** ግ ድጋፍ ላይ አደረገ፥ በድጋፍ አስያዘ።
**ደጋ** ስ ከባህር ወለል በጣም ከፍ ብሎ የሚገኝና የአየር ጠባዩ ቀዝቃዛ የሆነ አካባቢ፤ የቆላ ተቃራኒ።
**ደገኛ** ስ በደጋ የሚኖር ሰው።
**ደጋሚ**[1] "ደገመ[1]" ስር ተመ.
**ደጋሚ**[2] "ደገመ[2]" ስር ተመ.
**ደጋሽ** "ደገሰ" ስር ተመ.
**ደጋን** "ደገነ" ስር ተመ.
**ደጋገመ** "ደገመ[1]" ስር ተመ.
**ደጋፊ** "ደገፈ" ስር ተመ.
**ደግ** ቅ 1. ጥሩ፥ መልካም። 2. ቸር፥ ለጋስ። 3.ይሁን፥ እሺ ለማለት የሚነገር አባባል።
**ደገኛ** ቅ ጥሩ፥ መልካም (ለነገር፥ ለሰው)።
**ደግሞ** "ደገመ[1]" ስር ተመ.
**ደግዳጋ**[1] "ደገደገ[1]" ስር ተመ.
**ደግዳጋ**[2] "ደገደገ[2]" ስር ተመ.
*ደጎለጎለ
**ድጉልጉል** ቅ ወፍራምና ቅርፀ ቢስ የሆነ።
**ድጉልጉል አለ** ግ ተድጎለጎለ።
**ድጉልጉል አደረገ** ግ አድጎለጎለ።
**ተድጎለጎለ** ግ 1. ወፍራምና ቅርፀቢስ ሆነ። 2. ከውፍረትና ከቅርፀ ቢስነት የተነሳ ቀልጠፍ ብሎ መራመድ ተሳነው።
**አድጎለጎለ** ግ አወፈረ፥ ቅርፀቢስ አደረገ።
**ደጎመ** ግ ደገፈ፥ በመጠኑ እርዳታ አደረገ፥ በጎደለ እየሞላ አገዘ (በገንዘብ፥...)።
**ደጓሚ** ቅ አጋዥ፥ እርዳታ የሚያደርግ (የገንዘብ፥...)።
**ድጎማ** ስ በጎደለ መሙያ ወይም ለማጠናከሪያ የሚሆን መጠነኛ እገዛ፥ እርዳታ (የገንዘብ፥...)።
**ተደጎመ** ግ ተደገፈ፥ በመጠኑ እርዳታ ተደረገለት፥ ታገዘ (በገንዘብ፥...)።
**ደጎሰ** ግ የመፃህፍትን ገበታ በቆዳ፥ በባህር አረብ ሸፍኖ ወይም ለብዶ ልባዱን በልዩ ልዩ ቅርፅ ሸለመ፥ አስጌጠ።
**መደጎሻ** ስ በመፅሃፍ ልባድ ላይ ልዩ ልዩ ቅረፆችን ለመስራት የሚያገለግል ከብረት የተሰራ

የቅርፅ ማውጫ::

**ደጓሽ** ስ መፅሃፍ ጠራዥ::

**ድጉስ** ስ 1. የተደጎሰ፥ የተጌጠ፥ የተሸለመ የመፅሃፍ ገበታ ሽፋን :: 2. ሰገባ፥ አሮት::

**ደጎባ**[1] ቅ በቂ የቀለም ትምህርት የሌለው፤ ትምህርት አልገባ የሚለው (ሰው)::

**ደጎባ**[2] ስ 1. የአንበጣ ኩብኩባ:: 2. ሰታ፥ ወጣት::

**ደጓሚ "ደጎመ"** ስር ተመ.

**ደጓሽ "ደጎሰ"** ስር ተመ.

**ደጭመረጭ** ስ በቆላና በወይናደጋ አካባቢ የሚበቅልና መድሃኒትነት አለው የሚባል አነስተኛ የእፅዋት አይነት::

**ደፈረ** ግ 1. ጎበዘ፥ በረታ:: 2. ጨከነ፥ ሳይፈራ ቀረ:: 3. ናቀ፥ አዋረደ፥ ዝቅ አድርጎ ተመለከተ:: *እንዴት ብትደፍረኝ ነው የጎረጥ ያየህኝ?* 4. ሴትን በግብረ ስጋ ተገናኝ (ከፍላጎቷ ውጭ በሆነ መንገድ፥ በማስገደድ)::

**ደፋር** ቅ 1. ጎበዝ፥ ብርቱ፥ ቆራጥ:: 2. ጨካኝ፥ የማይፈራ:: 3. (ዘይ.) ባለጌ፥ ሰው የማያከብር::

**ድፍረት** ስ 1. አለመፍራት፥ ቆራጥነት:: 2. (ዘይ.) ብልግና፥ ሰው አለማክበር፥ ንቀት::

**ተደፈረ** ግ 1. ተጣሰ፥ ተነካ:: (ድንበር፥ ህግ፥...):: 2. (ዘይ.) ተናቀ፥ ተዋረደ::

**ተደፋፈረ** ግ 1. ተበረታታ፥ ሳይፈራ ቀረ:: 2.ተናናቀ::

**ተደፋፈሩ** (ዘይ.) በግብረ ስጋ ተዋወቁ::

**ተዳፈረ** ግ የድፍረት ድርጊት ፈፀመ::

**አደፋፈረ** ግ አበረታታ፥ አነቃቃ፥ ገፋፋ::

**ደፈረሰ** ግ 1. ተበጠበጠ፥ ከጭቃ፥ ከአፈር፥... ጋር ተደበላለቀ፥ ጥራቱ ተበላሸ (ውሃ):: 2. ጎሸ፥ አተላ (ጠጅ፥ ጠላ፥...):: 3. (ዘይ.) ታወከ፥ ተሸበረ፥ ተረበሸ (አገር፥ ፀጥታ፥...)::

**ድፍርስ** ቅ 1. ብጥብጥ፥ ከጭቃ፥ ከአፈር፥... ጋር የተደበላለቀ፥ ያልጠራ:: 2. ከአተላ ጋር የተደበላለቀ፥ ያልጠራ (ጠላ፥ ጠጅ፥...)::

**አደፈረሰ** ግ 1. በጠበጠ፥ ከጭቃ፥ ከአፈር፥... ጋር ደበላለቀ፥ ጥራቱን አበላሸ (የውሃን፥...):: 2.ከአተላ ጋር ደበላለቀ (ለጠላ፥ ለጠጅ፥...):: 3.አወከ፥ ረበሸ፥ አሸበረ (አገርን፥ ፀጥታን፥..)::

**አደፍራሽ** ቅ አዋኪ፥ በጥባጭ::

**ደፈር** ስ የተራራ ጫፍ፥ ገመገም::

**ደፈቀ** ግ ዘፈቀ፥ ነከረ (ፈሳሽ ውስጥ)::

**ደፈቃ** ስ 1. ዘፈቃ (በውሃ ዋና ጊዜ አንዱ ሌላውን በማስጠም የሚጫወቱት ጨዋታ:: 2. (ስፖ.) በመረብ ኳስ ጨዋታ ላይ ኳስ በተቃራኒው ቡድን ሜዳ ውስጥ እንድታርፍ አክርሮ ወደ መሬት መምታት::

**ተደፈቀ** ግ ተዘፈቀ፥ ተነከረ::

**ደፈነ** ግ 1. ክፍት የነበረውን በአንድ ነገር ዘጋ፥ ገጠመ፥ ሸፈነ፥ መረገ፥ አሸገ:: 2. ቀበረ፥ ደበቀ፥ ሰወረ:: 3. ተደፈነ (አይን):: 4. የተሰጠውን ጥያቄ ሙሉ በሙሉ መለሰ፥ ሙሉውን ነጥብ አገኘ::

**በደፈናው** መዋ. በአጠቃላይ (ዝርዝር ሁኔታው ሳይገለጥ)::

**ድፍን** ቅ 1. ምንም ያልተነካለት፥ ሙሉ:: *ድፍን እንጀራ*:: 2. ምንም አይነት ቀዳዳ፥ ሽንቁር የሌለው:: 3. ያልተከፈተ፥ እሸግ (ውስጡ ባዶ ቦታ ሊኖረው ወይም ላይኖረው ይችላል):: 4. መላው፥ ጠቅላላው:: *ወሬው ድፍን አዲስ አበባ ሰማው*:: 5. (ዘይ.) ከልክ በላይ ዝምታ የሚያበዛ፥ የማይናገር:: 6. ሲያናግሩት መልስ የማይሰጥ፥ ጋግርታም:: 7. (ዘይ.) ትምህርት የማይገባው::

**ድፍን አለ** ግ 1. በጣም ጨለመ:: 2. ዝግት አለ::

**ድፍን ራስ** ድንጋይ ራስ፥ ደደብ::

**ድፍንፍን** ቅ 1. ግልፅ ያልሆነ፥ ጭፍንፍን:: 2. ልኩስኩስ፥ ርምጥምጥ፥ ስራ የማይሳካለት::

**ድፍንፍን አለ** ግ 1. በጣም ጨለመ:: 2. ተደፈነ::

**መድፍነ ፀር** ስ አንድን ሰው ጠላት እንዳይነሳበት ይረዳዋል ወይም ጠላቱ ሊያደርስበት ከሚችለው ጉዳት ሊጠብቀው ይችላል ተብሎ የሚታመንበት የአስማት አይነት::

**ተደፈነ** ግ 1. ክፍት የነበረው ቦታ ወይም ቀዳዳ ተዘጋ፥ ተገጠመ:: 2. ተጨፈነ (አይን በበሽታ ምክንያት)::

**ተዳፈነ** ግ 1. ተቀበረ፥ ተሸፈነ (እሳት፥...):: 2. (ዘይ.) በምስጢር ተይዞ፥ ተደብቆ እንዲኖር ተደረገ፥ ሳይጋለጥ ቀረ፥ ተሸፋፈነ::

**ተድፈነፈነ** ግ ተርመጠመጠ፥ ተልኩሰከሰ::

**አደፈነ** ግ ላዩ የዳነ መስሎ ውስጡ ቂም ያዘ፥ አቀበረ፥ ለገመ (ቁስል)::

**አዳፈነ** ግ 1. የእሳት ፍምን በአመድ ውስጥ ቀበረ፥ ሸፈነ (እንዳይጠፋ):: 2. (ዘይ.) እንዳይገለጥ ወይም ተሸፋፍኖ እንዲቀር አደረገ (አንድን ነገር ወይም ጉዳይ)::

**አዳፈነበት** በጥይት፥... መታው፥ ገደለው::

**አድፈነፈነ** ግ 1. አጭፈነፈነ፡ 2. አልኩሰኩሰ፥ አርመጠመጠ:: 3. ደባበቀ::

**ደፈደፈ** ግ 1. እንክሮንና ቂጣን ከጥንስስ ጋር በውሃ ለወሰ፥ አዋሃደ፥ በወፍራሙ በጠበጠ::

2. መረገ፥ ለደፈ:: *መድሃኒቱን ቁስሉ ላይ ደፈደፈ*:: 3. (ዘይ.) ሳከከ፥ አሳበበ:: *ጥፋቱን በሙሉ በወንድሙ ላይ ደፈደፈ*::

**ድፍድፍ** ስ 1. በወፍራሙ በውሃ ተለውሶ የተዘጋጀ የጥንስስ፥ የእንኩሮ፥ የቂጣ ውሁድ፥ ድብልቅ:: 2. ሳይጠራ በድፍድፍ መልክ የሚገኝ ማንኛውም ጥንተ ነገር:: *የነዳጅ ዘይት ድፍድፍ*::

**ድፍድፍ አለ** ግ ወፈረ (ለቅርፅ)::

***ደፈደፈ**

**ደፈደፍ (ደፈዳፋ)** ቅ ርብትብት::

**ደፍደፍ አለ** ግ ተንደፈደፈ::

**ተንደፋደፈ** ግ 1.ተንፈራፈረ፥ ተንፈራጠጠ:: 2. ተፍጨረጨረ፥ ተጣጠረ:: 3. ተርመጠመጠ፥ ተልከሰከሰ::

**አንደፋደፈ** ግ 1. አንፈራፈረ፥ አንፈራገጠ:: 2. አርመጠመጠ::

**ደፈጠ** ግ 1 ሸመቀ፥ ተደበቀ:: 2. አጠመደ::

**ደፈጣ** ስ ሽመቃ::

**የደፈጣ ውጊያ** ስ ሽምቅ ውጊያ::

**ደፋጣ** ቅ ሰዋራ፥ ደባቃ (ቦታ)::

**አደፈጠ** ግ አሸመቀ፥ ተደበቀ::

**አድፋጭ** ቅ 1. ሸማቂ:: 2. (ዘይ.) ሁኔታዎች እስከሚረጋጉ ወይም እስከሚለይላቸው ድረስ ድምፁን አጥፍቶ የሚቀመጥ::

**ደፈጠጠ (ደፈጨጨ)** ግ ረገጠ፥ ጸመጠ፥ ጨፈለቀ፥ ጻጠ::

**ደፍጣጣ(ድፍጥጥ፥ ድፍጥ)** ቅ 1. ቅርፁ የተበላሸ፥ የተጠፈጠፈ:: 2.አፍንጫው ጠፍጣፋ የሆነ::

**ተደፈጠጠ** ግ 1. ተረገጠ፥ ተጸመጠ፥ ተጨፈለቀ፥ተጻጠ:: 2. ተጠፈጠፈ፥ ደፍጣጣ ሆነ::

***ደፈጠፈጠ**

**ድፍጥፍጥ አለ** ግ ተድፈጠፈጠ::

**ድፍጥፍጥ አደረገ** ግ አድፈጠፈጠ::

**ተድፈጠፈጠ** ግ ተፍረጠረጠ::

**አድፈጠፈጠ** ግ አፍረጠረጠ::

**ደፈጣ "ደፈጠ"** ስር ተመ.

**ደፈጨጨ "ደፈጠጠ"** ን ተመ.

**ደፈጫ** ስ እብ ::

**ደፋ** ግ 1. ባፍጢሙ ጣለ፥ ፈነገለ:: 2. አፈሰሰ፥ ከነበለ (ፈሳሽን):: 3. ዘረገፈ፥ ገለበጠ (ፈሳሽ ያልሆነን ነገር):: 4. አዘነበለ፥ ወደ አንድ በኩል አመዘነ:: 5. አፋን ወደ መሬት አድርጎ አስቀመጠ (እቃን):: 6. በአደራ አስቀመጠ (ሳይሸጥ የቀረን እቃ)::

**ደፋት** ያለ ውዴታዋ በግብረ ስጋ ተገናኛት::

**ደፋው** ገደለው::

**ደፋ ቀና አለ** ግ በስራ ተጠመደ፥ ለፋ፥ ባተሌ ሆነ::

**ደፋታ** ስ ቁልቁለት፥ ሽርታታ::

**ድፋት** ስ የድጓ ዜማ ምልክት፥ ምልክቱም (ለ) ነው::

**ድፌት** ስ በቆብ ቅርፅ የሚሰራ የሹርባ አይነት::

**ድፎ** ስ የአበሻ ትልቅ ዳቦ::

**ደፋፋ** ግ 1. አፋሰሰ:: 2. አባከነ:: 3. በርካሽ ቶሎ ቶሎ ሸጠ::

**ደፋ ደፋ አለ** ግ በመቻኮል ቶሎ ቶሎ ሄደ::

**ደፋ ደፋ አደረገ** ግ ደፋፋ፤ ቶሎ ቶሎ ፈፀመ፥ አደረገ::

**ድፍት ብሎ ቀረ** ሞተ (ብዙውን ጊዜ ባልታሰበ ቀንና ቦታ)::

**ድፍት ብሎ አደረ** ጠጡን አደረ::

**ተደፋ** ግ 1. ተፈነገለ፥ ወደቀ:: 2. ፈሰሰ፥ ተከነበለ:: 3. አዘነበለ (ወደ አንድ በኩል)::

**ተደፋፋ** ግ ተድፋፋ::

**ተዳፋ** ግ ተቆለቆለ፥ ወደታች ወረደ::

**ተዳፋት** ስ ቁልቁለት::

**ተድፋፋ** ግ ባከነ፥ ያለ አግባብ ቶሎ ቶሎ እንዲያልቅ ሆነ::

**አዳፋ** ግ ገፈተረ፥ አንገላታ፥ አጣደፈ፥ አቻኮለ::

**አድፋፋ** ግ አባከነ፥ ያለ አግባብ እንዲያልቅ አደረገ::

**አድፋፊ** ቅ አባካኝ::

**ደፋር " ደፈረ"** ስር ተመ.

**ደፋታ "ደፋ"** ስር ተመ.

**ደፋጣ "ደፈጠ"** ስር ተመ.

**ደፋፋ "ደፋ"** ስር ተመ.

**ደፍ** ስ የግራና የቀኝ መቃኖችን የሚያቆሙበት ከመዝጊያ ስር የሚገኝ አግዳሚ እንጨት(ቤት ስር የ"በር"ን ስእል ተመ.)::

**ደፍ ደፍ አለ "*ደፈደፈ"** ስር ተመ.

**ደፍዳፋ "*ደፈደፈ"** ስር **"ደፈደፍ"**ን ተመ.

**ደፍጣጣ "*ደፈጠጠ"** ስር ተመ.

**ዱ** ፡የ **"ደ"** ፊደል ካእብ ዘር::

**ዱለታ "ዶለተ"** ስር ተመ.

**ዱለት**[1] ስ ከተከተፈ የበግ ወይም የፍየል ጨጓራና ጉበት በድልሀና በቅቤ የሚዘጋጅ ምግብ (እንደአስፈላጊነቱ አንዳንድ ጊዜ የሽንጥ ስጋ

በመጡ ይታከልበታል)::

**ዱለት**[2] **"ዶለተ"** ስር **"ዱለታ"** ን ተመ.

**ዱላ** ስ 1. ለመምቻ፥ ለመመርኮዣ፥... እንዲያገለግል ሆኖ ከእንጨት የሚዘጋጅ በትር:: 2. (ዘይ.) ድብድብ፥ ጠብ::

**በዱላ ተለቀቀበት (ተለቀቀው)** በዱላ ደበደበው::

**በዱላ አንቆራጠጠ** እየተከታተለ በዱላ መታ፥ ነረተ፥ ደበደበ::

**በዱላ ከካው** ጭንቅላቱን በዱላ ፈነከተው::

**ዱላ ቀረሽ ጠብ** ስ ከዱላ በመለስ በቃላት ወይም በስድብ ብቻ የሚካሄድ ከፍተኛ ጠብ::

**ዱለኛ** ቅ ተደባዳቢ ::

**ዱልዱም "ዶለዶመ"** ስር ተመ.

**ዱማች** ስ ምሳ፥ የቀንኛ::

**ዱር** ስ ጫካ፥ ደን፥ ሰው ያልሰፈረበት ቦታ::

**ዱር ቤቴ አለ** ወመኔ ሆነ፥ እቤቱ ማደር ተወ፥ ወነበደ፥ ሸፈተ::

**ዱር አደሬ** ቅ 1. ቤት የለሽ:: 2. ዱርዬ::

**ዱርዬ** ቅ ወመኔ::

**ዱርር "*ዶረረ"** ስር ተመ.

**ዱርሸት** ስ ቅጠሉ የሚከረፋ፥ የሚገማ የሃረግ አይነት::

**ዱርዬ "ዱር"** ስር ተመ.

**ዱሮ(ድሮ)** ስ 1. ጥንት፥ ቀድሞ የነበረው ጊዜ:: *በድሮ በሬ ያረሰ የለም*:: ተው.ግ. 2. ከዚህ ፊት በነበረው ጊዜ:: *ድሮ የገዛው ልብስ አለ::*

**ዱሽ** ስ 1. ኩንትሽ፥ ጣቶቹ የተቆረጡ እጅ ወይም እግር:: 2. ቆማጣ::

**ዱቄት** ስ የደቀቀ፥ የተፈጨ፥ የላመ (ብዙውን ጊዜ እህል)::

**ዱቄት ሆነ** በጣም ደቀቀ፤ ተሰባበረ::

**ዱቅንዱቅ (ዱቀንዱቂት)** ስ የትል አይነት::

**ዱቢት** ስ 1. ወፍራም የሽንብራ እንጀራ፥ ሰረባት:: 2. በአሳ አምሰያ ከሽንብራ የሚዘጋጅ ትንሽ ጥቢኛ::

**ዱባ** ስ 1. ተቀቅሎ የሚበላ ድቡልቡል ወይም ሞላላ የሆነ ትልቅ ፍሬ ያለው ሃረግማ ተክል፤ ፍሬውም ዱባ ይባላል:: 2. (ዘይ.) አጭርና ወፍራም የሆነ (ሰው)::



ዱባ 1ኛ ፍቺ

**[የ] ዱባ ፍሬ** ስ ነጭና ጠፍጣፋ የሆነ የዱባ ተክል ዘር::

**ዱቤ** ስ የእቃውን ወይም የአገልግሎቱን ዋጋ በሌላ ጊዜ ለሚከፈል፥ በገዥና በሻጭ መካከል የሚካሄድ የገበያ ስምምነት::

**ዱቬ** ስ በፋብሪካ ተዘጋጅቶ የሚቀርብ የዱቄት አይነት::

**ዱቬ በርበሬ** ስ ዛላው ወፍራምና ረዥም የሆነ የማይፋጅ በርበሬ::

**ዱብ**

**ዱብ እዳ** ስ ድንገተኛ፥ ያልታሰበና ያልተፈለገ ነገር:: *የመሬትና የትርፍ ቤት መወረስ ለቀጅ ዱብ እዳ ነበር የሆነባቸው::*

**ዱብ አለ** ግ 1. ከላይ ወደታች ዘለለ፥ ጡብ አለ:: 2. ወደቀ፥ ጠብ አለ (ዝናብ፥ እንባ)::

**ዱብ አደረገ** ግ ጣለ::

**ዱብ ዱብ አለ** ግ 1. አንድ ቦታ ላይ ሆኖ ደጋግሞ ዘለለ፤ እንጣጥ እንጣጥ አለ:: 2. ጠብ ጠብ አለ፥ ወዳደቀ::

**ዱብ ዱብ አደረገ** ግ 1.ጠብጠብ አደረገ፥ አፈሰሰ (እንባን፥ ዝናብን፥...):: 2. ጣል ጣል አደረገ፥ አንጠባጠበ::

**ዱታ**

**ዱታ ነኝ አለ** ያዙኝ ልቀቁኝ አለ፥ ለመማታት፥... ተጋበዘ ::

**ዱካ**[1] **"ደካ**[1]**"** ስር ተመ.

**ዱካ**[2] ስ በርጩማ፥ ግርንቡድ::

**ዱያታም "ደዌ"** ስር ተመ.

**ዱያት "ደዌ"** ን ተመ.

**ዱዳ(ዲዳ)** ቅ 1. መናገር የማይችል (ሰው):: 2. (ዘይ.) ሃሳቡን ወይም የልቡን አውጥቶ፥ አብራርቶ፥ ግልፅ አድርጎ መናገር የማይችል::

**ዱድማ** ዝ.ከ.

**ዱግ** ስ 1. ቀደም ባለው ጊዜ የሹም ወኪል ወይም እንደራሴ መጠሪያ:: 2. ተወላጅ፥ ዝቅተኛ፥ የበታች ሹም::

**ዴ** የ "ደ" ፊደል ሳልስ ዘር::

**ዴሞትፌር** ስ የጠመንጃ አይነት::

**ዲሞክራሲ** ስ 1. ስለጣን በጠቅላላው ህዝብ በሚመረጡ ተወካዮች እጅ የሚሆንበት ስርአተመንግስት:: 2. የተለያዩ ፖለቲካዊ አመለካከቶችን፥ የንግግር፥ የፅሁፍ፥ ሰላማዊ ሰልፍ የማድረግ፥... ነፃነትን የሚፈቅድ ስርአት::

**ዲሞክራሲያዊ** ቅ ህዝባዊ::

**ዲሞክራት** ስ አፍቃሪ ዲሞክራሲ የሆነ ሰው::

**ዲሬክተር(ዳይሬክተር)** ስ 1. የትምህርት

ቤት ስራ መሪ፤ ርእሰ መምህር:: 2. ስራ አስኪያጅ፤ ስራ መሪ::

**ዴር** ስ 1. ጥሩር፥ ከብረት የተሰራ ልብስ:: 2. የድንጋይ አጥር:: 3. በሰንጠረዥ መጫወቻ ውስጥ ያለ ግንብ:: 4. ፈረሰኛ::

**ዲስከስ(ዲስክ)** ስ ከድንጋይ፥ ከእንጨት ወይም ከብረት የሚሰራ፥ ቅርፁ ክብና ጠፍጣፋ የሆነ፥ ለውርወራ ስፖርት የሚያገለግል እቃ::

**ዲስኩር** ስ ብዙ ሰው በተሰበሰበበት የሚደረግ ንግግር::

**ዲቃላ** **"ደቀለ"** ስር ተመ.

**ዲባታማ** ስ መልኩ ወደዳለቻነት የሚያደላና ፊካ ያለ ወይን ጠጅ የሚመስል፥ እንደ ማጭድ ወደፊት የጎበጡ ቀንዶች ያሉት፥ በበረሃማ ስፍራዎች የሚገኝ፥ አንገተ ረጅም የሆነ፥ እፅዋት በል እንስሳ ::

**ዲብ** ስ ከፍታው አነስተኛ የሆነ የአፈር ጉብታ፥ ቁልል ታ::

**ዲና** ስ አመፀኛ፥ አደጋ ጣይ (ሰው)::

**ዲና ደመታ** አደጋ ጣለ::

**ዲናሞ** ስ የእንፋሎትን ወይም የውሃን፥...ሃይል ወደ ኤሌክትሪክ ሃይል የሚለውጥ ሜካኒካዊ መሳሪያ::

**ዲናር** ስ የገንዘብ ስም::

**ዲዛይን** ስ አንድ ነገር በተጨባጭ ከመሰራቱ በፊት በወረቀት ላይ ተስሎ የሚታይ ንድፍ::

**ዲያቆን** **"ዳቆነ"** ስር ተመ.

**ዲያቢሎስ(ዲያብሎስ)** ስ 1. የሰይጣን አለቃ:: 2. (ዘይ.) ርጉም፥ ክፉ::

**ዲደን** ስ ብርዳማ የሆነ ሃይለኛ ነፋስ::

**ዲዳ** **"ዱዳ"** ን ተመ.

**ዲግሪ** ስ 1. በዩኒቨርሲቲ ደረጃ ትምህርቱን ተከታትሎ ለፈፀመና ፈተናውን ላለፈ ሰው የሚሰጥ የምስክር ወረቀት፤ የትምህርት ማስረጃ:: 2. የማእዘን ወይም ዘዌ መለኪያ አሃድ:: 3. የሙቀት መጠን መለኪያ አሃድ:: *በመቶ ዲግሪ ሴንቲ ግሬድ ውሃ ወደ እንፋሎትነት ይለወጣል::*

**የዲግሪ ፕሮግራም [ትምህርት]** ስ የአስራ ሁለተኛ ክፍልን ብሄራዊ ፈተና ካለፉ በሂላ በዩኒቨርስቲ ውስጥ በተለያዩ የትምህርት ዘርፎች ለአራት አመት ወይም ከዚያ በላይ የሚሰጥ የትምህርት ፕሮግራም::

**ዲፕሎማ (ዲፕሎም)** ስ በተወሰነ የትምህርት ዘርፍ ላይ ተገቢውን ስልጠና ወይም እውቀት ላገኘ የሚሰጥ የምስክር ወረቀት ወይም የትምህርት ማስረጃ::

**ዲፕሎማሲ** ስ በሃገሮች መካከል ሊኖር የሚገባውን ግንኙነት አስመልክቶ በየውጪ ጉዳይ መስሪያ ቤቶች በኩል በተመደቡ የኤምባሲ ስራተኞች የሚከናወን ስራ፤ ከላይ የተጠቀሰውን ስራ የማከናወን ዘዴ፥ ጥበብ::

**ዲፕሎማት** ስ የዲፕሎማሲን ስራ የሚያከናውን ግለሰብ፤ የኤምባሲ ከፍተኛ ባለስልጣን::

**ዲፕሎም** **"ዲፕሎማ"** ን ተመ.

**ዳ** የ **"ደ"** ፊደል ራብእ ዘር::

**ዳሀ(ዳኸ)** ግ በእግርና በእጁ ሄደ (በተለይ ለህፃን)::

**ዳህራይ** **"ደሃራይ"** ን ተመ.

**ዳለቻ(ዳለች)** ቅ አመድማ፥ ቡላ፥ ግራጫ ቀለም ያለው::

**ዳለጠ** ግ ሟለጠ::

**ዳላጣ** ቅ ድጥ፥ የሚያሟልጭ::

**አዳለጠ** ግ አሟለጠ፥ አዳጠ፥ አሟለጨ::

**ዳሌ** ስ ከጭን በላይ፥ ከወገብ በታች ያለ የሰውነት ክፍል::

**ዳልጋ** ስ በበሬ፥ በላም፥... አንገት ላይ ከማንቁርት እስከ ፍርንባ የተንጠለጠለ ቆዳ::

**[የ] ዳልጋ አንበሳ** ስ አሸዋማ ቀይ ሆኖ ወደ ሆዱ ነጣ የሚልና ወደ ጉያውና እግሮቹ አካባቢ ደብዘዝ ያሉ ጠቃጠቆ ምልክቶች ያሉበት፥ የሂላ እግሮቹ ከፊተኛቹ ይበልጥ ረዘም የሚሉ፥ ታላላቅ ቋጥኞች በሚገኙባቸው ኮረብታዎች ላይ የሚኖር፥ የአንበሳ ዘር የሆነ የዱር አውሬ (ስእሉን የዱር\እንስሳ ስር ተመ.)::

**ዳመነ** ግ ደመና ሆነ::

**ዳመና(ደመና)** ስ በእንፋሎት ወይም በተን መልክ ከመሬት ከተነሳ በሂላ የተነደፈ ጥጥ በመምሰልና ልዩ ልዩ ቅርፅ በመያዝ በሰማይ ላይ ሲንሳፈፍ የሚታይ ረቂቅ የሆነ የውሃ ነጠብጣብ ክምችት::

**ዳመና አረገዘ(ጣለ)** ዳመና አንገዋበበ፥ ዳመና ሆነ፥ ሊዘንብ የተቃረበ መሰለ::

**ድምንምን አለ** ግ ጥቁርቁር፥ ጭልምልም አለ::

**ተድመነመነ** ግ ጠቋቆረ፥ ጭልምልም አለ::

**አዳመነ** ግ ዳመነ::

**አድመነመነ** ግ አጠቋቆረ፥ አጨላለመ::

**ዳመጠ** ግ 1. ዳጠ፥ ደፈጠጠ:: 2. አባጣ ጎባጣ የነበረውን እንዲስተካከል ወይም ልስቅ እንዲል አደረገ:: 3. የተፈለቀቀን ጥጥ በመዳመጫ ድንጋይ ላይ በማድረግና አጭርና ቀጭን በሆነ የብረት ዘንግ ከላይ ወደታች በመዳጥ ጥጡን ከፍሬው ለየ::

**መዳመጫ** ስ ጥጥን ለመዳመጥ የሚያገለግል ጠፍጣፋና ለስላሳ ድንጋይ::

**የመዳመጫ ብረት** ስ የተፈለቀቀን ጥጥ ከፍሬው ለመለየት የሚያገለግል አጭር፥ ቀጭንና ለስላሳ የሆነ የብረት ዘንግ።

**ዳመጠ** ስ 1. በመዳመጫ ተዳምጦ ከፍሬው የተለየ ጥጥ። 2 (ዘይ.) አፍንጫ ደፍጣጣ (ሰው)።

**ዳማ**[1] ቅ ደም የሚመስል የቀይ አይነት። *ዳማ ፈረስ።*

**ዳማ**[2] ስ ከብና ጠፍጣፋ ሆነው ከፕላስቲክ ወይም ከእንጨት፥... የተሰሩ ጠጠሮችን በሰሌዳ ላይ በማንቀሳቀስ የሚደረግ ጨዋታ።

**ዳማከሴ** ስ ሰዎች ለመድሃኒትነት የሚጠቀሙበት የእፅዋት አይነት።

**ዳምጠው** ስ መንገድ ሲሰራ በትላልቅ የብረት መዳመጫዎች ንጣፉን እየዳመጠ የሚያስተካክል እጅግ ከባድ ተሽከርካሪ።

**ዳሞትራ** ስ መልኳ ሽረሪት የሚመስል ጥቁርና ተናዳፊ የሆነች ነፍሳት።

**ዳሞት ወይራ** ስ እንደ ወይራ ጠንካራ የሆነ የዛፍ አይነት።

**ዳረ** ግ አጋባ፥ ትዳር አስያዘ፤ ሴትና ወንድን በትዳር አጣመረ፤ ጋብቻ እንዲመሰርቱ አደረገ።

**መዳሪያ** ስ ልጆች በተጋቡ ጊዜ ከወላጆች የሚሰጥ ሃብት፥ ንብረት።

**ዳረገ** ግ 1. ድርጎ ፈቀደ፥ እንዲሰጥ አደረገ። 2. (ዘይ.) አጋለጠ፥ አሳልፎ ሰጠ።

**ዳረጎት** ስ 1. ድርጎ። 2. ስጦታ፥ ጉርሻ።

**ድርጎ** ስ 1. በተወሰነ ጊዜ ለድርጎኛ የሚሰጥ የተወሰነ መጠን ያለው ምግብ፥ መጠጥ፥...። 2. እንደ እርቦ ያለ መስፈሪያ፥ መለኪያ።

**ድርጎኛ** ቅ በተወሰነ ጊዜ የተወሰነ መጠን ያለው ምግብና መጠጥ፥... የሚሰጠው ወይም የሚቀበል ሰው።

**ተዳረገ** ግ 1. ተሰጠ። 2. ለችግር፥ ለመከራ፥... ተጋለጠ።

**አደራጎተ** ግ ዳረጎት ሰጠ።

**ዳሩ** ታዲያ፥ ግን። *ፈልጌው ነበረ፤ ዳሩ ምን ያደርጋል ላላገኘሁትም።*

**ዳሩ ግን** የሆነ ሆኖ፥ ግን፥ ሆኖም፤ ምን ያደርጋል፥ ምን ይሆናል። *ትምህርቱን ተከታትዬ ነበር፤ ዳሩ ግን ፈተናውን አልወሰድኩም።*

**ዳራ** "ደሃራይ"ን ተመ.

**ዳር (ዳርቻ)** ስ 1. ጠርዝ፥ ጫፍ። 2. አጠገብ። *ቤቱ ከመንገድ ዳር ነው።* 3. ከአንድ ከተወሰነ ክልል ውጭ። *ኳሷ ወደዳር ወጣች።* 4. መጨረሻ፥ ጫፍ። *ነገሩ ዳር ሳይደርስ አልቀረም።*

**ዳር አገር** ጠረፍ። *ሰውዬው ዳር አገር ይኖራል።*

**ዳር አደረሰ** ፍፃሜ አደረሰ።

**ዳር ወጣ** 1. ይፋ ሆነ። *ነገሩ ዳር ወጣ።* 2. ሊያልቅ ደረሰ። *ነገሩ ዳር ደርሷል።*

**ዳር ዳር አለ** 1. ከጀለ። 2. አመነታ። *መወሰን ላቅቶት ዳር ዳር ይላል።*

**ዳር እስከ ዳር** በሙሉ፥ በጠቅላላው። *ወሬውን ህዘቡ ዳር እስከ ዳር ሰምቶታል።*

**ዳሰ** ግ 1. የወፍጮውን መጅ በሃይል ሳይጫን ወይም ሳያጠብቅ እንደ አሻሮ ያለውን እህል በቀላሉ ፈጩት ፈጩት አደረገ። 2. ዳመጠ፥ ደፈጠጠ።

**መዳሻ** ስ ትልቅ የወፍጮ መጅ።

**ዳሰሰ** ግ 1. ዳበሰ፥ ነካ፥ ነካካ። 2. ቃኘ፥ ፈለገ።

**ዳሰሳ** ስ 1. ዳበሳ፥ መነካካት። 2. አንድን ጉዳይ በተመለከተ የሚደረግ ቅኝት ወይም አጠቃላይ የሆነ ፍለጋ ወይም የግኝቱ ገለፃ።

**በዳሰሳ** በግምት፥ በመላ።

**ዳስ** ስ ብዙውን ጊዜ ድግስ ያለባቸው የገጠር ሰዎች እንግዶቻቸውን በአንድነት ለመጋበዝ ያስችላቸው ዘንድ እንደ አጠና፥ ጨፈቃና ቅጠላ ቅጠል ባሉ ነገሮች የሚሰሩት ጊዜያዊ መጠለያ።

**ዳስ ጣለ** ዳስ ሰራ፤ አዘጋጀ።

**ዳስተር** ስ በቁጥር ሰሌዳ ላይ በጠመኔ የተፃፈን ፅሁፍ ለመጥረግ፥ ለማጥፋት የሚያገለግል ፀጉራም መጥረጊያ።

**ዳሸቀ** ግ 1. ተረገጠ፥ ታሸ፥ ደቀቀ። 2. በሰበሰ፥ በካ (ጭቃ)። 3. ደከመ፥ አቅም የሌለው ሆነ። *ኢኮኖሚው ዳሽቋል።*

**አዳሸቀ** ግ በሃይል መታ፥ ረገጠ።

**ዳቆነ** ግ የድቁና ማእረግ ተቀበለ።

**ድቁና** ስ የዲያቆንነት ማእረግ፥ ስልጣን።

**ዲያቆን** ስ በድቁና ማእረግ በቤተክርስቲያን የሚያገለግል ቀዳሽ፥ ካህን።

**አዳቆነ** ግ የዲያቆንነት ማእረግ ወይም ስለጣን ሰጠ።

**ዳበረ** ግ 1. ፋፋ፥ ወፈረ፥ ተመቸው። 2. ሰፋ፥ ተስፋፋ፥ ብዛት አገኘ። 3. ለተክል፥ ለሰብል የሚስማማና የሚጠቅም ጥሩ አፈር ሆነ። 4. አደገ፥ ላቀ፥ ጨመረ።

**አዳበረ** ግ አሳደገ፥ ቀደም ሲል በነበረው ላይ በመጨመር አስፋፋ (ለምሳሌ ሃሳብን)።

**ማዳበሪያ** ስ አፈር ለተክል ወይም ለሰብል ተስማሚና ጠቃሚ ነገር እንዲኖረው የሚያደርግ እንደ ፍግ ያለ ወይም በፋብሪካ ተሰርቶ የሚወጣ የልዩ ልዩ ንጠረነገሮች ውሁድ።

**አዳባሪ ሃሳብ** ስ አጎላማሽ፥ አጠናካሪ ሃሳብ።

**ዳበሰ** ግ 1. ነካካ፥ ዳሰሰ። 2. ፈተሸ፥ መረመረ፥

ፈለገ (በእጅ በመነካካት)::

**ዳበሳ** ስ ዳሰሳ::

**በዳበሳ** 1. ማየት በማይቻልበት ሁኔታ በእጅ ብቻ በመነካካትና በመረዳት:: *ክበሪቱን በዳበሳ ላገኘሁት*: 2. በግምት፥ በመላ፣ በዳሰሳ::

**ዳቢት** ስ የጎድን ዘርፍ፣ ከብራኳ ጋር የተያያዘ የትከሻ ስጋ::

**ዳባ** ስ 1. የበሬ ቆዳ፣ ቁርበት:: 2. ከበሬ፥ ከኣጋዘን፥...ቆዳ የሚሰራ የመናንያን ልብስ፥ ኣፅፍ::

**ዳባ ለባሽ** ስ የበሬ፥ የኣጋዘን፥... ቆዳ የሚለብስ መናኝ መነኩሴ::

**ዳቤ** ስ ሊጡ በወፍራሙ ተዘጋጅቶ የሚጋገር ወፍራም እንጀራ::

**ዳብሬ** ስ ከእንስራ ኣነስ የሚል ትልቅ ገንቦ::

**ዳቦ** ስ 1. ብዙውን ጊዜ የስንዴ ዱቄት በወፍራሙ ተቦክቶ በተለያየ ቅርፅና መጠን የሚዘጋጅ ምግብ:: 2. (ዘይ.) ወፍራም (እንጀራ ወይም መጠጥ)::

**ዳቦ ደፋ** ዳቦ (ድፎ) ጋገረ:

**ዳቦ ቆሎ** ስ በኣብዛኛው የስንዴ ወይም የፍርኖ ዱቄት በወፍራሙ ከተቦካ በሂዋላ ሊጡ እየተድበለበለ በቆሎ ቅርፅ ተዘጋጅቶና ተቆልቶ የሚቀርብ የምግብ ኣይነት::

**ዳቦት** ስ ችቦ::

**ዳተኛ** ቅ ቸልተኛ፣ ልግመኛ::

**ዳነ** ግ 1. ህመሙ ለቀቀው፥ ተፈወሰ፥ ታሞ የነበረው ጤነኛ ሆነ፥ ሻረ:: 2. ተረፈ፥ ኣመለጠ:: *ደርሶ ከነበረው ኣደጋ እርሱ ብቻ ዳነ::*

**መዳኛ** ስ 1. መትረፊያ፥ ማምለጫ:: *መዳኛ የለውም*: 2. መድሃኒት::

**መድሃኒት(መዳኒት)** ስ 1. ከተለያዩ ስራስሮች፥ ማእድናት ቅጠላ ቅጠሎች፥... በዱቄት፥ በእንክብል፥ በቅባት፥ በፈሳሽ፥... መልክ የሚዘጋጅ የህመም መፈወሻ:: 2. ኣብነት:: 3. በጤና ላይ ጉዳት የሚያስከትል መተት፥ ድግምት፥ ስራይ፥...::

**መድሃኒት ቀመሰ** 1. የኮሶ መድሃኒት ጠጣ:: 2. በጠላት የተዘጋጀ ጎጂ መድሃኒት ተደረገበት (በምግብ ወይም በመጠጥ ኣማካይነት)::

**መድሃኒት ነክቶታል** መጥፎ መተት፥ መድሃኒት ተደርጎበታል ::

**መድሃኒት ቀማሚ** የተለያዩ መድሃኒቶችን በተለያየ መልክ የሚያዘጋጅ ባለሙያ ::

**መድሃኒት ቤት** ስ መድሃኒት የሚሸጥበት መደብር ::

**መድሃኒተኛ** ስ 1. ባለመድሃኒት፥ መድሃኒት ኣዋቂ:: 2. ጠላቶቼ ናቸው ብሎ በሚገምታቸው ሰዎች ላይ ጎጂ መድሃኒት የሚያደርግ ሰው ::

**መድን(መድህን)** ስ ዋቢ፥ ዋስትና ::

**ተዳነ** ግ ዋቢ፥ መድን ሆነ:: *ማን ተዳነህ* ::

**ኣዳኝ** ቅ ፈዋሽ ::

**ዳንስ "ደነሰ"** ስር ተመ.

**ዳንኪራ** ስ 1. ጭፈራ፥ ድለቃ፥ ዝላይ:: 2. ሽብሽባ፥

**ዳንኪራ መታ /ረገጠ** ጨፈረ፥ ደለቀ::

**ዳንዳ "ደንዳ"** ን ተመ.

**ዳንዴ** ቅ 1. ጠረንገሎ፥ ጠብደል:: 2. (ዘይ.) ወንበዴ፥ ቀማኛ ::

**ዳንግሌ በግ** ስ ቅላቱ እሳት የሚመስል ቀይ በግ::

**ዳኘ** ግ የከሳሽንና የተከሳሽን፣ የበዳይንና የተበዳይን ክርክር ወይም ጉዳይ ሰምቶ ፍርድ ሰጠ::

**ዳኛ** ስ 1. ኣንድን ጉዳይ ኣስመልክቶ ብያኔ፥ ፍርድ፥ ውሳኔ፥...ለመስጠት ስልጣን ያለው ሰው:: 2. (ስፖ.) በኣንድ ስፖርታዊ ውድድር ወቅት እንደ ውድድሩ ኣይነት ከሜዳው ውጭ ወይም ከሜዳው ውስጥ በመሆን የስፖርት ህጎች መከበርን የሚቆጣጠርና ውሳኔ የሚሰጥ::

**ዳኛ ረገጠ** ኣልዳኝም ኣለ፥ የዳኛን ፍርድ ኣንኳሰሰ ::

**ዳኛ ቀጠነኝ ኣለ** ዳኛን ናቀ ::

**የዳኛ ራት** ስ ወደ ኣንድ ኣካባቢ ለሄደ ባለስልጣን የኣካባቢው ነዋሪ ኣዋጥቶ ያቀርበው የነበረ ምግብና መጠጥ ::

**ዳኝነት** ስ የመፍረድ፥ የመወሰን፥ የመበየን ተግባር ::

**ዳኝነት ገባ** 1. የተወሰነበትን የዳኝነት መቀጫ ከፈለ:: 2. የዳኝነት መቀጫ ተጣለበት ::

**የዳኝነት** የዳኝነቱን ስራ ላከናወነው ፍርድ ቤት ተረቺው የሚከፍለው ገንዘብ ::

**ተዳኘ** ግ ለህግ ተገዛ፥ ታዘዘ፥ የዳኛን ብያኔ ተቀበለ፥ ስርኣት ያዘ ::

**ኣዳኝ** ግ ለዳኛ አቤት ኣለ፥ ከሰሰ ::

**ዳከረ** ግ 1. ላቆጠ፥ ተለወሰ:: (ጭቃ ውስጥ):: 2. (ዘይ.) በጣም ለፋ፥ ደከመ፥ ማሰነ ::

**ኣዳከረ** ግ 1. ኣላቆጠ፥ ለወሰ:: 2. በጣም ኣለፋ፥ ኣማሰነ ::

**ኣዳካሪ** ቅ በማይመለከተው ጉዳይ ውስጥ ጥልቅ የሚል፥ ዘባራቂ፣ የሰው ጉዳይ የሚያበላሽ ::

**ዳካ** ስ ብዙውን ጊዜ ለማቡኪያ የሚያገለግል እንደ ዋዲያት ያለ እቃ ::

**ዳክዬ** ስ የእግሮቹ ጣቶች እርስ በርሳቸው በስስ ቆዳ የተያያዙ÷ ምንቃሩ ጠፍጠፍ የሚል÷ አንገቱና እራሱ ላይ የሚያብለጨልጭ ግራጫ ቀለም ያለው÷ በወንዝ÷ በባህር ወይም በየብስ የሚኖር የአሞራ አይነት(ስእሉን አሞራ ስር ተመ.)::

**ዳዊት(መዝሙረ ዳዊት)** ስ በመፅሃፍ ቅዱስ ውስጥ የሚገኝ የፀሎት መፅሃፍ ክፍል ወይም ራሱን ችሎ የተዘጋጀ የዚሁ የፀሎት መፅሃፍ መጠሪያ::

**ዳዊት ደገመ** 1. መፅሃፈ ዳዊትን ተምሮ ጨረሰ:: 2. መፅሃፈ ዳዊትን በማንበብ ፀለየ÷ፀሎት አደረገ ::

**ዳዊት ደጋሚ** ስ 1. ፀሎተኛ(ዳዊትን በማንበብ):: 2. ከዳዊት ትምህርት በስተቀር ተወማሪ ሌላ ትምህርት የሌለው::

**ዳዊት አስደገመ** 1. ዳዊት ተምሮ እንዲጨርስ አደረገ:: 2. የዳዊት ፀሎት እንዲፀለይለት አደረገ::

**ዳዋ** ስ ጥሻ::

**ዳውላ** ስ 1. ሃያ ቁና የሚይዝ ትልቅ ስልቻ:: 2. በጭነት ከብት ጀርባ ላይ የሚደረግ መደላድል÷ የቁርቋሬ መከላከያ:: 3. (ዘይ.÷ ስድብ) ጠብደል::

**ዳውጃ** ስ ከቄጤማና ከቃጫ የሚሰራ ምንጣፍ::

**ዳዳ** ግ ከጀለ÷ማድረግ ፈለገ::

**ዳዴ** ስ ህፃን ልጅ በሌላ ሰው እየተደገፈ የሚያደርገው የመራመድ ልምምድ ወይም ሙከራ::

**ዳዴ አለ** ግ 1. ለመራመድ ሞከረ (ህፃን):: 2. ቀስ እያለ ሄደ:: 3. እድገቱ ፍጥነት በሌለው ሁኔታ ሆነ::

***ዳገተ**

**ዳገት** ስ አቀበት፤ ወደፊት ሲሄዱ ከፍ እያለ የሚሄድ አስቸጋሪ መንገድ ወይም ቦታ፤ የቁልቁለት ተቃራኒ::

**አዳገተ** ግ አስቸገረ÷ አቃተ::

**አዳጋች** ቅ አስቸጋሪ÷አዋኪ::

**ዳጉሳ** ስ ፍሬው ጥቁር÷ቀይ ወይም ነጭ የሆነና ጎመን ዘር የሚያክል የእህል አይነት::

**ዳግመኛ** "ደገመ[1]" ስር ተመ.

**ዳግሚያ** "ደገመ[1]" ስር "ዳግም" ን ተመ.

**ዳግማዊ** "ደገመ[1]" ስር ተመ.

**ዳግም** ዝ.ከ.

**ዳግሞሽ** "ደገመ[1]" ስር "ዳግመኛ" ን ተመ.

**ዳጎሰ** ግ ወፈረ::

**ዳጎስ ያለ** ቅ ወፈር ያለ::

**ዳጠ** ግ 1. ደፈጠጠ÷ጨፈለቀ:: 2. ዳለጠ÷ ድጥ ሆነ÷ እግር አስከዳ÷ አንሻተተ::

**ዳጥ** ስ ሲረግጡት የሚያሟልጭ ጭቃማ (ቦታ)::

**ድጥ** ዝ.ከ.

**ድጣም** ቅ ዳጥ የሆነ (ቦታ)::

**አዳጠ** ግ አዳለጠ÷አንሸራተተ::

**ዳፈ** ግ ገፋ÷ አዳፋ÷ገፈተረ::

**ዳፈለ** ግ ጎፍላ አይነት ፀጉር አወጣ÷ፀጉራም ሆነ::

***ዳፈነ**

**ዳፌን** ስ 1. አንድን ግዴታ በተወሰነ ጊዜ ውስጥ ያለመፈፀም ሁኔታ (ግብርን በወቅቱ አለመክፈል÷ቅዳሴን ማስታጎል÷...):: 2. አንድን ግዴታ በተወሰነ ጊዜ ባለመፈፀም ምክንያት የሚከፈል መቀጮ::

**ተዳፈነ** ግ 1. ታጎለ÷ መፈፀም የነበረበት ነገር ሳይፈፀም ቀረ:: 2. አመድ ለበሰ÷ ተቀበረ(እሳት)::

**አዳፈነ** ግ አስታጎለ÷መፈፀም የሚገባውን ነገር ሳይፈፅም ቀረ::

**ዳፋ** ስ ጦስ÷መዘዝ::

**ዳፍንት** ስ አነስተኛ ብርሃን ባለበት ወይም በጨለማ ውስጥ በደንብ ለማየት የማያስችል (የሚከለክል) የአይን በሽታ::

**ዳፍንታም** ቅ 1. ዳፍንት የያዘው ሰው:: 2. (ዘይ.) ሀ. ንቃት÷ ቅልጥፍና የሌለው:: ለ. ደደብ÷ ትምህርት የማይገባው::

**ዴ** የ "ደ" ፊደል ሃምስ ዘር::

**ዴሲማል** ስ ከነጥብ በኋላ የሚፃፍ በአንድና በዜሮ መካከል ያለ ማንኛውም ቁጥር፤ አስርዮሽ ወይም በአስርዮሽ÷ በመቶኛ÷... የሚገለፅ ክፍልፋይ ቁጥር÷(ለምሳሌ 0.27 ዴሲማል ቁጥር ሲሆን ሃያ ሰባት መቶኛ የሚለውን አሃዝ ያሳያል ወይም ይወክላል)::

**ዴሲ ሜትር** ስ የርዝመት መለኪያ፤ 10 ዴሲ ሜትር 1 ሜትር ይሆናል::

**ዴፈረንሽያል (ዲፈሬንሻል)** ስ ሁለቱን የመኪና የኋላ እግሮች ፍጥነት ለማስተካከያነት የሚረዳ የመኪና አካል::

**ድ** የ"ደ" ፊደል ሳድስ ዘር::

**ድሁር** ቅ በጣም አጭር (ሰው)::

**ዴሂት** ስ 1. አጭርና ቀጭን የሆነች የዋልታ ዙሪያ ማገር:: 2. የቂጥኝ አይነት::

**ድሃ** "ደሃ" ን ተመ.

**ድህንፃ** ስ የበገና÷ የክራር ጅማት መግረፊያ:: (የበገናን ስእል ተመ.)::

**ድለላ**[1] "ደለለ " ስር ተመ.
**ድለላ**[2] "ደለ[2]" ስር ተመ.
**ድለቃ** "ደለቀ[1]" ስር ተመ.
**ድላል** "ደለለ[2] " ስር ተመ.
**ድል** ስ ተፎካካሪን፥ ተቀራኒን፥ ጠላትን፥.. በማሸነፍ፥ በመርታት የሚገኝ ውጤት።
**ድል ሆነ/ተነሳ** ተሸነፈ።
**ድል መታ/ነሳ/ አደረገ/ ተቀዳጀ/** አሸነፈ፥ የበላይነት አገኘ፥ ረታ፥ ።
**ድልህ** "ደለሀ" ስር ተመ.
**ድልምጥ** "ደለመጠ" ስር ተመ.
**ድልቂያ** "ደለቀ[1]" ስር ተመ.
**ድልብ** "ደለበ" ስር ተመ.
**ድልዝ**[1] " ደለዘ[1] " ስር ተመ.
**ድልዝ**[2] "ደለዘ[2] " ስር ተመ.
**ድለዳል** "ደለደለ" ስር ተመ.
**ድልድል** ዝ.ከ.
**ድልድል** ዝ.ከ.
**ድልድይ** ስ በወንዝ ወይም የወንዝ ቅርፅ ባለው መሬት ላይ ከእንጨት፥ ከድንጋይ፥ ከብረት፥... የሚሰራ መሸጋገሪያ።
**ድሎት** "ደላ" ስር ተመ.
**ድመት** ስ ብዙውን ጊዜ አይጥ እንዲያድን ተብሎ በቤት ውስጥ እንዲኖር የሚደረግ፥ፀጉሩ ልስልስ የሆነ ትንሽ የቤት እንስሳ(ስእሉን የቤት እንስሳ ስር ተመ.)።
**ድማሚት** "ደማሚት" ን ተመ.
**ድም**
**ድም አለ** ግ እንደ ከበሮ ወይም እንደ መድፍ ጩሀት ያለ ድምፅ አሰማ፥ ግም አለ።
**ድምር** "ደመረ" ስር ተመ.
**ድምበር** "ደነበረ[3]" ስር "ድንበር"ን ተመ.
**ድምበርተኛ**"*ደነበረ[3]" ስር "ድንበርተኛ" ን ተመ.
**ድምቡሎ(ድንቡሎ)** ስ 1. ባለ አምስት ሳንቲም መሃለቅ። 2. (ዘይ) ድንቡጭ ያለችና ደመግቡ የሆነች ልጅ እግር ሴት።
**ድምቡሽ(ድንቡሼ)** ቅ የፋፋ፥ ያማረበት (ህፃን ልጅ)።
**ድምቡጮ** ዝ.ከ.
**ድምቢጥ** "ድንቢጥ" ን ተመ.
**ድምብላል** ስ መጠኑ እንደ ዘንጋዳ የሆነ ዱቡልቡል የቅመም አይነት።
**ድምብል** "ድንብል" ን ተመ.
**ድምድማት** "ደመደመ" ስር ተመ.
**ድምጥማጥ**
**ድምጥማጡ ጠፋ** 1. ደብዛው ጠፋ፤ ያለበት፥ አድራሻው ታጣ። 2. ተደመሰሰ።
**ድምፅ(ድምጥ)** ስ 1. በመናገር፥ በማዜም፥ በእንቅስቃሴ አማካይነት ወይም አንድ አካል ከሌላው ጋር ሲላተም የሚፈጠርና ጆሮ ሊሰማው የሚችል ማንኛውም ስርአት የተከተለ ጩሀት ። 2. አንድን ጉዳይ፥ሃሳብ፥... በመደገፍ.. ወይም በመቃወም ወይም ሌላ አቋም በመያዝ የራስን ውሳኔ፥ምርጫ በይፋ (እጅ በማውጣት) ወይም በምስጢር (ካርድ በመጣል) · የማሳወቅ፥ የማስመዝገብ ሁኔታ።
**ድምፁ አይሰማም** ዝምተኛ፥ጭምት ነው።
**ድምፁ ያምራል** ጥሩ ድምፅ አለው።
**ድምፁ ጠፋ** 1. ዝም አለ። 2. አድራሻው ታጣ።
**ድምፁን ሰለበው** ድምፁን ዘጋው።
**ድምፅ ሰጠ** 1. በምርጫ ወይም በውሳኔ ጊዜ ድጋፉን ወይም ተቃውሞውን እጅ በማውጣት ወይም በሌላ ዘዴ አሳወቀ። 2. ድምፁ እንዲጨምር፥ እንዲጎላ አደረገ (የሬዲዮ፥የቴሌቪዥን)። 3. ድምፅ አሰማ።
**ድምፅ ሰጪ** ስ መራጭ (ድምፅ በመስጠት)።
**ድምፀ መረዋ** ቅ ጥሩ ድምፅ ያለው ሰው።
**ድምፀ ተአቅቦ** ስ በስብሰባ ላይ ለሚተላለፍ ውሳኔ የድጋፍ ወይም የተቃውሞ ድምፅ አለመስጠት።
**ድምፅ መቅጃ** ስ ማንኛውንም ድምፅ (ጩሀት፥ንግግር፥ዜማ፥...) እየተቀበለ በከር ጥብጣብ ወይም በሸክላ ላይ እንዳለ መዝግቦ ወይም ቀርፆ የሚያስቀር መሳሪያ።
**ድምፅ ማጉያ** ስ የአንድን ነገር ድምፅ እየተቀበለ መልሶ እንደአስፈላጊነቱ የድምፁን ሃይል ጨምሮና አጉልቶ የሚያሰማ መሳሪያ።
**ድምፅ የሌለው መሳሪያ** ስ እንደ ጩቤ፥ ጎራዴ፥ ሰንጢ፥... ያለ የጦር መሳሪያ።
**ድምፃዊ** ቅ 1. ሲያዜም ወይም ሲዘፍን ድምፁ የሚያምር፥ ደስ የሚል። 2. ዘፋኝ።
__ድረስ "ደረሰ[1]" ስር ተመ.
**ድሪ** ስ ከብር ወይም ከወርቅ የሚሰራ የአንገት ጌጥ።
**ድሪ** "*ደራ[1] ስር "ድሪያ" ን ተመ.
**ድሪቶ** "ደረተ" ስር ተመ.
**ድሪቷም** ዝ.ከ.
**ድሪያ** "*ደራ[2] " ስር ተመ.

**ድራማ** ስ በቴአትር ቤት፥በሬዲዮ፥ በቴሌቪዥን የሚቀርብ ወይም የቀረበ ተውኔት።

**ድራማ** ስ ያልተወቃ የዘንጋዳ ወይም የማሽላ ራስ ክምር።

**ድራር**[1] ስ አስከሬን ወይም የሬሳ ሳጥን መቃብር ውስጥ ከገባ በሂላ አፈር እንዳይጫነው ከለላ የሚሆን የእንጨት ወይም የድንጋይ ርብራብ።

**ድራር አቃፊ** ስ በመቃብር ውስጥ በሬሳ ሳጥን ዙሪያ የሚደረደርና ርብራቡን (ድራሩን) የሚሸከም ድንጋይ።

**ድራር**[2] ስ የትልቅ በአል ዋዜማ።

**ድራሽ** " **ደረሰ**[1] " ስር ተመ.

**ድራብ** "**ደረበ**" ስር "**መደረቢያ**" ን ተመ.

**ድራት** " **ደራ**[1] " ስር ተመ.

**ድራፍት**[ቢራ ] ስ በፋብሪካ ተጠምቆ እንደ ወጣ፥ ብዙ ሳይቆይ በትኩሱ ለተጠቃሚ የሚቀርብ ቢራ ።

**ድር** "'**ደራ**[2] " ስር ተመ.

**ድርሰት** "**ደረሰ**[2] " ስር ተመ.

**ድርሳን** ዝ.ከ.

**ድርስ** "**ደረሰ**[1] " ስር ተመ.

**ድርሻ** ዝ.ከ.

**ድርቀት** "**ደረቀ**" ስር ተመ

**ድርቄ** ስ ሰገባ።

**ድርቅ** "**ደረቀ**" ስር ተመ.

**ድርቅና** ዝ.ከ.

**ድርቆሽ** ዝ.ከ.

**ድርበብ** "'**ደረበበ**" ስር ተመ.

**ድርብ** "**ደረበ**" ስር ተመ.

**ድርብብ** "'**ደረበበ**" ስር ተመ.

**ድርት** "**ደረተ**" ስር ተመ.

**ድርያ** "**ደራ**[1] " ስር "**ድሪያ**" ን ተመ.

**ድርድር** "**ደረደረ**" ስር ተመ.

**ድርድር** ዝ.ከ.

**ድርጅት** "**ደረጀ**" ስር ተመ.

**ድርገት ወረዱ** ስ (ኢ.ኦ.ተ.ቤ.) በቅዳሴ ስነ ስርአት ማብቂያ ላይ ምእመናኑን ለማቁረብ መስዋእቱን ይዘው ቀዳስያኑ በአንድነት ከመቅደስ ብቅ አሉ።

**ድርጊት** "***ደረገ**" ስር ተመ.

**ድርጎ** "**ዳረገ**" ስር ተመ.

**ድርጎኛ** ዝ.ከ.

**ድርጭት** ስ አሸዋማ መልክ ያለውና ከርግብ አነስ የሚል የወፍ አይነት።

**ድርፋጭ** "**ደረፈጠ**" ስር ተመ.

**ድሮ** "**ዱሮ**" ን ተመ.

**ድስት** ስ ወጥ ለመስሪያ ወይም ለመቀቀያ እንዲያገለግል ከሸክላ ወይም ብረት ነክ ከሆኑ ነገሮች የሚሰራ፥የተለያየ መጠን ያለው እቃ።

**ድቀት** ስ 1. ክስረት። 2. ውርደት።

**ድቁስ** "**ደቆሰ**" ስር ተመ.

**ድቁና** " **ዲቆን**" ስር ተመ.

**ድቃቂ** "**ደቀቀ**" ስር ተመ.

**ድቅን** "**ደቀነ**" ስር ተመ.

**ድቅድቅ** "**ደቀደቀ**[1] " ስር ተመ.

**ድቋ** ስ በጉሽ ጠላ መልክ የሚዘጋጅ የጠላ አይነት።

**ድቡልቡል** "**ድብልብል**" ን ተመ.

**ድቡሽት** ስ ሲረግጡት ትምክ ትምክ የሚል አሸዋማ መሬት።

**ድባ** ስ ድቡልቡል ቅጽፅ ያለው የዶቃ አይነት።

**ድባቅ**

**ድባቅ መታ** አጠፋ፥ አወደመ፣ አሸነፈ፥ ደመሰሰ።

**ድባብ** ስ ከሃር ጨርቅ የሚሰራና የብር ወይም የወርቅ መርገፍ ያለበት፥ በበአል ቀን በቤተክርስቲያን ለታቦት የሚዘረጋ ትልቅ ጥላ።

**ድባኖ** "**ደበነ**" ስር ተመ.

**ድቤ** ስ ለመቃብር ተብሎ የተቆፈረ አፈር።

**በድቤ ተቀበረ** ያለ ሳጥን ወይም ያለ ድራር ተቀበረ(አስከሬኑ አፈር ብቻ ለበሰ)።

**ድቤ** ስ ትንሽ ነጋሪት፣ የቃልቻ ከበሮ።

**ድብ**[1] ስ ረጅም ፀጉርና ጥፍር ያለው፥ ጠንካራና ሃይለኛ የሆነ አውሬ።

**ድብ**[2]

**ድብ አለ** ግ ወደቀ፥ ዱብ አለ።

**ድብ አደረገ** ግ አፈረጠ፥ ጣለ።

**ድብል**[1] "**ደበለ**" ስር ተመ.

**ድብል**[2] "**ደበለለ**[2] " ስር ተመ.

**ድብልቅ** "**ደባለቀ**" ስር ተመ.

**ድብልቅልቅ** ዝ.ከ

**ድብልብል** "'**ደበለበለ**" ስር ተመ.

**ድብርቅ** ስ መድሃኒትነት አለው የሚባል፥ ፍሬው ተወቅጦና ከአጥሚት ጋር ተፈልቶ የሚጠጣ፥ በወይና ደጋ የሚበቅል የእፀዋት አይነት።

**ድብርት** "ደበረ[3]"

**ድብስብስ** "ደበሰ" ስር ተመ.

**ድብቅ** "ደበቀ" ስር ተመ.

**ድብብቆሽ** ዝ.ከ

**ድቡት** ስ ትንሽ የእህል ክምር::

**ድብትርና** "ደበተረ" ስር ተመ.

**ድብኝት** ስ 1. ከጭቃ የተሰራ የእህል ማስቀመጫ፥ ጎታ ጉስጉሻ:: 2. (ዘይ.) አጭርና ወፍራም የሆነ (ሰው)::



ድብኝት 1ኛ ፍቺ

**ድብክብክ** "'ደበከበከ" ስር ተመ.

**ድብደባ** "ደበደበ[1]" ስር ተመ.

**ድብዳብ** ስ ለመቀመጫነት የሚያገለግል ከነፀጉሩ የተለፋ የበግ ቆዳ::

**ድብደባ** ስ የአፈር፥ የጉድፍ ክምር፤ ኩይስ::

**ድብድብ** "ደበደበ[4]" ስር ተመ.

**ድብድብ** "ደበደበ[2]" ስር ተመ.

**ድንስር** "'ደነሰረ" ስር "ደንሳራ"ን ተመ.

**ድንቁርና** "ደነቀረ"ስር ተመ.

**ድንቅ** "ደነቀ" ስር ተመ.

**ድንቅፍቅፍ** "*ደነቀፈ" ስር "ደንቀፍቃፋ"ን ተመ.

**ድንበር** "ደነበረ[3]" ስር ተመ.

**ድንበርተኛ** ዝ.ከ

**ድንቡሉ** "ድምቡሎ" ን ተመ.

**ድንቡሽ** "ድምቡሼ"ን ተመ.

**ድንቢጥ (ድምቢጥ)** ስ መጠኗ አነስተኛ የሆነ የወፍ አይነት::

**ድንብል (ድምብል)** ስ ሴቶች በክር ሰክተው አንገታቸው ላይ የሚያደርጉት ቀለበት::

**ድንብርብር** "ደነበረ[2]" ስር ተመ.

**ድንት አለም** ዝንት አለም ::

**ድንች** ስ የፍሬው ቅርፅ ክብ ወይም ሞላላ ሆኖ በመሬት ውስጥ እንደ ሽንኩርት የሚያፈራና የሚፋፋ፥ ተቀቅሎ፥ ተጠብሶ፥... የሚበላ ተክል::

**ድንን** ስ 1. ችፍግ ብሎ የሚገኝ ደን:: 2. (ዘይ.)ችፍግ ያለ ፀጉር::

**ድንኩል**

**ድንኩል ድንኩል አለ** ግ ድክ ድክ አለ (የህፃን ልጅ አካሄድ)::

**ድንክ** ቅ ከመሰሎቹ በተለየ በጣም አጭር የሆነ ትክለ ሰውነት ያለው::

**ድንክ አልጋ** ስ አጠር፥ ጠበብ ብሎ ለመቀመጫም እንዲያገለግል ሆኖ ከእንጨትና ከጠፍር የሚሰራ አልጋ::

**ድንኳን** ስ ከሸራ ወይም ከአቡጀዲ፥... የሚሰራ፥ እንደ ቤት ሆኖ በጊዜያዊነት የሚያገለግል መጠለያ::




ድንኳን

**ድንኳን ጣለ (ተከለ)** ድንኳን ዘረጋ::

**ድንገት** ተው.ግ 1. ሳይታሰብ:: *ስመጣ ድንገት ሞተ::* 2. ምናልባት::*ድንገት መኪና ካለገኘሁ ነገ እሄዳለሁ::*

**ድንገተኛ** ቅ 1. ያልታሰበ:: ስ 2. ድንገት የሚያጋጥም የህመም አይነት:: 3. ድንገተኛ ለተባለው በሽታ ማስታገሻ ይሆናል የሚባል መድሃኒት(ብዙውን ጊዜ ስራስር)::

**ድንገተኛ ክፍል** ስ ድንገት የታመሙ ወይም አደጋ ያጋጠማቸው ሰዎች የሚታከሙበት ክፍል (ሃኪም ቤት)

**ድንጉላ[ፈረስ]** ስ ያልተኮላሸ ፈረስ::

**ድንጉል** ስ 1. ከአንድ የንብ መንጋ መካከል ስራው ውሃ ማጋዝ የሆነና የማይናደፍ ንብ :: 2. ድንጉል ከሚባለው የንብ ድምፅ ጋር የሚመሳሰል ወፍራም ድምፅ የሚወጣው የበገና ኽምማት::

**ድንጉርጉር** "ደነጎረ[2]" ስር ተመ.

**ድንጉጥ** "ደነገጠ" ስር ተመ.

**ድንጋሌ** "ድንግል" ስር ተመ.

**ድንጋይ(ደንጊያ)** ስ 1. ብረትነት የሌለው ጠጣር የማእድን አይነት:: 2. (ዘይ.)ደደብ፤ ነገር የማይዘልቀው፥ ጠንካራ፥ቻይ:: 3. "ባትሪ" ስር " ባትሪ ድንጋይ" ን ተመ.

**ድንጋይ ነው** ደደብ፥ የማይገባው ነው::

**የድንጋይ ልብስ** ስ በድንጋይ ላይ ተለጥፎና ጭፍቅ ብሎ የሚበቅል አረንጓዴ የእፅዋት አይነት::

**የድንጋይ ከሰል** ስ እየነደደ ሙቀት

የሚሰጥና ጋዝ የሚገኝበት ጥቁርና ጠጣር ማእድን::

**ድንጋይ ልብ (ልበ ድንጋይ)** 1. ጨካኝ:: 2. የማይገባው:: *ድንጋይ ልብ ስለሆነ ቢነግሩት ላይገባውም::*

**ድንጋይ ራስ** ደደብ::

**ድንጋይ በእግሩ** ሰነፍ፥ ቅልጥፍና የሌለው ጎታታ::

**ድንጋያማ** ቅ ድንጋይ የበዛበት ቦታ ወይም መሬት::

**ድንጋጌ** "**ደነገገ**" ስር ተመ.

**ድንጋጤ** "**ደነገጠ**" ስር ተመ.

**ድንግል** (**ብ.ቁ.ደናግል**) ስ 1. ድንግልና:: 2. የግብረ ስጋ ግንኙነት ፈፅሞ ያላደረገ:: ቅ 3. ታርሶ፥ ተቆፍሮ የማያውቅ (መሬት)::

**ድንጋሌ** ስ ንፅህና፥ ህይወትን በሙሉ የግብረ ስጋ ግንኙነት ፈፅሞ ሳያደርጉ የመኖር ሁኔታ::

**ድንግላዊ (ድንግላይ)** ቅ ህይወቱን በሙሉ ከግብረ ስጋ ግንኙነት ርቆ የሚኖር::

**ድንግልና** ስ 1. ክብረ ንፅህና፥ ህግ:: 2. ከግብረ ስጋ ግንኙነት ርቆና ተጠብቆ የመኖር ሁኔታ::

**ድንፋታ** "**ደነፋ**" ስር ተመ.

**ድኝ** ስ ቀለሙ ቢጫ የሆነ የማእድን አይነት::

**ድከን** "**ደከነ**" ስር ተመ.

**ድኩላ** ስ አንገቱ ነጭ፥ በጀርባው ላይ አልፎ አልፎ ነጣ ያሉ ምልክቶችና ጥቁር ሽንትር ያለው፥ ሌላ አካሉ ወርቅማ የሆነ፥ ከአጋዘንና ከኒያላ ወገን የሚመደብ፥ቀንዶቹ እስከ 50 ሳንቲ ሜትር የሚረዝሙ፥ ቅጠላቅጠል፥ ሳር፥... የሚመገብ የዱር እንስሳ (ስእሉን "የዱር እንስሳ" ስር ተመ.)::

**ድኩም** "**ደከመ**" ስር ተመ.

**ድካ** "**ደካ[1]**" ስር ተመ.

**ድካም** "**ደከመ**" ስር ተመ.

**ድክመት** ዝ.ከ.

**ድክን** "**ደከነ** " ስር "**ድከን** " ን ተመ.

**ድኮት** ስ ከብር ወይም ከነሃስ የሚሰራ እንደ አንባር ያለ የእግር ጌጥ::

**ድኳ** "**ደኳኳ** "ን ተመ.

**ድው[1]**

**ድው አለ** ግ ፀጥ፥እረጭ አለ::

**ድው አለው** ፍዝዝ፥ቅዝዝ አደረገው::

**ድው[2]**

**ድው አለ** ግ ግው የሚል ድምፅ አሰማ::

**ድውር** "**ደወረ**" ስር ተመ.

**ድውይ** "**ደዌ**" ስር ተመ.

**ድድ** ስ በጥርሶች መብቀያ፥ ጥርሶችን አጥብቆ የሚይዝ ስጋ::

**ድዱን አሰጣ** ገለፈጠ፥ በሆነ ባልሆነ ነገር ሳቀ::

**ድዳም** ቅ (ስድብ) 1. ከተለመደው መጠን በላይ ድዱ ከጥርሶቹ ጎልቶ የሚታይ ሰው:: 2. በሆነ ባልሆነ ነገር የሚስቅ፥የሚገለፍጥ::

**ድድር** "**ደደረ**" ስር ተመ.

**ድድቅ** "**ደደቀ**" ስር ተመ.

**ድጅኖ** ስ ሁለቱም ጫፎቹ ድንጋይ ለመፈንቀል፥ መሬት ለመማስ እንዲያገለግል ሆኖ ሙሉ በሙሉ ከብረት የተሰራ መሳሪያ::



ድጅኖ

**ድጉልጉል** "***ደጎለጎለ**" ስር ተመ.

**ድጉስ** "**ደጎሰ**" ስር ተመ.

**ድጋሚ** "**ደገመ[1]**" ስር ተመ.

**ድጋም** "**ደገመ[2]**" ስር ተመ.

**ድጋፍ** "**ደገፈ**" ስር ተመ.

**ድግ** "***ደገደገ**" ስር ተመ.

**ድግምተኛ** "**ደገመ[2]**" ስር ተመ.

**ድግምታም** ዝ.ከ.

**ድግምት** ዝ.ከ.

**ድግር** ስ ከሞፈር ቂጥ ጋር በቅትርት ከእርፍና ከማረሻ ጋር በወገል የሚያያዝና ማረሻ የሚሰነጠቀውን መሬት እያሰፋ የሚሄድ የእርሻ መሳሪያ(ስእሉን ሞፈር ስር ተመ.)::

**ድግስ** "**ደገሰ**" ስር ተመ.

**ድግዝግዝታ** "***ደገዘ**" ስር ተመ.

**ድግድግ** ዝ.ከ.

**ድግግም** "**ደገመ[1]**" ስር ተመ.

**ድግግሞሽ** ዝ.ከ.

**ድግጣ** ስ የግንዱ ውፍረት እንደ ጨፈቃ ሆኖ መለል መለል ያለ፥ በወይና ደጋ የሚበቅል የእፅዋት አይነት::

**ድኋማ** "**ደኀመ**" ስር ተመ.

**ድኅ[1]** ስ ያሬድ ከደረሳቸው መካከል ትልቁ የዜማ መፅሃፍ::

**ድኅ[2]** ስ ደቃቅ ገለባ እብቅ::

**ድጣም** "ዻጠ" ስር ተመ.

**ድጥ** ዝ.ክ.

**ድጦሽ** ስ ተቀቅሎ የተደፈጠጠ ምስር፥ የአተር ክክ::

**ድፊት** ስ ወፍ፥ ቆቅ፥... ለመያዝ የሚያገለግል እንደ ወንፊት ያለ፥ ቅርጫት መሰል ወጥመድ::

**ድፋርሳ** ስ መልኩ ግራጫማ ቡና ቀለም የሆነ፥ በአንገቱ ዙሪያ፥ ከቂጡ አካባቢና ከየኮቴዎቹ በላይ እንደ ቀለበት የዞሩ ነጫጭ ሽንትሮች ያሉት፥ ቆዳው መጥፎ ጠረን የሚያመነጭ፥ እንደ ደጋን ጎበጥ ያሉ ቀንዶች ያሉት ሳረበል የዱር እንስሳ::

**ድፋት** "ደፋ" ስር ተመ.

**ድፈት** ዝ.ክ.

**ድፍረት** "ደፈረ" ስር ተመ.

**ድፍርስ** "ደፈረሰ" ስር ተመ.

**ድፍን** "ደፈነ" ስር ተመ.

**ድፍንፍን** ዝ.ክ.

**ድፍድፍ** "ደፈደፈ" ስር ተመ.

**ድፍጥ** "ደፈጠጠ" ስር "ደፍጣጣ" ን ተመ.

**ድፍጥጥ** ዝ.ክ.

**ድፎ** "ደፋ" ስር ተመ.

**ዶ** የ "ደ" ፊደል ሳብእ ዘር::

**ዶለ** ግ ከተተ፥ ጨመረ፥ አገባ::

**ዶለተ** ግ 1. አሴረ፥ አደመ:: 2. ተሰበሰበ (ለምክክር)::

**ዱለታ(ዱለት)** ስ ሴራ፥ አድማ::

**ዱለተኛ** ቅ አድመኛ፥ ሴረኛ::

**ዶለዝ** ቅ 1. ስለት የሌለው፥ ዱልዱም:: 2. ወፍራምና ፍርጥም ያለ ሰውነት ያለው (ሰው):: 3. (ዘይ.) ደደብ፥ ደነዝ፥ እውቀት የማይገባው::

***ዶለዶለ**

**ዶልዷሌ** ቅ ቸር፥ ለጋስ::

**ተንዶለዶለ** ግ በብዛት ወረደ፥ ፈሰሰ (ፈሳሽ)::

**አንዶለዶለ** ግ በብዛት አወረደ፥ አፈሰሰ::

**ዶለዶመ** ግ ደነዘ፥ ስለት የለሽ ሆነ::

**ዱልዱም** ቅ 1. ስለት የሌለው፥ ደነዝ:: ስ 2. አጠር ብሎ ችምችም ያለ የዶሮ ኮከኔ::

**ዶልዱማ** ቅ ስለት የሌለው፥ ደነዝ::


**አዶለዶመ** ግ ስለትን አደነዘ፥ ዱልዱም እንዲሆን አደረገ::

**ዶላር** ስ በአሜሪካ፥ በካናዳ፥ በአውስትራሊያ፥... የሚያገለግል የገንዘብ ስም::

**ዶልዷሌ** "*ዶለዶለ" ስር ተመ.

**ዶልዷማ** "ዶለዶመ" ስር ተመ.

**ዶማ** ስ እጀታ ያለው መቆፈሪያ::



ዶማ

**ዶመኛ** ስ 1. በሬ ስለሌለው የእርሻ መሬቱን እየቆፈረ በማምረት የሚተዳደር ሰው:: 2. በዶማ የሚቆፍር::

***ዶረረ**

**ዱርር** ቅ ጅንን፥ ኩሩ::

**ተዶረረ** ግ 1. ኩራ፥ ተጀነነ:: 2. ተቀጣ፥ አኩረፈ::

**ተዶራሪ** ቅ ኩሩ፥ ጅንን::

**አዶረረ** ግ አኩረፈ፥ ተቆጣ::

**ዶሮ** ስ 1.የሚረባ፥ ስጋው ለምግብነት የሚያገለግል፥ የአሞራ ወገን የሆነ የቤት እንስሳ(ስእሉን የ"ቤት እንስሳ" ስር ተመ.):: 2. (ዘይ.) ደቃቃ የሆነ፥ አቅም የሌለው (ሰው)::

**የዶሮ ብልት** ስ ዶሮ ከተገነጣጠለ በኋላ የሚወጣው እንደ መላላጫ፥ ፈረሰኛ፥...ያለው የዶሮ አካል::

**ዶሮ ጮሀ** እኩለ ሌሊት ሆነ::

**ዶሮ ማታ** 1. አንድ ሰው አንድን ከበድ ያለ ነገር ፈጥኖ እንዲፈፅም(ለምሳሌ መራራውን ኮሶ ጅው አድርጎ እንዲጠጣ) የሚነገር የማደፋፈሪያ ቃል:: 2. ባዶ ተስፋ::

**ዶሮ በጋን** 1. በጣም ትንሽ ለሆነ ነገር በጣም የተለቀ መከተቻ፥ መያዣ ማድረግ:: 2. እጅግ አለመጠን ያነሰ::

**የዶሮ ማር** ስ ከገረንገሬና ከአምጃ እንጨት ላይ የሚገኝ ማር የሚመስል ሙጫ::

**የዶሮ ብልት** ስ እንደ ፈረሰኛ፥ መላላጫ፥... ያለ የዶሮ ስጋ::




የዶሮ ብልት

**[የ] ዶሮ ወጥ** ስ ከዶሮ ብልት ብቻ የተዘጋጀ ወጥ።

**ዶሮ ዳቦ** ስ ሊጡ በዶሮ ወጥ ተለውሶ ከእንቁላሉና አጥንቱ ጋር አብሮ የተጋገረ የአበሻ ዳቦ።

**ዶሰኛ** ቅ ሃይለኛ፥ ጉልበተኛ።

**ዶሴ** ስ ማህደር፥ ፋይል።

**ዶሴ ከፈተ** ፋይል ከፈተ፥ ሙግት ጀመረ።

***ዶሸዶሸ**

**ዶሸዶሸ አለ** ግ ተንዶሸዶሸ፥ ተንጦሸጦሸ።

**ዶሸዶሸ አደረገ** አንዶደሸዶሸ፥ አንጦሸጦሸ።

**ተንዶሸዶሸ** ግ 1. በውሃ የራስ ጥሬ (ሽንብራ፥ ባቄላ፥..) ሲቆላ የሚሰጠውን አይነት ድምፅ ሰጠ። 2. ተቆላ (የራስ ባቄላ፥ አተር፥...)።

**አንዶሸዶሸ** ግ 1. በውሃ የራስ ጥሬ ሲቆላ የሚሰጠውን አይነት ድምፅ እንዲሰጥ አደረገ። 2. ቆላ (የራስ ባቄላን፥ አተርን፥...)።

**እንዱሸዱሸ** ስ በውሃ በጣም ከራሰ በኋላ የተቆላ ጥሬ (ባቄላ፥ አተር፥...)።

**ዶቃ** ስ ብዙውን ጊዜ ጥቁር ሰማያዊ ቀለም ያለውና ቅርፁ እንደ ወፍራም ቀለበት የሆነ፥ መጠኑ ከቀለበት ያነሰ፥ በክር ተሰክቶ አንገት ላይ በጌጥነት የሚንጠለጠል ከጠርሙስ የሚሰራ የልጆች ጌጥ።

**ዶቅማ** ስ ጥቁር ፍሬ የሚያፈራና ፍሬውም የሚበላ ጠንካራ የሆነ የዛፍ አይነት፤ ፍሬውም ዶቅማ ይባላል።

***ዶበረ**

**አዶበረ** ግ ተከፋ፥ ተቀየመ፥ አኩረፈ።

**አስዶበረ** ግ አስከፋ፥ አስቀየመ፥ አስኩረፈ።

**ዶቢ** ስ የሳማ አይነት።

**ዶኩሜንት** ስ በምስክርነት ወይም በማስረጃነት ሊያገለግል የሚችል ማንኛውም የፅሁፍ መረጃ፥ ሰነድ።

**ዶኩሜንታሪ ፊልም** ስ የሰዎችን የአኗኗር ዘዴ፥ የእለት ተእለት የስራ እንቅስቃሴና ውጤት፤ የእንስሳትን አኗኗር፥ ጠባይ፥...፤ የተፈጥሮ አካባቢን ሁኔታ የሚያሳይ ጥናታዊ ወይም ዘጋቢ ፊልም።

**ዶኬ** "*ዶከደከ" ስር ተመ.

**ዶክተር** ስ 1. የህክምና ሳይንስ ምሩቅና በህክምና ስራ ላይ የተሰማራ ባለሙያ። 2. በማንኛውም የእውቀት ዘርፍ በዩኒቨርስቲ የሚሰጠውን ከፍተኛውንና የመጨረሻ ደረጃ የሆነውን ሶስተኛ ዲግሪ የተቀበለ ሰው።

**ዶዮ** ስ (የን.አነ.) ቅመም፥ ቅባት፥... የሌለበት መናኛ ወጥ።

**ዶግ** ስ ጥንካሬ የሌለው፥ ቅጠሉ እንስሳል የሚመስል የእፅዋት አይነት።

**[የ] ዶግ አመድ አደረገ** አወደመ፥ አጠፋ።

**ዶሻማ** ቅ በጥቁርና በቀይ መካከል ያለ የከብት መልክ።

**ዶጮ** ስ 1. መጠኑ አነስተኛ የሆነ የገንቦ አይነት። 2. (ዘይ.) አጭርና ወፍራም የሆነ (ብዙውን ጊዜ ለልጅ)።

**ዶፈ** ግ ከነፋስ ጋር የተቀላቀለ ሃይለኛ ዝናብ ያለማቋረጥ ጣለ፥ ዘነበ።

**ዶፍ** ስ ነፋስ ቅልቅል የሆነና ለረጅም ሰአት ያለማቋረጥ የሚዘንብ ሃይለኛ ዝናብ።

**ዶፈዶፈ** ግ ገዘፈ፥ ወፈረ።

**ዶፈዶፍ (ዶፍዶፋ)** ቅ ወፍራም፥ ቅርፀቢስ፥ ከመወፈሩ የተነሳ ቅርፁ የማያምር፥ የተድበለበለ።

**ዶፍ** "ዶፈ" ስር ተመ.

**ዶፍዷፋ** "ዶፈዶፈ" ስር ተመ.

**ዷ**[1] የ "ደ" ፊደል ፍንፅቅ ዘር።

**ዷ**[2]

**ዷ አለ** ግ እንደ ጥይት ጮሀ ወይም እንደ በንብ ፈነዳ።

**ዷ አደረገ** ግ እንደ ጥይት ተኩስ ወይም እንደ በንብ ፍንዳታ ያለ ድምፅ አሰማ፥ አጮሀ።

**ተንዷዷ** ግ በተደጋጋሚ የተኩስ ወይም የፍንዳታ ድምፅ ሰጠ ወይም ተሰማ።

**አንዷዷ** ግ ተከታታይ የሆነ የፍንዳታ ወይም የተኩስ ድምፅ አሰማ።

# ጀ

**ጀ** ከ"ደ" ፊደል ዘር ቀጥሎ የሚመጣ የአማርኛ ፊደል (ግእዙ ሆሄ)::

**ጀለ** ግ ቄለ፥ ሞኘ ሆነ::

**ጅል** ቅ ቂል፥ ሞኝ::

**ጅላጅል** ቅ ቂላቂል፥ ሞኛሞኝ፥ ወደቂልነት የሚወስደው::

**ተጃጃለ** ግ 1 ቂል፥ ሞኝ ሆነ:: 2 ተሞኘ::

**አጀለ** ግ አቄለ፥ አሞኘ::

**አጃጃለ** ዝ.ከ.

**ጀለተ (ዠለተ)** ግ በዛ፥ ሰፋ፥ ተንሰራፋ (አትክልት፥ ፀጉር)::

***ጀለጀለ**

**ጀልጃላ** ቅ አለቅጥ የረዘመ፥ ዘልዛላ (ብዙውን ጊዜ ለልብስ)::

**ጅልጅል አለ** ግ ተንጀለጀለ፥ ተንዘረፈፈ::

**ተንጀለጀለ** ግ ያለቅጥ ረዘመ፥ተንዘረፈፈ::

**ተንጀላጀለ** ዝ.ከ.

**አንጀለጀለ** ግ ያለቅጥ አረዘመ ወይም አስረዘመ (ብዙውን ጊዜ ለልብስ)::

**አንጀላጀለ** ዝ.ከ.

**ጀለጠ "ዠለጠ"** ን ተመ.

**ጀላ** ስ (ነውር) የወንድ ብልት::

**ጀሌ** ስ 1. የጦር መሳሪያ ያልያዘ ዘማች:: ቅ 2. ተራ ህዝብ :: 3. መሪ ያልሆነ፥ ተከታይ፥ ወይም ተራ አባል (የእንቅስቃሴ፥ የድርጅት)::

**ጀልባ** ስ መጠኑ አነስተኛ የሆነ የውሃ ላይ መጓጓዣ:: (ስእሉን "መጓጓዣ" ስር ተመ.)

**ጀልጃላ "*ጀለጀለ"** ስር ተመ.

**ጀመለ** ግ በብትን፥ በዝርዝር የነበረውን በአንድነት አደረገ::

**ጅመላ** ስ ጥቅል፤ ያልተበተነ፥ በአንድነት የሆነ::

**በጅምላ** ተው.ግ 1. በጥቅል፤ በነጠላ ያልሆነ (የሸቀጣ ሸቀጥ ግገርና አሻሻጥ መንገድ):: 2. በአጠቃላይ:: *ሁሉም ሰራተኛ በጅምላ ሰነፍ ሊይባልም::*

**ጅምላ ነጋዴ(ሻጭ)** ስ ሸቀጦችን በችርቻሮ ሳይሆን በጥቅል የሚሸጥ ነጋዴ፤ አከፋፋይ::

**ጀመረ** ግ 1. አንድን ስራ፥ ተግባር ለመስራት አንድ ብሎ ከመነሻው ተነሳ:: 2. አንድን ስራ፥ ድርጊት ማካሄድ፥ መስራት ያዘ:: *ስራ የምንጀምረው በሁለት ሰአት ላይ ነው::* 3. አንድን ስራ ለማከናወን፥ ለመፈፀም ወጠነ:: 4. አንድ ድርጊት መካሄድ ያዘ፥ ወይም አንድ ሁኔታ ድንገት ተከሰተ:: *ሸንባ መወረድ ጀመረ/ዝናብ መዝነብ ጀመረ::* 5. አንድን ነገር ለመስራት፥ ለማውጣት ቀዳሚ ሆነ:: *የሁትመትን ስራ የጀመረችው ሃገር ትደነቃለች::* 6. (ነገርን፥ ጠብን፥..) ጫረ፥ ተነኮሰ ወይም ድርጊቱን ለመፈፀም የመጀመሪያው ወገን ሆነ:: 7. አንድ ነገር፥ መሳሪያ፥... ተግባሩን ማከናወን ያዘ፥ ወይም አንድ ሁኔታ መሆኑ፥ መካሄዱ ተከሰተ:: *ሆቴሉ ስራ ጀመረ::*

**መጀመሪያ** ስ 1. መነሻ:: ተው.ግ. በቅድሚያ፥ በፊት::

**ለመጀመሪያ ጊዜ** 1. ማንም ሳያደርገው በፊት፥ *ለመጀመሪያ ጊዜ ሳለምን የዞረ እሱ ነው::* 2. ለአንደኛ ጊዜ:: 3. ከዚህ ቀደም ሳይሞከር፥ ሳይደረግ:: *ቀለም የቀባሁት ለመጀመሪያ ጊዜ ነው::*

**የመጀመሪያ እርዳታ** ስ አደጋ የደረሰበት ሰው ሁነኛውን ህክምና እስኪያገኝ ድረስ ለጊዜው የሚደረግለት የመጀመሪያ ህክምና::

**ጀማሪ** ቅ 1. ቀዳሚ፥ መስራች፥ ቀርቋሪ:: 2. ተለማማጅና ለአንድ ስራ ገና አዲስ የሆነ::

**ጅማሬ** ስ 1. የአነሳስ፥ የአጀማመር ሁኔታ:: 2. የመጀመሪያ ደረጃ::

**ጅማሮ "ጅምር"** ን ተመ.

**ጅምር (ጅማሮ)** ቅ 1. ያላለቀ፥ ስራው የሚቀጥል፥ የተጀመረ:: 2. የአጀማመር ሁኔታ:: 3. አንድ ሰው የጀመረውና ያልጨረሰው ስራ:: *ጅምሬን ልጨርስ::*

**አስጀመረ** ግ 1. አንድ ሰው አንድን ስራ እንዲሰራ አያያዘ፥ አቆናጠጠ:: 2. አንድ ስራ፥ ጉዳይ፥... እንዲጀመር ወይም ለመጀመሪያ ጊዜ እንዲሰራ አደረገ::

**ተጀመረ** ግ 1. መካሄድ፥ መከናወን፥ መስራት ያዘ:: 2. ለመጀመሪያ ጊዜ ታየ፥ ተከሰተ:: *የትያትር ጥበብ በሃገራችን ከተጀመረ ሃምሳ አመታት አልፏል::* 3. ተሞከረ:: *አልተሳካም እንጂ ተጀምሮ ነበር::*

**ጀማ** ስ ለአንድ ለተወሰነ ጉዳይ የተሰበሰቡ ሰዎች፤ ጉባኤ::

**ጀምበር (ጀንበር፥ ዥምበር፥ ዠንበር)** ስ ፀሃይ:: *ጀምበር ስትጠልቅ ወደ ቤቱ ይገባል::*

**ጀምበር ስትጠልቅ** ወደ አመሻሽ ላይ፥ መሸት ሲል::

**ጀምብ** ስ ከሁለት የቀርቃባ ጭነት አንዱ::

**ጀሞ** ስ ከብረት የሚሰራና ቅርፁ ሳይጻ ወይም አካፋ የሚመስል እሳት መጫሪያ።
**ጀረጀፈ** ግ አረጀ፥ ገረጀፈ።
**ጀረገገ "ዠረገገ"** ን ተመ.
**ጀርባ (ዠርባ)** ስ 1. ከማጅራት እስከ መቀመጫ ያለ በሆድና በደረት ተቃራኒ አቅጣጫ የሚገኝ የሰውነት ክፍል( ሰውነት ስር ተመ.)። 2. የአንድ ነገር (ወረቀት፥ ሰሌዳ፥ ቤት...) የሃለኛ ገፅታ።
**ጀርባውን ሰጠ /አዞረ/** 1. ፊቱን አዞረ። 2. ችላ አለ።
**የጀርባ አጥንት** ዋነኛ የሆነ፥ በጣም አስፈላጊ ነገር። *ቡና ለአገሪቱ ኢኮኖሚ የጀርባ አጥንት ነው።*
**ጀበና** ስ ከቆርቆሮ ወይም ከነሃስ ወይም ከሸክላ የሚሰራና ለቡና ለሻይ፥... ማፍያነት የሚያገለግል እቃ።
**ጀበደ "ዠበደ"** ን ተመ.
**ጀባ** ግ እነሆ፤ ይህው ወይም እባክዎን ይጋበዙ ለማለት የሚያገለግል ቃል። *አቦል ጀባ።*
**ጀባ አለ** ግ (ተራ አነ.) ሰጠ።
**ጀባ** ስ ፀጉሩ ሳይመለጥ የተለፋ የበሬ ቆዳ።
**ጀብራራ "* ዠበረረ"** ስር **"ዠብራራ"** ን ተመ.
**ጀብዱ(ጀብድ፥ ዠብድ፥ ዠብዱ)** ስ የጉብዝና፥ የጀግንነት ስራ።
**ጀብደኛ** ቅ 1 ጀብዱ የሰራ። 2 ለዝና ሲል ሁኔታዎችን ሳያመዛዝን አጉል የሆነ የድፍረት ስራ የሚሰራ።
**ጀቦነ** ግ ሸፋፈነ፥ አለበሰ።
**ተጀቦነ** ግ ጠቅላላ ወይም መላ አካሉን ተሸፈነ።
**ጀተሬ "ዠተሬ"** ን ተመ.
**ጀነቶ** ስ የነጭና የቀይ ጠቃጠቆ ያለበት ድቡልቡል ዶቃ።
**ጀነነ** ግ አኮራ፥ አተበተ።
**ጅንን** ቅ ኩሩ።
**ተጀነነ** ግ ኮራ፥ ተቤተ።
**ጀነጀነ** ግ በብዛት ሰበሰበ፥ አስገባ፥ ጠቀጠቀ።
**ተጀነጀነ** ግ በብዛት ተሰበሰበ፥ ተጠቀጠቀ።
**ጀንበር "ጀምበር"** ን ተመ.
**ጀንዲ (ዠንዲ)** ስ ለመኝታ ንጣፍ የሚያገለግል የተለፋ የበሬ ወይም የላም ቆዳ።
**ጀንፈል(ጀፈል)** ስ ከነአምቡጡ የሆነ ወይም ያልተፈለፈለ ቡና።
**ጀውጃዋ(ዠውዠዋ)** ቅ ከውካዋ፥ አቅለቢስ።
**ጀዲ[መሬት]** ስ በታህሳስ ወር የሚወጣ የከከብ አይነት። በተጨማሪ **"ከከብ ቆጠራ"** ን ተመ.
**ጀጀረ** ግ የምግብ ፍላጎት አሳጣ።
**ጀጀበ** ዝ.ከ.
**ጀገነ** ግ ጎበዘ፥ ደፈረ፥ ጀግና ሆነ።
**ጀግና** ስ 1. ለሃገር፥ ለወገን መስዋእትነት ከፍሎ ጥሩ ተግባር ያከናወነ፤ ወኔ፥ ድፍረት በሚጠይቅ ሁኔታ ላይ ጀብዱ የሰራ። 2. ብርታት፥ ጥንካሬ በሚጠይቅ ስራ ላይ ችግርን ተቋቁሞ ለውጤት የበቃ ጎበዝ። 3. ወጣት፥ ጎረምሳ።
**ጀጎለ** ግ አጠረ፥ ቀጠረ፥ አጥር አበጀ።
**ጀጎል** ስ አጥር፥ ቅጥር።
**ጀፈጀፈ** ግ ብዙ ቅርንጫፍ አወጣ።
**ጀፍጃፋ** ቅ ብዙ ቅርንጫፍ፥ ቅጠል ያለው።
**ጀፍጀፎ** ቅ እጅብ ብሎ በብዛት የበቀለ (ቡቃያ፥ ችግኝ፥...)።
**ጁ** የ **"ጀ"** ፊደል ካእብ ዘር።
**ጁሆ** ስ መያዣ፥ መድን።
**ጂ** የ **"ጀ"** ፊደል ሳልስ ዘር።
**ጂምናስቲክ** ስ ሰውነትን ለማፍታታት፥ ለማዳበር... የሚሰራ የአካል ማሰልጠኛ ስፖርት።
**ጂምናዚየም** ስ ጂምናስቲክ ለመስራት የሚያገለግሉ የተለያዩ መሳሪያዎች ያሉበትና ጅምናስቲክ የሚሰራበት ትልቅ አዳራሽ።
**ጂኒ (ጅን)** ስ ሰይጣን።
**ጂኒው ተነሳበት** ቁጣ ቁጣ አለው፥ ተናደደ።
**ጂኒያም** ቅ (ስድብ) 1. ሰይጣናም። 2. ተናዳጅ።
**ጂና** ስ 1. የቀንድ ከብት ጅራት። 2. ከበሬ ጅራት ወይም ከበግና ከፍየል ቅልጥም ላይ ተገፎ እንደጅንፎ ከበትር ወይም ከዱላ ላይ የሚጠለቅ ቆዳ።
**ጂኦሎጂ** ስ የመሬትን አካል (እንደ ድንጋይ አፈር ማእድን፥... ያሉትን) አፈጣጠርና ምንነት የሚያጠና ሳይንስ፥ የከርሰ ምድር ጥናት።
**ጂኦሜትሪ** ስ የመስመሮችን፥ የማእዘኖችን፥ የወለሎችን ጠባይና ዝምድና የሚያጠና ሳይንስ።
**ጂኦተርማል** ስ ከከርሰ ምድር የሚገኝ የተፈጥሮ እንፋሎት ሃይል።
**ጂኦግራፊ** ስ ስለመሬት ገፅታ፥ ስለአገሮች አቀማመጥ፥ ስለወንዞች፥ ተራሮች፥ አየር ጠባይ

ህዝብ ሁኔታ፥... የሚያጠና ሳይንስ፤ የመልክአምድር ጥናት።

**ጃ** የ "ጀ" ፊደል ራብእ ዘር።

**ጃል** በንግግር ላይ መገረምን፥ መደነቅን፥ ግራ መጋባትን ለመግለፅ የሚያገለግል ቃል። *ምነው ጃል! እንዲህ ኣደረግህኝ።*

**ጃሎ**[1] ስ መሬት ለመቀየስ የሚያገለገል የመሃንዲስ ዘንግ።

**ጃሎ**[2]**[መገን]** በሽለላ ወይም በቀረርቶ ጊዜ እንደመግቢያ ሆኖ የሚያገለግል ቃል።

**ጃርት** ስ አካሉ በአደጋ ጊዜ በየአቅጣጫው እንደጦር በሚወረወር ጫፈ ሹል ነገር የተሸፈነ ድንች ዱባ፥ በቆሎ፥... የሚበላ አውሬ።



ጃርት

**የጃርት ወስፌ** ስ በጃርት ሰውነት ላይ እንደ ፀጉር የሚበቅል፥ መጠኑ እርሳስ የሚያህል፥ ውስጠ ክፍትና ቀለመ ዥንጉርጉር የሆነ፥ በአደጋ ጊዜ በየአቅጣጫው እንደጦር የሚወረወር ጫፈ ሹል አካል።

**ጃስ** አንድን ነገር እንዲያባርር ውሻን ሩጥ፥ ያዝ ለማለት የሚያገለግል ቃል።

**ጃንሆይ** "ትልቁ!"፥ ገናናው!" በማለት ነገስታትን ለመጥራት የሚያገለግል የአክብሮት መጥሪያ ቃል።

**ጃንደረባ (ዣን ደረባ)** ስ በጥንት ጊዜ ንግስቲቱን እንዲጠብቅ፥ እንዲያጫውት ተብሎ ቤተመንግስት ውስጥ እንዲቀመጥ ይደረግ የነበረ ስልብ።

**ጃንጥላ(ዣንጥላ)** ስ 1. ከዝናብ፥ ከፀሃይ ለመከላከል የሚያገለግል ጥላ። 2. ከፍ ካለ ቦታ ወይም ከአየር ወደ ምድር በቀስታ ለመውረድ የሚያገለግል እንደ ጥላ ያለ ነገር፤ ፓራሹት።

**በጃንጥላ ወረደ** በጃንጥላ (ፓራሹት) አማካይነት ከአውሮፕላን ላይ (ከአየር) ወደ ምድር ወረደ፤ እምድር ላይ አረፈ።

**ጃኖ** ስ ሰፊ የሆነ ቀይ ጥለት ያለበት ኩታ።

**ጃኖ የመሰለ** በጣም ቀይ የሆነ።

**ጃኬት** ስ አጭር ኮት።

**ጃዊሳ** ቅ 1. አካሉ ግዙፍ የሆነ ጉልበታም(ሰው)። 2. ሆዳም። 3. ቀማኛ፥ ወንበዴ።

**ጃዝ[ሙዚቃ]** ስ የተለያዩ የሙዚቃ ምት አይነቶችን የሚይዝና በእንቅስቃሴ የተሞላ ነፃ የአጨዋወት ስልት የተላበሰ ዘመናዊ ሙዚቃ።

**ጃጀ** ግ በጣም ከማርጀቱ የተነሳ አእምሮው በትክክል ማሰብ፥ ማስታወስ፥... ተሳነው።

**ጃፖኒ** ስ እጅጌ የሌለው ወይም እጅጌው ከትከሻ ላይ የሚቀር ቀሚስ፥ ሸሚዝ፥...።

**ጄ** የ "ጀ" ፊደል ሃምስ ዘር።

**ጄላቲ** ስ ከተለያዩ የፍራፍሬ አይነቶች የተዘጋጁ ቅመማት፥ ስኳር፥ ውሃ፥ የምግብ ቀለም፥... በአንድነት ተደባልቆ በበረዶ መልክ የሚዘጋጅ ጣፋጭ።

**ጄት** ስ ፈጣን የአውሮፕላን አይነት።

**ጄኔራል** ስ በወታደራዊ ክፍል ውስጥ ከሌተና ጄነራል በላይ ያለ ከፍተኛ የጦር መኮንኖች ማእረግ።

**ጅ** የ "ጀ" ፊደል ሳድስ ዘር።

**ጅላጅል** "ጀለ" ስር ተመ.

**ጅል** ዝ.ከ.

**ጅማሬ** "ጀመረ" ስር ተመ.

**ጅማት(ዥማት)** ስ 1. የደም ስር። 2. በተለይ ጡንቻማ በሆኑ የስጋ ብልቶች አካባቢ የሚገኝ ስር። 3. ለክራር ለበገና፥ ለደጋን ክር እንዲሆን ተፍቆ የከረረና የደረቀ የፍየል ወይም የበግ አንጀት።

**ጅማታም** ቅ (ስድብ) በጣም ቀጭን (ሰው)።

**ጅምላ** "ጀመለ" ስር ተመ.

**ጅምር** "ጀመረ" ስር ተመ.

**ጅረት(ዥረት)** ስ ወንዝ።

**ጅሬ (ጅር)** ስ በአንድ አለቃ (ገመሬ) የሚመራ የዝንጀሮ መንጋ።

**ጅራት (ዥራት)** ስ 1. በእንስሳት የኋለኛ አካል ላይ የሚገኝ፥ በአብዛኛው በፀጉር የተሸፈነ ተወዛዋዥ የሰውነት ክፍል፥ ጭራ እየተባለም ይጠራል። 2. በቅርፁ ወይም በያዘው ቦታ ጭራ (ጅራት) የመሰለ ነገር። *ጅራት ያለው ኮከብ የአውሮፕላን ጅራት።*

**ጅራት ሆነ** መጨረሻ ሆነ፥ ኋላ ቀረ።

**ጅራቱን (ጭራውን) ቆላ** ተለማመጠ።

**ጅራታም ኮከብ** ስ ጅራት መሰል ቅጥያ ያለው የኮከብ አይነት።

**ጅራፍ** ስ ከወደ ጫፉ ቀጭን ሆኖ ከወደ መያዣው ወይም ማንጠልጠያው በኩል እየወፈረ የሚሄድ ከልጥ ወይም ከቃጫ፥... የሚሰራ፥ ሲያወናጭፉት የሚጮህና ለመግረፊያ የሚያገለግል ገመድ፥ ጉንጉን ወይም የተሰፋ ጠፍር።




ጅራፍ

**ጅር** “ጅሪ” ን ተመ.

**ጅርጅር**

**ጅርጅር አለ** ግ ግርግር አለ፥ ወዲያና ወዲህ ተመላለሰ።

**ጅስ** የቀንድ ከብትን “ሂድ”፥ “ዞር በል” ለማለት የሚያገለግል ቃል።

**ጅስም** ስ ሰውነት፥ አካል፥ ገላ (ወሎ)።

**ጅብ** ስ 1.ከትከሻው ከፍ ብሎ ከጻሊው አጠር ያለ፥ መልኩ እንደየዝርያው ቀላ ያለ፥አፈርማ፥ግራጫ፥ አመድማ ሆኖ በአብዛኛው ዥንጉርጉር አለበለዚያም ሸልምልም የሆነ የማሽተትና የማየት ችሎታ ያለው ስጋ በል የዱር አውሬ(ስእሉን የዱር እንስሳ ስር ተመ.)።2. (ዘይ.)ጉልበተኛ። (ስድብ፥ዘይ.)ሆዳም፤ ስግብግብ።

**ጅብ ወሰደው** ጅብ በላው።

**የጅብ ምርኩዝ** ስ በወይና ደጋና በቆላ የሚበቅል የእፅዋት አይነት።

**የጅብ ሽንኩርት** ሽንኩርት የሚመስልና በዱር የሚገኝ የእፅ አይነት።

**[የ] ጅብ ጥላ** ስ ቀለሙ ነጣ ያለ፥ ዣንጥላ መሰል ቅርፅ ያለው፥ እንደእንጉዳይ ያለና በመስክ የሚበቅል የእፅዋት አይነት።

**ጅብሪል** ስ አፉ ቀይ፥ ክንፉ በስተላይ በኩል ጥቁር በስተውስጥ ነጭ የሆነ፥ ሃይለኛ ድምፅ ያለው የአሞራ አይነት።

**ጅብራ (ዥብራ)** ስ ግንዱ ቀጥ ያለና ረጅም፥ ቅጠሉ ሰፋፊ የሆነና ጀደጋ የሚበቅል በኢትዮጵያ ብቻ የሚገኝ የእፅዋት አይነት።

**ጅን** “ጂኒ” ን ተመ.


**ጅንን** “ጀነነ” ስር ተመ.

**ጅንጀሮ** “ዝንጀሮ” ን ተመ.

**ጅንግላ** ስ 1. እንደ እግር ብረት ለማሰሪያ የሚያገለግል ግንድ። 2. የአባያ በሬ መቅጫ ረጅም ግንድ፤ እንዛዝላ (እንደ ቀንበር በትከሻው የሚጎትተው)።

**ጅንፎ (ዥንፎ)** ስ በትር እንዳይሰነጠቅ በብትሩ ቂጥ ላይ የሚሰካ ከብረት የሚሰራ ጥምዝ ቀለበት።

**ጅዋጅዌ (ዥዋዥዌ)** ስ ግራና ቀኝ በተተከሉ የእንጨት ወይም የብረት ምሰሶዎች አናት ላይ ከተጋደመ እንጨት ወይም ብረት ጋር በገመድ ታስሮ በተንጠለጠለ መቀመጫ ላይ ተቀምጠው ወደፊትና ወደሗላ በአየር ላይ በመወርወር ልጆች የሚጫወቱበት መጫወቻ፤ ጨዋታውም ጅዋጅዌ ይባላል።



ጅዋጅዌ

**ጅው (ዥው)**

**ጅው አለ** ግ ሄደ።

**ጅው ብሎ ሄደ** 1. ምንም ሳያቆመው፥ ሳያግደው ነጎደ። 2. ወደግራ ወይም ወደቀኝ ሳያመራ ወይም ሳይቆም ቀጥ ብሎ ሄደ።

**ጅው አለበት** ራሱን አዞረው።

**ጅው ያለ** ቀጥ ያለ (መንገድ፥ ገደል፥...)።

**ጅው ያለ** ገደል ጥልቀት ያለው ቀጥ ያለ ገደል።

**ጅው አደረገ** ግ በአንድ ጊዜ ጭልጥ አድርጎ ጠጣ።

**ጅጊ (ጅጌ)** ስ የያንዳንዱን ሰው ስራ በየተራው በቡድን እየሆነ ለማከናወን፥ ለማካሄድ በስምምነት የሚፈጠር ጊዜያዊ የስራ ህበረት፤ ደቦ፤ ወበራ።

**ጅግራ(ዥግራ)** ስ ስጋው የሚበላ፥ በዱር የሚገኝ እንደዶሮ ወይም እንደቆቅ ያለ ዝንጉርጉር የአሞራ ወገን(ስእሉን አሞራ ስር ተመ.)

**ጆ** የ “ጆ” ፊደል ሳብእ ዘር።

**ጆሮ** ስ 1. ለመስማት ወይም ለማዳመጥ የሚያገለግል የሰውነት ክፍል(ስእሉን ራስ ስር ተመ.)። 2. የሲኒ፥ የኩባያ የእንስራ፥... መያዣ።

**ጆሮ ዳባ ልበስ አለ** ሰምቶ እንዳልሰማ ሆነ።

**ጆሮውን ሰጠ** 1. ሆን ብሎ አዳመጠ። 2. ሰምቶ ተቀበለ፥ አመነ።

**ጆሮውን ተከለ** አንድ ነገር ለመስማት፥ ለማዳመጥ አቀበቀበ፥ ጣረ።

**ጆሮውን ቀሰረ** ለማዳመጥ ተዘጋጀ፥ ጓጓ፥ ፈለገ።

**ጆሮውን ጣለ** 1. ለማዳመጥ አቀበቀበ፥

ጆሮውን ዝግጁ አደረገ። 2. በህመም ምክንያት ጆሮውን ወደታች አንጠለጠለ፥ አንዘለዘለ (ለምሳሌ ውሻ)።

**ጆሮዬ ገማ** በየጊዜው የምሰማው መጥፎ ነገር በዛ፥ ሰለቸኝ።

**ጆሮ ለጆሮ** ቅርብ ለቅርብ።

**ጆሮ የሚጠልዝ** ጆሮን የሚያሳምም፥ የሚያደነቁር ከፍተኛ ድምፅ።

**የጆሮ ልም/ቅጠል** ስ ቀለበትን፥ ጉትቻን፥ ሎቲን ለማንጠልጠያ እንዲሆን የሚበሳው፥ ከወደታች ያለው የጆሮ ጫፍ(ስእሉን ራስ ስር ተመ.)።

**የጆሮ ታምቡር** ስ በጆሮ ውስጠኛ ክፍል የሚገኝ፥ የድምፅ ሞገድ ሲያርፍበት የሚርገበገብ ስስ ነገር ወይም አካል።

**የጆሮ ወርቅ** ስ ከወርቅ የተሰራና በጆሮ ላይ የሚንጠለጠል ጌጥ።

**ጆሮ ደግፍ** ስ ከጆሮ በታች የሚገኙ እጢዎችን የሚያሳብጥ በሽታ።

**ጆሮ ግንድ** ስ በጆሮ አካባቢ ያለ የሰውነት ክፍል።

**ጆሮ ግንዱን አለው** 1. ከጆሮው አካባቢ መታው። 2. ሸጠው። 3. አታለለው።

**ጆሮጠቢ** ስ ወሬ እየለቃቀመ የሚያቀብል፤ ሰላይ።

**ጆተሬ** "ጕተሬ"ን ተመ.

**ጆተኒ (ጆቶኒ)** ስ የእግር ኳስ ሜዳና የተጫዋቾች ምስል ያሉበትን ቅርፅ ከነእጀታዎቹ እንዲይዝ ተደርጎ በጠረጴዛ መልክ የተሰራ የኳስ መጫወቻ፤ ጨዋታውም ጆተኒ ይባላል።

**ጆፌ** ስ ጀፍጀፋ፤ ፀጉሩ ወይም ላባው፥... ብዙ የሆነ።

**ጆፌውን** ጣለ በአንድ ነገር ዙሪያ ወይም አካባቢ አንዣበበ።

**ጆፌ አሞራ** ስ ላባው ብዙ የሆነ ትልቅ አሞራ፤ ጥንብ አንሳ (ስእሉን አሞራ ስር ተመ.)።

**ጆፍጆፌ** ስ ብዛትና ርዝመት ያለው ፀጉር።

**ጇ** ስ የ "ጀ" ፊደል ፍንፅቅ ዘር።